# ኝጣፋ

## የመሣሪያዎች አገልግሎት

አዘጋጅ ሞንቴ ሳይር
ትርጉም ግርማዊ
እርማት ቁምላቸው ፋንታሁን

ኤ-ኤን-ፒ
1996

Copyright 2003
First printing 1000 copies.

Translated into Amharic from the English book
Total Youth Resources for Africa
Edited and Adapted for Africa by Monte Cyr

Translator: Girmawi
Editing: Kumlachew Fantahun
Cover art: Roman Tadesse

Prepared by:
ANP
PO Box 8974
Addis Ababa
Ethiopia

## ማውጫ

ገጽ

ለአንባብያን—5
የመጽሐፉ ዓላማ—6
ለአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዕቅድ ማውጣት—16
አጠቃላይ የወጣቶችን አገልግሎት መምራት—18
አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት መርሐግብር ማዘጋጀት—25

ዝብመኛዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች
ይቅርታ—39
የቤተሰብ ችግሮች—43
ውሳኔዎችን ማሳለፍ—47
ሌሎች በኛ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መቆጣጠር—51
ቅድስና: የራሴን ወይም የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል56
ውርጃ: የህይወትና የሞት ጉዳይ! —60
ቁጡ የምትሆነው ለምንድነው?—64
መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? —68
ቆሻሻን ብንዘራ...
ቆሻሻን እናመርታለን —72
ብቸኝነትን መቋቋም—76
የማበረታታት ስጦታ—81
ራስህን መቆጣጠር—87
«አትጨነቁ!» —93
ጸሎትህ ኃይልን የተላበሰ ይሁን—98
ኃጢአት መሆኑን እንዴት አውቃለሁ?—104
ለትችት ወይም ለስደት ምላሽ የምንሰጠው እንዴት ነው?108
ሀብታችን ተቆጣጥሮናል?—112
እርስበርሳችን መደጋገፍ አለብን—119
እምነትህን ማሳደግ—124
የስኬት አባዜ—128
ሱስ አስያዥ ዕፆች: መጠቀም ወይም መተው—133
ዛሬ ዘላለም አይደለም—138

የሐሰተኛ ሃይማኖቶች አደጋ——144
መዝናናት ትክክል ነው ወይስ...? ——153
እግባብነት የጎደለው የፍቅር ግንኙነት ——158
ስሜቶች፡ ጠቃሚዎች ወይስ አዛዦች?——163
ጭንቀትን መከላከል——168
ደኅንነትን እንዳገኘሁ እንዴት አውቃለሁ?——173
የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ——178
በአግባቡ አይሆንም ማለትን ማወቅ——183

**የወጣቶች አገልግሎት አስተዋጽኦዎች**

የሚሲዮን አገልግሎት——191
በዕለተገና ክርስቶስን ማየት ይቻላልን? ——195
ይኸው ደስታ በልቤ ውስጥ ፈሷል——203
ጊዜው አሁን ነው——209
አፕረተር፣ ክርስቶስን አገናኘኝ (ጸሎት)——214

**የወጣቶች ስብሰባዎች**

እንደገና መጀመር——219
አዳዲስ ጨርቆች፣ አዲስ ዳሰሳ——223
የዓሣ አጥማጅ——229
ኦንተና ዳኛው——236
ቤተመቅደስን እንዴት መገንባት ይቻላል? ——241
የጥፋት ቤተመቅደስ——248
ታላቅ ሁን——255
የእግዚአብሔር አሸናፊ ቡድን ——260
የለውጥ በዓል——265
ዋስትና——269

አማራጭ የመክፈቻ እንቅስቃሴዎችና ጨዋታዎች——276


## ለአንባብያን

ወጣቶች ለነገይቱ ቤተክርስቲያን ህልውና ወሳኝ ኃይላት በመሆናቸው ይህንኑ ኃላፊነት የሚወጡበትን ዓቅም መገንባቱ ለቤተክርስቲያን ወሳኝ ነው:: ይሁንና፣ ይህንን ዓቅም እንዴት መገንባት እንደሚቻል ለብዙዎቻችን ግልጽ አይደለም::

ለዚህም አንዱ ችግር በወጣቶችና በአዋቂዎች መካከል የሚገኘው የዕድሜ ክፍተት ወጣቶችንና አዋቂዎችን የተለያዩ ዓለማት ዜጎች ለማድረግ መብቃቱ ነው:: አዋቂዎች የወጣቶችን ዓለም ረስተውታል:: ወጣቶች ደግሞ ገና ከአዋቂዎች ዓለም አልደረሱም:: ለወጣቶች የራሳቸውን ዓለም ያማከለ ጠቃሚ አገልግሎት ካልተበረከተላቸው የነገይቱን ቤተክርስቲያን ሲረከቡ ይቅርና እምብዛም በክርስትና ሕይወታቸው ሊገፉ አይችሉም:: ለዚህም ነው ይህ መጽሐፍ ለቤተክርስቲያን ጠቃሚ የሚሆነው::

ከባህርያቸው ተቅበጥባጭነት የተነሣ ወጣቶች ለብዙ ሰዓታት ቁጭ ብለው ረዥም ስብከት ሊያዳምጡ አይችሉም:: በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ በጨዋታዎች (ጌሞች)፣ እንቅስቃሴዎች፣ ድራማዎች፣ ጭውውቶች፣ ውይይቶች... የተሞሉ ትምህርቶች ተካተዋል:: ይህም የወጣቶች አገልግሎት መሪ በነዚህ መርሆች ላይ በመመሥረትና ከእግዚአብሔር መንፈስ ምሪትን በመቀበል ፍሬያማ አገልግሎትን እንዲያበረክት ያስችለዋል ብለን እናምናለን::

መጽሐፉ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የተተረጎመ ቢሆንም፣ አብዛኞቹን የባሕል ችግሮች ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል:: ይሁንና፣ እንደ ስሞች፣ አካባቢዎችና መዝሙሮች ያሉ እንዳሉ የቀረቡ ነገሮች ስላሉ፣ የወጣቶች አገል.ጋዮች በአገራዊ ስያሜዎች ተክተው ቢጠቀሙ መልካም ይሆናል::

የእንግሊዝኛ መዝሙሮቹን እንዳለ ያስቀመጥሁት አንዳንድ አብያተክርስቲያናት የአማርኛና የእንግሊዝኛ መዝሙሮችን የሚጠቀሙ በመሆናቸው ነው:: ከእንዲህ ዓይነቶቹ አብያተክርስቲያናት መካከልም ይህን መጽሐፍ ያሳተመው የናዛሬን ቤተክርስቲያን አንዱ ነው:: በመሆኑም የእንግሊዝኛ መዝሙሮቹ የግድ መዘመር ያለባቸው አይደሉም:: የወጣቶች አገልግሎት መሪ እንደ አመቺነቱ ለቡድኑ የሚስማሙትን የአገራችንን መዝሙሮች መርጦ ሊጠቀም ይችላል::

ጨዋታዎቹ (ጌሞች)፣ ጭውውቶችና ድራማዎች በአብዛኛው ብዙ ወጪ በማይጠይቅ መልኩ የተዘጋጁ ስለሆኑ፣ ማንኛውም የወጣቶች አገልግሎት መሪ ቢጠቀምባቸው መልካም ነው:: ይህን መጽሐፍ እጅግ ጠቃሚ ካደረጉትና የትምህርት ባለሙያዎችንም ካስመሰገኑት ነገሮች መካከል አንዱ የነዚህ ጨዋታዎችና እንቅስቃሴዎች ከትምህርቱ ጋር ተሰናኝቶ መገኘት ነው:: በመሆኑም፣ እንቅስቃሴዎቹን ወደ ዳር ትቶ በትምህርቱ ላይ ብቻ ማተኮሩ ያው የተለመደውን የአዋቂዎች ትምህርት ከማቅረብ እምብዛም የተሻለ አይሆንም::

ግርማዊ

# የመጽሐፉ ዓላማ

**ምሳሌ**

ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት መርከቦች በአንድ ወደብ ውስጥ በጸጥታ ተቀምጠዋል። ምንም እንኳዋን እነዚህ መርከቦች ከውጭ ሲታዩ አንድ ዓይነት ቢመስሉም፣ በጣም የተለያዩ ነበሩ። የሁለት የተለያዩ ኩባንያዎች ንብረቶች ነበሩ። አንደኛው የማክዲል የትራንስፖርቴሽን ኩባኒያ ንብረት ሲሆን፣ ሌላኛው የስሚዝ የትራንስፖርቴሽን ኩባንያ ንብረት ነበር።

አንድ ቀን ሁለቱም ኩባንያዎች መርከቦቻቸውን ለማደስና ለባሕር ላይ አገልግሎት ዝግጁ ለማድረግ ፈለጉ። ከብዙ ሰዓታት ድካምና ወጪ በኋላ፣ መርከቦቹ ተሳፋሪዎቻቸውን ጭነው ለመጓዝ ተዘጋጁ። መርከቦቹ ታድሰው ሥራ የጀመሩበት ይህ ቀን እንዴት ታላቅ ነበር! እያንዳንዱ መርከብ ላይ ሰዎች ሽርጉድ ይሉ ጀመር። መርከቦቹ ግርማሞገስ ተላብሰው ጉዟቸውን ሲጀምሩ የሁለቱም ኩባንያዎች ልብ ይዘል ጀመር።

ለተወሰነ ጊዜ ሁለቱም ኩባንያዎች ትርፋማ ሥራ ሲያከናውኑ ቆዩ። ከዚያ በኋላ ግን ማክዲል ኩባንያ በስኬታማነቱ ቢገፋም፣ ስሚዝ ከሥራው ጋር ግብግብ ለመግጠም ተገደደ። በተከሰተው ችግር ምክንያት ከተደረገው ጥናት ለመረዳት እንደተቻለው፣ ማክዲል መደበኛ ጥገናዎችን ከመካሄዱም በላይ፣ ሌሎች አገልግሎቶችንም ጨምሯል። ከዚህም በላይ፣ ማክዲል ሥራ በማይበዛባቸው ወራት መርከቦቻቸውን በደረቅ ወደብ ላይ እንደሚያሳርፉ ለማወቅ ተችሏል። ይህም በዓመቱ ውስጥ መርከቦቹ የሚያጓጉዛቸው ተሳፋሪዎችና ጭነቶች ቁጥር እንዲቀንስ ያደርጋል። የስሚዝ ኩባንያ ግን እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች ብዙ ገንዘብ እንደሚያከስሩ በማሰብ መርከቦቹ በየሳምንቱ ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል። የስሚዝ ኩባንያ የተቻለውን ያህል ሰው በማሳፈር ከትኬት ሽያጭ ብዙ ገንዘብ ለማሰባሰብ ይጥር ነበር። ይህንንም ለተወሰነ ጊዜ ተግባራዊ ሊያደርግ ችሏል።

አያሌ ወራት አለፉ። ቀስ በቀስ አንዳንድ ነገሮች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። በስሚዝ መርከብ ውስጥ የሚሳፈሩ ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ መጣ። በመደበኛነት ከደረቅ ወደብ ላይ እንዲያርፍ የሚደረገው የማክዲል መርከብ ግን ደንበኞቹን ለማርካት እየጣረ አገልግሎቶቹንና መርሐግብሩን ማሳደጉን ቀጠለ። የኋላ ኋላ የስሚዝ መርከቦች ተሳፋሪዎቻቸውን ሊያጓጉዙ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ። በመሆኑም፣ ወደ ዕቃ ጫኝነቱ ተግባር ተለወጡ።

በሁለቱ ኩባንያዎች መካከል የነበረው ልዩነት ምን ይመስልሃል? የሚክዲል ኩባንያ እያደገ የሄደውና የስሚዝ ኩባንያ የከሰረው ለምን ይመስልሃል? እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች መቼም ቀላል ምላሾች.



የሏቸውም። በዚህ ሁኔታ ግን (እንደ ብዙዎቹ ሁኔታዎች ሁሉ) መልሱ ወደ አንድ ሁነኛ ጉዳይ ያመለክታል። ይኸውም የዓላማ ጉዳይ ነው።

የማክዲል ኩባንያ የመርከቡ ዓላማ ለተሳፋሪዎቹ ብቃት ያለው አገልግሎትና መርሐግብር መስጠት እንደሆነ ተገንዝቧል። ስለሆነም፣ ለዚህ ኩባንያ ሃላፊዎች መርከባቸው በውሃ ውስጥ መርመስመሱ ብቻ በቂ አልነበረም። ዓላማቸው ብዙ ሕዝብ አጣቦ መጫን ብቻ አልነበረም። ዓላማቸው የተሳፋሪዎቻቸውን ፍላጎቶች ማሟላት ነበር። ይህንንም ያደረጉት ደንበኞቻቸውን «ለማርካት» ከቻሉ ትርፋማ ንግድ እንደሚያንቀሳቅሱ ስለተገነዘቡ ነው።

በሌላ በኩል፣ የስሚዝ ኩባንያ ዓላማ አንድ ብቻ ነበር። ይኸውም ትርፍ ማግበስበስ ነበር። ኩባንያው በትርፍ ላይ በማተኮሩ ብዙ ሕዝብ በመጫንና ተደጋጋሚ ጉዞ በማድረግ ላይ ትኩረት አድረገ። ኩባንያው የከሰረው በስንፍና ምክንያት ሳይሆን ዘላቂነትን ከግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባቱ ነው።

በወጣቶች አገልግሎት ረገድም፣ ለተመሳሳይ ችግሮች የሚያጋልጡ ሁኔታዎች አሉ። የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች ጥንቃቄ ካላደረጉ፣ የወጣቶች አገልግሎት መርሐግብር ዓላማ ሲደበዝዝ... እንዲሁም እስከናካቴው ሊጠፋ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወደ ፍጻሜ ያደርሳሉ ተብለው የታሰቡት ነገሮች፣ ማለትም የወጣቶች መርሐግብሮችና ተግባራት በራሳቸው ፍጻሜ ይሆናሉ። በዚህም ጊዜ፣ «ፍሬያማ» የወጣቶች አገልግሎት የሚለካው በተወሰኑ መርሐግብሮች ቁጥርና. ውስብስብነት ይሆናሉ። ምንም እንኳዋን እንዲህ ዓይነቱ የወጣቶች አገልግሎት በብዛት የሚታይ ቢሆንም ውጤታማ እለመሆኑ ግልጽ ነው። «ፍሬያማ» የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች የወጣቶችን አገልግሎት ዓላማ የሚገነዘቡና መሪነታቸውን ዓላማ ባለው መንገድ ለወጣቶች የአገልግሎት ስልት መመሪያ ለመቀመር የሚጠቀሙ ሰዎች ናቸው።

**የዓላማ መግለጫ ምንድነው?**

በአጭር አገላለጽ፣ የማንኛውም ድርጅት ዓላማ ድርጅቱ የሚኖርለት አጠቃላይ፣ ሁሉን አቀፍ፣ የረዥም ጊዜ ምክንያት (ወይም ምክንያቶች) ነው። እያንዳንዱ ድርጅት እንዲህ ዓይነት የዓላማ መግለጫ ሊኖረው ይገባል። የድርጅቱን የህልውና ምክንያት የሚያስረዳው ይኸው ዓላማ ነው። በሁሉም የአመራር ደረጃዎች ላይ የሚሠራ መሆን አለበት። የዓላማ መግለጫ ድርጅቱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ሁሉ የሚለካ ዘንግ ይሆናል። እስኪ ያንተን የዓላማ መግለጫ ቀጥለን እንመልከት።

**የምትኖረው ለምንድነው?**

ለአገልግሎትህ የዓላማ መግለጫ አዘጋጅተሃል? ካልሆነ፣ ቀጥሎ የቀረበውን ካለህበት ሁኔታ ጋር በማዛመድ፣ በማሻሻል፣ ወይም

በመጠቀም የራስህን መግለጫ ጻፍ:: «የወጣቶች አገልግሎቶች ዓላማ አባሎቹን በክርስቲያናዊ እምነትና በተቀደሰ ባህርይ ማነጽና የእግዚአብሔርን ቃል፣ ብሎም የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ማስተማር ነው:: ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣትና በአምልኮ፣ በምስክርነት፣ በደቀመዝሙርነትና በህብረት እማካኝነት ወጣቶችን ለቤተክርስቲያን አጠቃላይ ተልዕኮ ማስታጠቅም የወጣቶች አገልግሎቶች ዓላማ ሊሆን ይገባል::» ይህ አንድ የዓላማ መግለጫ ነው:: ተስማሚ ነው አይደል? ይህ አጠቃላይ... ሁሉን አቀፍ... በአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ውስጥ የምንሳተፍበትን የረዥም ጊዜ ምክንያት የሚገልጽ... የወጣቶች አገልግሎት መሪዎችን ጉጉት የሚያንጸባርቅ መግለጫ... ብዙዎቻችን ለመሄድ የምንመርጠው አቅጣጫ ነው::

ምናልባት አንተ የወጣቶች መሪ ወይም ለወጣቶች አገልግሎት ፍላጎት ያለህ ሰው ትሆናለህ:: የወጣቶችን አገልግሎት ለመጀመር እየተዘጋጀህ ወይም ቀደም ሲል የጀመርከውን አገልግሎት የምታሻሽልባቸውን መንገዶች እየፈለግሁ ይሆናል:: ሁኔታህ ምንም ይሁን ምንም፣ የአገልግሎት ጥረቶችህን ዋንኛ ዓላማ ማወቅህ ጠቃሚ ነው:: ይህንን ካመንህ፣ የዚህን የወጣቶች አገልግሎት የዓላማ መግለጫ መሠረታዊ ክፍሎች ለመመልከት መሻትህ አይቀርም::

1. እንደ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች የመጀመሪያው ዓላማችን ወጣቶችን በክርስቲያናዊ እምነት ማነጽ ነው:: በቀላል አነጋገር፣ እንደ የወጣቶች አገልግሎት መሪ ተግባርህ ወጣቶችህን ካሉበት መንፈሳዊ ደረጃ ወደ ጠለቀ ለእግዚአብሔር የመሰጠት ደረጃ ማድረስ ነው:: የትኞቹም ሁለት ወጣቶች በመንፈሳዊ ጉዟቸው እኩል ደረጃ ላይ ሊሆኑ እንደማይችሉ አለጥርጥር ትገነዘባለህ:: ለአፍታ ቆም በልና እያንዳንዱን የቡድንህን አባል ገምግም:: አንድ ቡድን ታዳጊ፣ መካከለኛና ወደ ጎልማሳነት የተጠጉ ወንድና ሴት ወጣቶች ይኖሩታል:: ከጥሩ ቤተሰብና ከፈራረሰ ቤተሰብ የመጡ ወጣቶች እንደሚኖሩም ግልጽ ነው:: ደፋርና ቀልቀል የሚሉ፣ እንዲሁም ዓይናፋርና ዝምተኛ ወጣቶችም ይኖራሉ:: አንዳንዶች በቤተክርስቲያን የወጣቶች መርሐግብር ውስጥ በንቃት ሲሳተፉ፣ አንዳንዶች ግን እስከዚህም አይሳተፉም:: አንዳንዶች ለደቀመዝሙርነት ህይወት ራሳቸውን የሰጡ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ግን አይደሉም:: ፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት መሪ የቡድኑን አባላት ግላዊ ፍላጎቶች ለይቶ በማወቅ፣ በእያንዳንዱ ወጣት ህይወት ክርስቲያናዊ ብስለትንና ዕድገትን ሊጭሩ የሚችሉትን መርሐግብሮች ያካሂዳል:: ይህም በየትኛውም መንፈሳዊ የብስለት ደረጃ የሚገኙትን ወጣቶች የሚያካትት ነው:: ወጣቶችን በክርስቲያናዊ እምነት ለማነጽ የሚከተሉት ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው::



*ሀ. የበሳል ክርስቲያናዊ ህይወት ምሳሌ (ሞዴል) ሁኑላቸው::* ወጣቶች ሌሎችን የመከተል ዝንባሌ አላቸው:: የሚወዷቸውንና የሚያደንቋቸውን ሰዎች ይከተላሉ:: ስለሆነም፣ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች ክርስቲያናዊ ሞዴሎች መሆናቸው ጠቃሚ ነው:: የዩኤስኤ ካምፓስ ላይፍ ዳይሬክተር የሆኑት ቢል ሚይር እንደሚሉት፣ «ክርስቲያናዊ ህይወት እንደ ልብስ የምንለብሰውና የምናወልቀው አይደለም እንጂ፣ ክርስቲያናዊ ህይወትን በሞዴልነት ማሳየት ልብሶችን በሞዴልነት እንደማሳየት ነው:: በልብስ መደብሮች ውስጥ ወጣት ሴቶች ልብሶችን በሞዴልነት በሚያሳዩበት ጊዜ፣ ልብሱ በሰው ላይ ሲለበስ ምን እንደሚመስል ለብሰው ያሳያሉ:: አንድን ልብስ በመስቀያ ላይ ማየት በሰው ላይ ከማየት የተለየ ነው:: ስለሆነም፣ ሞዴሎቹ ለሰዎች፣ 'እነዚህ ልብሶች በእኔ ላይ ምን ይመስሉ ይሆን?' የሚለውን ውስጣዊ ጥያቄ ይመልሳሉ:: ክርስቲያናዊ ህይወትን በሞዴልነት በምናሳይበት ጊዜ ለወጣቶች እንደ ፍቅር፣ የባርነት አገልግሎትና ታዛዥነት ያሉትን ቃላት ፍችና የህይወት ተዛምዶ ማሳየታችን ነው::»

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ባስተላለፈው መልእክቱ ቀጣይነት ያለውና ክርስቶስን የሚመስል መሪ/ሞዴል አስፈላጊ መሆኑን አመልክቷል:: «በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድ፣ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ» (1ኛ ተሰ. 2:10)::

*ለ. ከወጣቶቹ ጋር በግል አብረሀ አሳልፍ::* አብዛኞቹ አጥቢያ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች ከወጣቶቻቸው ጋር ትርጉም ያለው የአንድ ለአንድ ግንኙነት የመመሥረት አቅም አላቸው:: የትኛውም ፕሮግራም ወይም ተግባር ከወጣቶች ጋር የሚደረገውን የግል ግንኙነት ሊተካ አይችልም:: የወጣቶች መሪዎች ከወጣቶች ጋር የግል ጊዜ ከሚያሳልፉባቸው መንገዶች መካከል ስልክ መደወል፣ ማስታወሻዎችንና ፖስትካርዶችን መለዋወጥ፣ የቤት ለቤት ጉብኝቶችና ወደ አንድ ስፍራ አብሮ መሄድ ይገኙባቸዋል:: ጥልቅ ግንኙነቶች የሚፈጠሩትና የሕይወት ለውጥ የሚከሰተው እንዲህ ባሉት ግላዊ ግንኙነቶች ውስጥ ነው::

በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ ያሳለፍከውን አገልግሎት መለስ ብለህ በምትመለከትበት ጊዜ ከፍተኛ ውጤት ያገኘኸው ከስብሰባዎችና መርሐግብሮች ሳይሆን ከወጣቶቹ ጋር ከነበረህ የአንድ ለአንድ ግንኙነት መሆኑን ትገነዘባለህ:: ክርስቶስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የጠለቀ ትርጉም ያለው ጊዜ ያሳለፈው በባህር ዳርቻዎች አካባቢ ለብዙ ሕዝብ በሚያስተምርባቸው ጊዜያት ሳይሆን ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ በሚጓዝባቸው፣ ዓሣ በሚያጠምድባቸው፣ በሚጸልይባቸውና በሚሠራባቸው ጊዜያት እንደነበረ ማስታወሱ ጠቃሚ ነው:: በነዚህ

ጊዜያት የአንድ ለአንድ ግንኙነት በመፈጠሩ ደቀመዛሙርቱን ለማወቅና ለማፍቀር ችሏል:: እነሱም ሊወዱትና ሊከተሉት በቅተዋል:: ጳውሎስ ይህንኑ የአገልግሎት መርህ እንዲህ ሲል ገልጾአል:: «ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጽናናን እየመሰከርንላችሁም፣ አባት ለልጆቹ እንደሚሆንን እንደሆንን ታውቃላችሁና» (1ኛ ተሰ. 2:11-12)::

*ሐ. በፍላጎቶች ላይ የተመሠረቱ መርሐግብሮችንና እንቅስቃሴዎችን በማቀድ ተግባራዊ አድርግ::* ከወጣቶቹ ጋር የምታደርገው የግል ግንኙነት ፍላጎቶቻቸውን በቅርብ እንድትገነዘብ ሊያስችልህ ይገባል:: ሌሪ ሪቻርድስ በመጽሐፋቸው ውስጥ እንደገለጹት፣ ወጣቶች በጉርምስና ዕድሜያቸው አምስት ፍላጎቶች አሏቸው:: እነዚህም የሚከተሉት ናቸው::

1. አንድ ወጣት ስለራሱ ጤናማ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል::
2. አንድ ወጣት መልካም ማህበራዊ ችሎታዎችና ጓደኞችን የማፍራት ችሎታ ሊኖረው ይገባል:: ይህም ከሰዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርግባቸውን መንገዶች እንዲያውቅ ይረዳዋል::
3. አንድ ወጣት ከተቃራኒ ጾታዎች ጋር ጤናማ አመለካከት ሊኖረውና ተገቢውን ግንኙነት ሊመሠርት ይገባል::
4. አንድ ወጣት ለመረጣቸው ሃይማኖታዊ እምነቶችና ሥነምግባራዊ እሴቶች ራሱን ሊሰጥ ይገባል::
5. አንድ ወጣት ራሱ የመረጣቸውን እሴቶችና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች መለየትና በነዚሁ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ሕይወት መምራት አለበት::

ውጤታማ የወጣቶች አገልግሎት መሪ እነዚህን የጉርምስና ዘመን የዕድገት ፈለጎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መርሐግብሮቹንና ተግባሮቹን ያዘጋጃል:: በዚህም ጊዜ፣ «ይህ መርሐግብር ወይም ተግባር ወጣቶቹ በሳልና ሁለንተናዊ ብቃት ያላቸው አማኞች ሆነው እንዲያድጉ የሚረዳቸው እንዴት ነው?» ሲል ራሱን ይጠይቃል:: መርሐግብሮች የሚዘጋጁት ይህን ጥያቄ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል::

*መ. ዕድገትን በወጣቶች ቁጥር ሳይሆን በሚያሳዩት መንፈሳዊ ዕድገት ለካ::* ወጣቶቹ ንቁዎች በመሆናቸው ብቻ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እያደጉ ናቸው ብለህ ልትገምት አይገባም:: ዕድገትን የማያመጣ ከሆነ አንድን ተግባር ለተግባራዊነቱ ብቻ ማከናወኑ እርባና የለውም:: አንድ ወጣት በቤተክርስቲያን ተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊ ሊሆንና በተመሳሳይ ጊዜ ክርስቶስን በመምሰሉ ረገድ እውነተኛ የሕይወት ለውጥ ላያሳይ ይችላል:: ስኬታማነትህን በወጣቶች ተግባራትና በተሳታፊ ወጣቶች ብዛት መለካቱ ተገቢ አይሆንም:: ነገር ግን በወጣቶቹ የእምነት ትጋት፣ የፍቅር ሥራና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ካላቸው ተስፋ የተነሣ በሚያሳዩት ትዕግሥት ስኬትህን



ብትለካ መልካም ነው (1ኛ ተሰ. 1:3):: እነዚህ በወጣት ደቀመዛሙርት ሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ ነገሮች የፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት መለኪያዎች ናቸው::

2. የአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዓላማ ወጣቶችን በተቀደሰ ባሕርይ መገንባት ነው:: የወጣቶች መሪ እንደመሆንህ መጠን፣ ያንተ ተግባር ወጣቶቹን ማዝናናት ወይም አሁን ያላቸውን መንፈሳዊነት ጠብቀው እንዲቆዩ ማድረግ ብቻ አይደለም:: ወጣቶቹ በሚገባ መዋኘት ሳይችሉ ውሃን በእግራቸው መምታታቸው ብቻ በቂ አይደለም:: ወጣቶቹ ወደ ቅድስና ሕይወት ዘልቀው እንዲገቡና እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው፣ ነፍሳቸው፣ አሳባቸውና ኃይላቸው፣ ባልንጀሮቻቸውን ደግሞ እንደራሳቸው እንዲወዱ በቃሉና በሕይወት ምሳሌነትህ ልታበረታታቸው ይገባል:: እንደ ሌሎች የዕድሜ ክልሎች ሁሉ ወጣቶችም ክርስቶስን እንዲመስሉ፣ ባለማቋረጥ የክርስቶስን የሚመስል አሳብና አመለካከት ይዘው እንዲኖሩና ለእግዚአብሔር ፍሬያማ አገልግሎትን እንዲያበረክቱ ተጠርተዋል::

3. ሦስተኛው አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዓላማ ለወጣቶች የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነው:: እንግዲህ ተግባራችን ወጣቶች በሳልና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች ሆነው እንዲያድጉ ማገዝ ከሆነ፣ መሣሪያችን ምን ሊሆን ይገባል? በቀላል አገላለጽ መሣሪያችን የእግዚአብሔር ቃል ነው:: እንዲያውም ከተፈለገው ግብ እንድንደርስ የተሰጠን እጅግ ጠቃሚው መሣሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ለምን? ምክንያቱም፣
ሀ. ወጣቶች የእግዚአብሔርን ማንነትና ምንነት የሚያውቁት ከቃሉ ነው (ሆሴዕ 6:6)::
ለ. ወጣቶች ስለራሳቸውና ስለሚኖሩባት ዓለም እውነትን የሚያውቁት ከእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 8:31-32)::
ሐ. ወጣቶች የሚገሰጹት፣ የሚማሩት፣ የሚታረሙት፣ የሚሰለጥኑትና ብቃትን የሚላበሱት በቃሉ ነው (2ኛ ጢሞ. 3:16-17)::

ከላይ የቀረቡት መርሆች እውነት ከሆኑ፣ የወጣቶች አገልግሎት በእግዚብሔር ቃል ላይ ጠንካራ አጽንኦት ሊሰጥ ይገባል:: የወጣቶች አገልግሎት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል ስንል መርሐግብሩ ራሱ እንደ አምልኮ፣ ምስክርነት፣ ደቀመዝሙርነት፣ አገልግሎትና ህብረት ባሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች ላይ መገንባት አለበት ማለታችን ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመሠረተው በነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተግባራት ነው:: የትኛውም አዲስ መርሐግብር እነዚህን ተግባራት ሊተካ አይችልም:: እነዚህ

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ የወጠናቸው በመሆናቸው በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ መካተት ይኖባቸዋል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መመሥረት ማለት በተጨማሪም ወጣቶች ቃሉን የማጥናት፣ የመመርመርና ለሕይወታቸው በሚዛመድ መልኩ ለቃሉ ምላሽ የመስጠት ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ነው:: ወጣቶች በስብሰባዎች፣ ካምፖች፣ በሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም በሌሎች ብዙ ተግባራት አማካኝነት የእግዚአብሔርን ቃል እንዲመረምሩ ሊደረግ ይገባል:: ምክንያቱም ቃሉ የወጣቶችንም ሆነ የአዋቂዎችን ሕይወት ለመለወጥ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰለታም ሰይፍ ነውና::

እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መመሥረት ማለት መርሐግብራችን በራሳችን ባሕርይ ላይ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ላይ ይመሠረታል ማለት ነው:: በአንድ የወጣቶች መሪ ተወዳጅነትና/ወይም የተፈጥሮ ችሎታ ላይ የተመሠረተ የወጣቶች አገልግሎት ጽኑና ዘለቄታዊ ሊሆን አይችልም:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ላይ የተመሠረተ መርሐግብር ኢሳይያስ የገለጸውን ዓይነት ፍሬ ያፈራል:: «የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም» (ኢሳ. 55:11)::

በወጣቶች አገልግሎት ስልታችን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ስፍራ ሊኖረው ይገባል:: ምክንያቱም ወጣቶቹ መጽሐፍ ቅዱስን መግዛታቸው ብቻ በቂ አይደለም:: ሊያነቡት ይገባል:: (መጽሐፍ ቅዱስ ለመግዛት ካልቻሉ ወይም ከሌላቸው በቃላቸው ቢያጠኑት መልካም ነው::) ማንበባቸው ብቻ በቂ አይደለም:: መረዳት አለባቸው:: ከዚህም በላይ ሊያምኑትና ሊኖሩት ይገባል!

4. የአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት አራተኛው ዓላማ ለወጣቶች የቤተክርስቲያኒቱን አስተምህሮ ማስተማር ነው:: ቀዳሚው ዓላማችን ወጣቶቻችንን ደቀመዛሙርት ማድረግ ነው:: ከሁሉም በላይ የሚያስፍልገው ይኼ ነው:: ነገር ግን ለወጣቶቻችን የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮ ከማስተማር ወደኋላ ልንል አይገባም:: ወጣቶች ወደ መደበኛ የስብከት ፕሮግራሞች ሲመጡ፣ የማይለዋወጡ የአዋቂ ሞዴሎች ሲኖሯቸውና ወደ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሲመጡ፣ የዚህ ዓይነቱ ትምህርት መደበኛ ባልሆነ መንገድ ይሰጣቸዋል:: ነገር ግን በቀጥተኛ መንገድም የቤተክርስቲያኒቱን አስተምህሮ ማቅረቡ ጠቃሚ ነው::



ዶ/ር ሪቻርድ ቴይለር እንዳሉት፣ «ደህንነትን ሳናገኝ አስተምህሮን ልንቀምር እንችላለን:: ነገር ግን አስተምህሮ ሳይኖር ደህንነትን ልናገኝ አንችልም:: በእምነት ከዳንን አንድ የምናምነው ነገር ሊኖረን ይገባል:: ይህ ደግሞ እውነት መሆን አለበት:: የዳንነው ስሕተትን በማመን አይደለም:: ክርስቶስ እንዳለው፣ በቃሌ ብትኖሩ እውነትን (አስተምህሮውን) ታውቃላችሁ:: እውነትም አርነት (አስተምህሮው የሕይወት ገጠመኝ ይሆናል) ያወጣችኋል::» የወጣቶች መርሐግብራችን ወጣቶች ስለ አስተምህሮ ጠንካራ ጥያቄዎችን እንዲያነሱ የሚጋብዝ ሊሆን ይገባል:: ይህንኑ አስተምህሮ ከተረዱና ጥሪውን ከተቀበሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን እንዲሰጡ በሚጠይቃቸው ጊዜ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁዎች ይሆናሉ:: የወጣቶች አገልግሎት ለዚህ ተገቢ ተግባር የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል::

5. አምስተኛው የአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዓላማ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነው:: ከፍርሃቶቻችን፣ ከቀድሞ ገጠመኞቻችን፣ አመለካከቶቻችን ወይም ከግላዊ የወጣቶች አገልግሎት ፍልስፍናችን ባሻገር፣ የእግዚአብሔር ቃል ዛሬም ሳይለወጥ ይሠራል:: ይህም ቃል ሂዱ! ሂዱና አስተምሩ... ሂዱና ስበኩ... ሂዱና ወደ እኔ እንዲመጡ አድርጓቸው... ሂዱና መስክሩልኝ ይላል:: የወንጌል ስርጭት የዓላማችን ክፍል ነው::

ምንም ያህል ሰው የሚስብ ባሕርይ፣ ምንም ያህል የተሟላ ዕቅድ፣ ወይም ምንም ያህል ብቃትን የተላበሰ መርሐግብር ቢኖረን፣ አብዛኞቹ ወጣቶች በራሳቸው ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን አይመጡም:: እኛ ወደነሱ መሄድ አለብን:: በወንጌል ስርጭት ላይ አጽንኦት የሚሰጥ የወጣቶች መርሐግብር ለማዘጋጀት የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን:: ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በሚከተሉት መንገዶች ነው::
ሀ. መንፈስ ቅዱስ በማህበረሰባችን ላሉት ያልዳኑ ወጣቶች በልባችን ውስጥ ሸክም እንዲሰጠን መፍቀድ (ገላ. 6:2)

ለ. የወጣቶች እንቅስቃሴዎችን ስታቅድ ለወጣቶች ወንጌል ማሰራጨትንም ከግንዛቤ አስገባ (ማቴዎስ 28:19-20)::
ሐ. የቡድንህ ወጣቶች የራሳቸውን ዓለም በወንጌል እንዲደርሱ አሠልጥናቸው (ኤፌሶን 4:11-12):: ለወጣቶች ወንጌሉን ለማድረስ ከወጣት ክርስቲያኖች የተሻሉ አገልጋዮች ሊገኙ አይችሉም:: ጆን ማስልማን እንደሚሉት፣ «የሚያሳዝነው፣ አብያተክርስቲያናት ብዙውን ጊዜ ወጣቶችን የቤተክርስቲያን የወደፊት ተስፋዎች አድርገው መመልከታቸው ነው:: ብዙውን ጊዜ ወጣቶች የጉርምስና ዕድሜያቸውን እስኪጨርሱ ድረስ በወጣቶች መጋቢያንና አዋቂ አገልጋዮች ዕቅዶች ለመመራት ይገደዳሉ:: ይህም ቤተክርስቲያን

ለወጣቶች ገና በለጋነታቸው ተገቢውን አገልግሎት እንዳያበረክቱ አድርጓል።» በአገልግሎታችን የመዝናኛን አስተሳሰብ እንዳንፈጥር መጠንቀቅ አለብን። ወጣቶችን የምናሠለጥንበት ዓላማ እንዲዝናኑ ለማድረግ ሳይሆን፣ ዓለምን በወንጌል በመድረሱ ረገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው።

6. በመጨረሻም፣ አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዓላማ ወጣቶችን ለቤተክርስቲያን አጠቃላይ ተልዕኮ አገልግሎት ብቁ ማድረግ ነው። ቤተክርስቲያን ተልዕኮ ሊኖራት ይገባል። እንዲያውም ሬይኖልድ ኒይቡር እንደሚሉት፣ «እሳት የሚኖረው በመንደዱ ምክንያት እንደሆነ ሁሉ ቤተክርስቲያንም የምትኖረው በተልዕኮዋ ነው።» የኋላ ኋላ አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዓላማ ሁላችን (በተለይም ወጣት አማኞች) የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፣ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ» ነው (ኤፌሶን 4:12-13)።
የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች እንደመሆናችን፣ ሥራችን ወጣቶችን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ነው። በአምልኮ፣ በምስክርነት፣ በደቀመዝሙርነት፣ በአገልግሎትና በህብረት አማካኝነት ወጣቶች አሁንም ሆነ ወደፊት በአገልግሎት ለመሳተፍ የሚያበቃቸውን የሥልጠና ዕድል ልንሰጣቸው እንችላለን። ክርስቶስ የአገልግሎትን አስፈላጊነት በቃሉና በምሳሌነቱ ግልጽ አድርጎልናል። «... *ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን። ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን። እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም*» (ማርቆስ 10:443-45)።

**መስመሩን ይዘህ ተጓዝ!**
አንድ አውሮፕላን አብራሪ ለጉዞ ለመዘጋጀት ወደ ማብረሪያው ክፍል (ኮክፒት) በሚገባበት ጊዜ፣ አንድ በጣም ጠቃሚ ሥርዓት ይፈጽማል። ይህም የራሱና የመንገደኞቹ ህይወት የሚመሠረትበት ወሳኝ ጉዳይ ነው። የአውሮፕላኑ መሣሪያዎች ሁሉ ተገቢ የአሠራር ቅደምተከተላቸውን ይዘው እንደሚገኙ ተራ በተራ ያጣራል። ያንን ተግባር ከፈጸመ በኋላ፣ በሬድዮ መገናኛ አማካኝነት የትራፊክ ተቆጣጣሪው «የኮድ ቁጥር» እንዲሰጠው ይጠይቃል። በመቀጠልም ፓይለቱ የኮድ ቁጥሩን ቪኦአር የጉዞ ሲስተም ከሚባል መሣሪያ ጋር ያገናኘዋል። ከዚህ በኋላ፣ ፓይለቱ የአውሮፕላኑን የቪኦአር ሲስተም ከተሰጠው የኮድ ቁጥር ጋር ማገናኘቱን ከቀጠለ፣ ከምድር ቁጥጥርና ከኦቶፓይሌት (ከአውሮፕላኑ ራሱን በራሱ የማብረሪያ መሣሪያ) በሚመጣለት የሬድዮ መልእክት እየተረዳ በአግባቡ ሥራውን



ሊያከናውን ይችላል። መስመሩን ይዞ ሊዘልቅ ይችላል። ነፋስ አቅጣጫ በመለወጡ ምክንያት እይታው ሊቀንስ ቢችልም፣ ሊፈራ ወይም ግራ ሊጋባ አይችልም። ለዚህም ምክንያቱ የኮድ ቁጥሩ ከፊት ለፊቱ ባለው መሣሪያ ላይ እስኪታየ ድረስ ከተፈለገበት ስፍራ እንደሚደርስ የሚያውቅ መሆኑ ነው።
ባንተም የወጣቶች አገልግሎት መርሐግብር ላይ ነፋስ መንፈሱ የማይቀር ነው። ምናልባት ቀደም ሲልም የነፋስ ወጀብ እያንገላታው ይሆናል። ተስፋ መቁረጥ የሚያይልባቸው አስቸጋሪ ጊዜያት ያጋጥማሉ። ምናልባት አሁን ያለኸው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ እይታህ ውስን ይሆንና ከፊትህ ምን እንዳለ ወይም ወዴት መሄድ እንዳለብህ ማወቅ ይቸግርሃል። ነገር ግን የወጣቶች አገልግሎትህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ የዓላማ መግለጫ ላይ ከመሠረትህ፣ መስመሩን ካልለቀቅህ፣ በዓላማ መግለጫህ ላይ ካተኮርህ ከግብህ እንደምትደርስ እሙን ነው። ፍሬያማ አይደለሁም የሚል ስሜት የሚያድርብህና አገልግሎትህን ለመተው የምትፈተንባቸው ጊዜያት ይኖራሉ። በእንደዚህ ዓይነት ጊዜያት የተጠራህበትን አገልግሎት አስታውስ። ይኸውም የወጣቶች አገልግሎት ነው። መስመርህን ሳትለቅ እንደ ጳውሎስ፣ «*በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ*» በማለት በአገልግሎትህ ትጋ (ፊልጵስዩስ 3:13-14)።

በዋጋ ተገዝታችኋልና
ለራሳችሁ ይደላችሁም።
ስለዚህ በሥጋችሁ
**እግዚአብሔርን**
**አክብሩ** (1ኛ ቆሮ 6:20)

በቃልና በኑሮ፣
በፍቅርም
በእምነትም፣
በንጽሕናም
ለሚያምኑቱ ምሳሌ
ሁን እንጂ ማንም
ታናሽነትህን አይናቀው
(1ኛ ጢሞ 4:12)

በእናንተ ስላለ ተስፋ
ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ
ሁሉ መልስ ለመስጠት
ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ
(1ኛ ጴጥሮስ 3:15)

## ለአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዕቅድ ማውጣት

አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ዓላማ ግልጽ ከሆነልህ በኋላ፣ የተግባር ዕቅድ መንደፍ ይኖርብሃል:: ማቀድ ምን፣ ለምን፣ የት፣ መቼ፣ እንዴትና በማን መደረግ እንዳለበት ከተግባሩ ቀደም ብሎ መወሰን ነው:: ምናልባት ከዚህ የበለጠ ሙያዊ (ቴክኒካል) የዕቅድ ገለጻ ትፈልግ ይሆናል:: ሮበርት ቦወር እንደሚሉት፣ ዕቅድ «ለአሁንም ሆነ ለወደፊት ስኬታማ ውጤት ለማግኘት ተብሎ የሚካሄድ የበፊትና የአሁን ተግባራት የምርመራ ሂደት ነው::»

አንድ ጊዜ አንድ ትንሽ ልጅ አባቱን፣ «ምን ያህል አርቀህ ማየት ትችላለህ፣ አባባ?» ሲል ጠየቀው::

«እኔ እንጃ የኔ ልጅ... 20 ማይሎች፣ ምናልባትም ደመና የሌለ ቀን 40 ማይሎች አይ ይሆናል:: አንተስ ምን ያህል ታያለህ?»

«እኔ ከዚያ ብዙ አርቄ ማየት እችላለሁ:: ከዋክብትን እጥርቼ ማየት እችላለሁ!»

ዕቅድ በቀጥታ ከፊታችን ያለውን ብቻ ሳይሆን፣ ከጊዜ ኮረብታ ባሻገር ወደ ረዥሙ ዓላማችን እንድንመለከት ይረዳናል:: ዕቅድ እግዚአብሔር በሕይወታችንና በምናገለግላቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ምን ሊሠራ እንደሚችል የምንመለከትበት ዕድል ነው::

### የዕቅድ አስፈላጊነት

ለወጣቶች አገልግሎት ጥረቶችህ መሳካት ዕቅድ በጣም አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው:: ያለ ዕቅድ ለወጣቶች አገልግሎት የነደፍሃቸው ዓላማዎችና ግቦች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም:: የበቂ ዕቅድ ጉድለት ብዙውን ጊዜ መርሐግብሮችና እንቅስቃሴዎች ባልተደራጀ መልኩ እንዲካሄዱ ያደርጋል:: በዕቅድ ጉድለት ሳቢያ የእግዚአብሔር ሀብቶች፣ የኛ ጊዜ፣ ችሎታችንና ንብረቶች አንዳንድ ጊዜ በአግባቡ ሳይያዙ ይቀራሉ... አንዳንዴም ይባክናሉ:: በአግባቡ ለማቀድ አለመቻል እግዚአብሔር የሰጠንን አገልግሎት በሚገባ ለማስተዳደር አለመብቃት ነው:: ስለሆነም፣ ዕቅድ ለፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት ወሳኝ ነው::

### በዕቅድ ላይ የሚቀርብ ተቃውሞ

ምንም እንኳዋን ብዙውን ጊዜ ለወጣቶች አገልግሎት ማቀድ የሚያስገኘውን ጥቅም ብንገነዘብም፣ ግማሹ ልባችን ዕቅድን ሊቃወም ይችላል:: እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎች ሳያቅዱ ተግባራቸውን በአግባቡ ሊያከናውኑ ይችላሉ:: ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ብቃት ያላቸው ሰዎች ብዙ አይደሉም:: ሌሎች ደግሞ የዕቅድን አስፈላጊነት ቢገነዘቡም፣ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ እርምጃ ላይ እየመራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ተግባራቸውን ለማከናወን ስለሚፈልጉ በረዥሙ ከማቀድ ይቆጠባሉ:: የዚህ ዓይነቱ መሪነት ለአንዳንድ ሰዎች እንደሚሠራ እንረዳለን::



ለብዙዎቻችን ግን ዕቅድ ጠቃሚና እጅግ አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም፣ በዕቅድ ላይ የሚቀርበውን ተቃውሞ ለመከላከል ማሰቡ ሳይበጅ አይቀርም::

1. በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ማቀድ እንደሚቻል ተገንዘብ:: መንፈስ ቅዱስ የሚመራው በግብታዊነት ወይም ባለቀ ሰዓት ላይ ብቻ እንደሆነ ማሰቡ ችሎታውን ይገድበዋል:: መንፈስ ቅዱስ ባለቀ ሰዓት ላይ የሚያደርገውን ያህል (ምናልባትም ከዚያ የበለጠ) የረዥም ጊዜ ዕቅድህን ሊያነሣሣው ይችላል::
2. እግዚአብሔር ወደርየለሽ ዕቅድ አውጭ እንደሆነ ተገንዘብ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተመረጠው ዓለም ሳይፈጠር በፊት ሲሆን፣ በመጨረሻው ዘመን ተገልጧል (1ኛ ጴጥሮስ 1:20):: የክርስቶስ በትስብእት መገለጥ መጨረሻ ላይ ብቅ ያለ አሳብ አልነበረም! እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደህንነት የረዥም ጊዜ ዕቅድ ነበረው!
3. ዕቅድ ፈጠራን እንደማያዳክምና እንዲያውም በብዙ ሁኔታዎች እንደሚያሳድግ ተገንዘብ:: ዕቅድ ፈጠራ ለዲስፕሊን እንዲገዛ ያደርገዋል:: በዲስፕሊን የተገራ ፈጠራ ደግሞ ለፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት ወሳኝ ነው::

### ለማቀድ ማቀድ?

በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከሚካሄድ ዕቅድ ተጠቃሚ ከሚሆኑ ከአብዛኞቹ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች አንዱ ከሆንህ፣ ምናልባትም ለማቀድ ዐቅደህ ይሆናል:: ለአገልግሎትህ ዕቅድ ለማውጣት ምን እንደምታደርግ ዐቅደሃል? (ይሄ የቃላት ድግግሞሽ ትንሽ ግርታ ሊፈጥርብህ ይችላል!) መልስህ አላቀድሁም የሚል ከሆነ፣ በድርጅታዊ ስልት ላይ ውሳኔ ብትሰጥ መልካም ነው:: የዚህ ክፍል ቀጣይ ክፍሎች ይህንኑ፣ ማለትም ለአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት እንዴት እንደምታቅድ የሚያስረዱ ስለሆነ በሚገባ አንብባቸው:: በዚህም ጊዜ ለእግዚአብሔር እንደምናደርጋቸው ሌሎች ነገሮች ሁሉ ዕቅድ ጥልቅ መንፈሳዊ ልምምድ ሊሆን እንደሚችል ትገነዘባለህ::

## አጠቃላይ የወጣቶችን አገልግሎት መምራት

አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው መሪዎቹ ፍሬያማ የሆኑ እንደሆን ብቻ ነው:: እንደ ሌሎች አገልግሎቶች ሁሉ፣ የቤተክርስቲያን የወጣቶች መርሐግብርም በማያቋርጥ፣ የተሰጠ መንፈሳዊ አመራር ላይ የሚመሠረት ነው::

ለአጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት የሚያስፈልጉ ብቃቶች

ለፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የግል ባሕርያት ምንድናቸው? ጥሩ የወጣቶች አገልግሎት መሪ የሚከተሉት ብቃቶች ሊኖሩት እንደሚገባ ከቃሉና ከልምምዳችን ለመረዳት እንችላለን::

1. *ከእግዚአብሔር ጋር ሕይወት ያለውና እያደገ የሚሄድ ግንኙነት ያለው::* በዚህ ረገድ የወጣቶች አገልግሎት ከቀድሞው የበለጠ ውስብስብና ብዙ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም:: ቀጣይ የቤተክርስቲያን ትውልድ የሆኑትን ወጣቶች ለቤተክርስቲያን አመራር መቅረጽ... የበሰጠ በሳል ክርስቲያን ይሆኑ ዘንድ ደቀመዝሙር ማድረግና... ለሕይወት ዘመን አገልግሎት ማስታጠቅ... ከፍተኛ ውጤት ያለውና ከባድ ሃላፊነት ነው:: ለአብያተክርስቲያኖቻችን መንፈሳዊ የሆነ የወጣቶች አመራር እጅግ አስፈላጊ ነው:: መሪዎቻችን ደህንነትን ያገኙና ከእግዚአብሔር ጋር እያደገ የሚሄድ ግንኙነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል:: የትኛውም ዓይነት ችሎታ ወይም የግል ጠባይ ይህንኑ ምትክ የሌለው ባሕርይ ሊተካ አይችልም:: ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ሕይወት ያለውና እያደገ የሚሄድ ግንኙነት ለወጣቶች አገልግሎት ጥረቶችህ ጽናትንና ሥልጣንን ይሰጠዋል:: ከዚህ ውጭ፣ የወጣቶች አገልግሎት ግልብና ፍሬ-አልባ ይሆናል:: ከጥሩ መርሐግብሮችና ብዙ የወጣቶች አገልግሎት ባጀቶች በላይ የሚያስፈልጉን እግዚአብሔርን የሚወዱ፣ ምሪቱን የሚከተሉ፣ በጸጋና ክርስቶስን በመምሰል የሚያድጉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የወጣቶችመሪዎች ናቸው (ኤፌሶን 4:14-15)::
2. *ወጣቶችን ከልቡ የሚወድ::* ፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት በመልክዓ ምድራዊ አካባቢ፣ መደበኛ ትምህርት ወይም በዕድሜ የተገደበ አይደለም:: ትንሽ ወይም ምንም መደበኛ ትምህርት የሌላቸው ሰዎች ብዙ ፍሬያማ የወጣቶች መርሐግብሮችን በማካሄድ ላይ ናቸው:: ዕድሜም ቢሆን ለወጣቶች አገልግሎት እንቅፋት አይደለም:: ነገር ግን አብዛኞቹ ውጤታማ የወጣቶች መሪዎች ይህንን ባሕርይ ይጋራሉ:: ይኸውም ለወጣቶች ሸክም... ርህራሄና... ፍቅር ያላቸው መሆናቸው ነው:: ያለዚህ አንድ የወጣቶች አገልግሎት መሪ ምንም ያህል ተፈጥሯዊ ስጦታዎች እና/ወይም ችሎታዎች ቢኖሩትም፣ ፍሬያማ አገልግሎት ለማበርከት መቸገሩ የማይቀር ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 13:1):: በመርሐግብር ዝርዝር ጉዳዮች ከመጠመድ ይልቅ ለወጣቶችና ለሚያሳስቧቸው ነገሮች ከልብ የመነጨ እንክብካቤ ማድረጉ የበለጠ አስፈላጊ ነው:: አብዛኞቹ ወጣቶች አንድ መሪ ከወጠናቸው መርሐግብሮች በላይ ትኩረት የሚሰጡት በሚያደርግላቸው አቀባበል ላይ ነው:: ከምንም ነገር በላይ፣ ወጣቶቻችን ፍቅርንና ተቀባይነትን ይፈልጋሉ:: ለዚህም የወጣቶች መሪ እንደመሆንህ፣ ብቸኛው የፍቅርና የተቀባይነት ምንጫቸው አንተው ልትሆን ትችላለህ::

ወጣቶችን ከመውደድ በተጨማሪ፣ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች አብረዋቸው ለመሆኑ ደስተኞች ሊሆኑ ይገባል:: አንድ ሰው ከልቡ ወጣቶችን እንደሚወድ ሊናገርና አብሯቸው ለመሆን ላይፈልግ ይችላል:: ወጣቶች መሪዎቹ በርግጥ አብረዋቸው ለመሆን መፈለጋቸውንና ከልባቸው ሳይፈልጉ በትዕግሥት እያስተናገዷቸው መሆኑን ለይተው ያውቃሉ::

3. *ለወጣቶች ምሳሌ ለመሆን የሚፈቅድ::* ለእግዚአብሔር መንግሥት ከተከናወኑት ተግባራት አብዛኛው ከመማር የተገኘ ሳይሆን ከሰዎች ምሳሌነት የተወሰደ ነው:: የወጣቶች መሪ ወጣቶች በምሳሌነት ሊከተሉ የሚችሉት ዓይነት ሰው መሆን ይኖርበታል:: ወጣቶች ከመሪዎቻቸው ሕይወት ለመመልከት የሚፈልጓቸውና ምላሽ ለመስጠት የሚነግሡባቸው ብቃቶች የሚከተሉት ናቸው... ሳይቋረጥ የሚቀጥል የተቀደሰ ሕይወት... የክርስቶስን የሚመስሉ አመለካከቶች... ክርስቲያናዊ የአኗኗር ስልት... ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች በጻፈበት ወቅት ይህንኑ የአገልግሎቱን ገጽታ ተገንዝቦ ነበር:: «ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ» (ፊልጵስዩስ 4:9)
4. *ጉጉትና የጋለ ስሜት ያለው::* ይህ በሰዎች ሕይወት ውስጥ መኖሩ ወይም አለመኖሩ በግልጽ የሚታወቅ ባሕርይ ነው:: ጉጉ የወጣቶች አገልግሎት መሪ በሚያከናውነው ተግባር የሚያምንና ይህንንም በአያሌ መንገዶች የሚያሳውቅ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ ስለ ራሱ፣ ስለ ቤተክርስቲያኑ፣ ስለ አምላኩ፣ ስለ አገልግሎቱና እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ ስላኖራቸው ሰዎች አዎንታዊ አመለካከት ያለው ነው:: ወጣቶች ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎች አካባቢ መሆን ያስደስታቸዋል:: ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎች እውነተኛ የሆነውን፣ ጭምትነት ያለበትን፣ ጽድቅ የሆነውን፣ ንጹሕ የሆነውን፣ ፍቅር ያለበትን፣ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን፣ ምስጋናም ቢሆን፣ እነዚህን እንዲያስቡ አሳስቧቸዋል (ፊልጵስዩስ 4:8):: የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች

እንደመሆናችን፣ አገልግሎታችንን በእምንታዊ ነገሮች ላይ መገንባት ይኖርብናል።

5. ወጣቶች የሚደገፉበት ዓይነት ሰው። ታላላቅ ነገሮችን ለመፈጸም ቃል እየገባ ተግባራዊ ከማያደርግ የወጣቶች አገልግሎት መሪ የበለጠ ወጣቶችን የሚያሳዝንና የወጣቶችን መርሐግብር በፍጥነት የሚያበላሽ ምንም ነገር የለም። የወጣቶች አገልግሎት መሪ ለተደጋፊነት፣ ለቀጥተኛነት፣ ለታማኝነትና ወጣቶቹ በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ ለመገኘት ትልቅ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። አንድ ወጣት መሪው እሱና ሌሎችም ወጣቶች የቡድኑን ዕቅዶች ተከትለው እንዲዘልቁ ለማድረግ የቆረጠ መሆኑን በሚገነዘብበት ጊዜ፣ መሪው የወጣቶቹን አመኔታና አክብሮት ለማግኘት ብዙ እንደጣረ መረዳት ይቻላል። መሪው የቡድኑን አመኔታ ካገኘ፣ በሕይወታቸው ላይ እውነተኛ ተጽዕኖ ለማሳደር ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው።
ጳውሎስ ለገላትያ አማኞች እንደጻፈላቸው፣ ከሌሎች ነገሮች (እንደ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ በጎነት፣ ቸርነትና ራስን መግዛት) በተጨማሪ፣ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ በሚያድርበት ጊዜ ታማኝነትን እንደሚያፈራ አስረድቷል (ገላትያ 5:22)። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የወጣቶች አገልግሎት መሪ የቃሉን ያህል መልካም ተግባር የሚፈጽም ነው።

6. የሚጸልይ። የወጣቶች አገልግሎት ብዙ ጥረቶችን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል። የወጣቶች አገልግሎት ብርታትን፣ ትዕግሥትን፣ መልካም አስተሳሰብን፣ ጥበብንና ዘዴን ይጠይቃል። ነገር ግን በተፈጥሮ እነዚህን ስጦታዎች አሟልተው የተገኙ ብዙ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች የሉም። ነገር ግን በጸሎትና እግዚአብሔርን በመተማመን እነዚህን ነገሮች ማግኘት ይቻላል። ስለሆነም፣ ፍሬያማ የወጣቶች አገልግሎት መሪ የሚከተሉትን ነገሮች ያደርጋል።
ሀ. እግዚአብሔር ብርታትን እንዲሰጠው ከመጸለዩም በላይ፣ ለሚያገለግላቸው ወጣቶች እውነተኛ መንፈሳዊ አመራር ለመስጠት ቁርጥ ውሳኔ ያደርጋል።
ለ. ተስፋ መቁረጥ በሚያይልበት ጊዜ ሳይቀር አገልግሎቱን እስከመጨረሻው ለማካሄድ የሚችልበትን ትዕግሥት እግዚአብሔር እንዲሰጠው ይጸልያል።
ሐ. አስቸጋሪ ውሳኔዎችንና ወሳኝ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር አስተዋይነትን እንዲሰጠው ይጸልያል።
መ. በመልካም የግንዛቤ ልክ ተግባሩን ለማከናወን የሚችልበትን ጥበብ እግዚአብሔር እንዲሰጠው ይጸልያል።



ሠ. ውስብስብ ሁኔታዎችንና ከአገልግሎቱ ጋር የሚመጡትን ብዙ ነገሮች የሚጠይቁ ሰዎች ማስተናገድ የሚችልበትን ዘዴ ከእግዚአብሔር በጸሎት ይጠይቃል።
ያዕቆብ በመልእክቱ ውስጥ በዓለም ሁሉ ለሚገኙ አማኞቹ ግሩም የተስፋ ቃል ሰጥቷል። «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን። ለእርሱም ይሰጠዋል» (ያዕቆብ 1:5)።

*መሪዎችን መመልመል*

ለአጥቢያ ቤተክርስቲያንህ፣ ለዞን ወይም ለቀጠና አመራር እንድትሰጥ ተጠርተህ ከሆነ፣ አንድን ነገር ለራስህ አምነህ ልትቀበል ይገባሃል። ይኸውም ምንም ያህል ችሎታ፣ ጊዜና ጉልበት ቢኖርህም፣ ሁሉንም ነገር ብቻህን ልትወጣው እንደማትችል ነው። ርዳታ ያስፈልግሃል። ደግሞስ ሌሎች ፈቃደኛና ብቃት ያላቸው ሰዎች እያሉ ለምን ብቻህን ትሠራለህ? አንዳንድ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች የቡድን ሥራን ጠቀሜታ ሳያውቁ ብቻቸውን ብዙ በመሥራታቸው ምክንያት ዝለው ይታያሉ። ውጤታማ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች አገልግሎታቸውን ለሌሎች ማካፈሉ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባሉ። ይህን በማድረጋቸውም ማንኛውም አንድ ግለሰብ ሊደርስ የማይችላቸውን ብዙ ወጣቶች ያገለግላሉ። አገልግሎታቸውም በዚህ መልኩ እየተባዛ ይሄዳል። አንተም ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አንዳንድ ረዳቶችን ለወጣቶች አገልግሎት ልትመለምል ትችላለህ። ለዚህም የሚያስፈልጉህ አንዳንድ መመሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበውልሃል።

1. የምትፈልጋቸውን አገዛዎች መርምር። የአመራር እገዛ የምትፈልግባቸውን አገልግሎቶች ዘርዝር። ዝርዝሩ ይህንን ሊመስል ይችላል። የትራንስፖርቴሽን አስተባባሪ፣ የማስታወቂያ አስተባባሪ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስተባባሪ፣ ከቤተክርስቲያን መልስ የወጣቶችን እንቅስቃሴዎች ስፖንሰር የሚያደርጉ አራት ባለትዳሮች፣ የካምፕ ስፖንሰሮች ሆነው የሚሠሩ ሦስት አዋቂዎች፣ የወጣቶች የመዘምራን ዳይሬክተር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ አዘጋጅ፣ የሚሲዮን ትምህርት ዳይሬክተር።
2. ጸልይ። እግዚአብሔር ራሱ ወዳዘጋጃቸው መሪዎች እንዲመራህ ጸልይ።
3. ቀደም ሲል የተገለጹትን የወጣቶች አገልግሎት ብቃቶች ከልስ። እንዲያውም ሰዎችን በምትገመግምበት ጊዜ እነዚህን ስድስት ብቃቶች ከስማቸው አጠገብ ልትዘረዝር ትችላለህ።
ሀ. ለወጣቶች አገልግሎት ችሎታ እንዳላቸው የሚያስቡትን ሰዎች ስሞች ጻፍ። ስለ ሰዎች ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ወይም

ልምድ የተወሰነ አስተሳሰብ ይዘህ አመለካከትህን አታዛባ። እነዚህ ለምርጫ የመጨረሻ መመዘኛዎች አለመሆናቸውን ተገንዘብ።

*ለ. ዝርዝሩ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ብቃታቸውን መርምር።*

*ሐ. ያንተን የማጣሪያ ምርመራ ካለፉ በኋላ፣ የምልምሎቹን የስም ዝርዝር ወደ መጋቢህ፣ ተባባሪ መጋቢህ፣ ወይም በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ለወጣቶች አገልግሎት ሃላፊነት ላለበት ሌላ መሪ ውሰድ።* ስለ ምልምሎቹ በግል ከነዚህ አገልጋዮች ጋር ተነጋገር። እጩዎቹ ለሥራው ብቁ ወይም በአገልግሎቱ ላይ የሚገኙ ስለመሆናቸው እነዚህ አገልጋዮች የራሳቸውን አሳብ ሊሰጡ ይችላሉ። ሁልጊዜም ወደ እጩው የወጣቶች አገልጋይ ሄደህ ከማነጋገርህ በፊት ሪፖርት ከምታደርግለት አገልጋይ ጋር መነጋገሩ መልካም ነው።

*መ. ብቃት እንዳላቸው የታመነባቸውን ሰዎች ሁሉ ሄደህ አነጋግር።* እያንዳንዱን እጩ ለብቻ ማነጋገሩ የተሻለ ይሆናል። በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ ለማገልገል ብቁዎች መሆናቸውን የምታምንባቸውን ዝርዝር ምክንያቶች በመስጠት አሳብህን በግልጽ ንገራቸው። ምን በማድረግ እንዲያገለግሉ እንደምትፈልግ (የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪ፣ የእንቅስቃሴዎች ስፖንሰር፣ የትራንስፖርት አስተባባሪ፣ ወዘተ.) በመግለጽ፣ በጽሑፍ የሰፈረ የሥራ ድርሻ ዝርዝር ስጣቸው። የሥራ ድርሻ ዝርዝሩ ከአገልጋዮቹ ምን እንደሚጠበቅና የብቃት መስኪያ መስፈርቶቹን በአስተዋጽኦ መልክ የሚያብራራ መሆን አለበት። ካንተና ከሌሎችም እጩ አገልጋዮች ጋር ለአጭር ውይይት እንዲሰባሰቡ ጠይቃቸው። ለወጣቶች አገልግሎት ያለህን ራእይና ሸክም አካፍላቸው። አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት በጥንቃቄ እንዲጸልዩበት አበረታታቸው።

*4. መልሳቸውን መቼ ሊነግሩህ እንደሚገባ አስታውቃቸው።*

*5. ምላሻቸው አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ በግንዛቤ ደግፈው።* ለወጣቶች መርሐግብርህ ሠራተኞችን ለመመልመል የምትጠቀምበት እንከን የለሽ መንገድ ሊኖር አይችልም። ምርጫህ ጥሩ ይሁን መጥፎ የሚረጋገጠው በጊዜ ሂደት ነው። ይሁንና፣ ከላይ የተጠቀሱትን የምልመላ ነጥቦች መጠቀም የስኬት ዕድልህን ያሰፋዋል።

**ለወጣቶች አገልግሎት መሪዎችን ማሳደግ**

የወጣቶችን የአገልግሎት ቡድን ከመለመልህ በኋላ ምን ታደርጋለህ? መቼም የሥራ ድርሻ ዝርዝር ከሰጠሃቸው በኋላ በአዲስ ሃላፊነቶቻቸው መልካም ዕድል እንዲገጥማቸው ተመኝተህ ዝም አትልም። ችሎታዎቻቸውን ለአገልግሎት ማሳደግ ይኖርብሃል። ቀላልና እጥር ምጥን ያለ የመሪዎች እድገት ስልት ከዚህ በታች ቀርቦልሃል።

1. *ከመሪዎቹ ጋር አብረህ አሳልፍ።* አነስተኛ የወጣቶች አገልግሎቶች ቡድን ካለህ፣ ከእያንዳንዱ መሪ ጋር በቂ ጊዜ ማሳለፍህን እንደ



መታደል ቁጠረው። ዓላማህም ከአገልግሎቱ ተግባራት ውስጥም ሆነ ውጭ ከቡድኑ አባላት ጋር ጠንካራ ግንኙነቶችን መመሥረት ነው። ለግላዊ ፍላጎቶቻቸው እንደሚገድህ እንዲገነዘቡ አድርግ። እነዚያ ፍላጎቶቻቸውን ለአንተ እንዲያካፍሉህ አበረታታቸው። ይህንን በማድረግ ለአገልግሎት የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ ስለምታግዛቸውና በተዘዋዋሪ መንገድ የራስህን አገልግሎት ፍሬያማ ስለምታደርግ፣ ይህ በመልካም ተግባር ላይ የዋለ ጊዜ መሆኑን ተገንዘብ። ሰፊ የወጣቶች አገልግሎት ቡድን ካለህ፣ ከቁልፍ የቡድንህ አባላት ጋር በቂ ጊዜ አሳልፍ። እነዚህም በተለይ ለአንተ የሚቀርቡና በቀጥታ ሪፖርት የሚያደርጉልህ ናቸው።

2. *የወጣት ሠራተኞችን የምክር ስብሰባዎች የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅ።* የወጣቶች አገልግሎት ቡድን የግድ መደበኛ ስብሰባ ማድረግ አለበት። እንዲህ ዓይነት ስብሰባዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማካተት ይኖርባቸዋል።

*ሀ.* ስብሰባዎቹ ስለ አገልጋዮችም ሆነ ስለ ወጣቶች *የምልጃ ጸሎት* የሚቀርብባቸው ጊዜያት መሆን ይኖርባቸዋል። ውጤታማ የወጣቶች አገልግሎት ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ላይ ጤናማ ጥገኝነት የሚታይበት ነው። አገልጋዮቹ ይህንኑ ለማድረግ ተነሳሽነትን የሚያገኙት ካንተ ይሆናል።

*ለ. አስተውሎት/ግንዛቤ።* የወጣቶችን አገልግሎት በሚያካሂዱበት ጊዜ የተማሩትን ትምህርትና ያገኙትን ግንዛቤ ለሌሎች ማካፈሉ በቡድን ስብሰባ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል። እነዚህ የልምድ መለዋወጫ ጊዜያት ለቡድኑ አንድነትንና የተልዕኮን ስሜት ለማምጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

*ሐ ግምገማ።* ቀደም ሲል የተካሄዱትን የወጣቶች እንቅስቃሴዎችና መርሐግብሮች *መገምገም* ሊያስፈራህ አይገባም። እያንዳንዱን ክስተት እያነሣችሁ መጀመሪያ ስለ ጠንካራ ጎኑ፣ ከዚያም መሻሻል ስለሚያስፈልጋቸው አቅጣጫዎች ተወያዩ። ዓላማዎችህንና ግቦችህን ለቡድኑ ግለጽ። ለዚህ የወጣቶች አገልግሎት የወጠንናቸውን ዓላማዎች እያሳካን ነው? እያልህ አለማቋረጥ ጠይቅ። መለወጥ ያለበት ምንድነው? መጨመር ያለበትስ?

*መ. መረጃ።* ስለ ወጣቶች አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ለማካፈል ከአጀንዳው የተወሰነ ጊዜ መመደብ ያስፈልጋል። እንዲህ ዓይነት ስብሰባዎች ስለ ወጣቶች ዝንባሌዎች፣ ብሎም ስለ አዳዲስ የወጣቶች መርሐግብር ማቴሪያሎችና መሣሪያዎች ለመወያየት መልካም ጊዜያት ናቸው።

*ሠ. ማቀድ።* ወደፊት ስለሚካሄዱት ክስተቶች በማሰብ ሥራዎችን መመደብ፣ ለትራንስፖርትና ማስታወቂያ አስፈላጊውን እርምጃ

መውሰድ ይኖርብሃል። በቡድኑ ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ ሰው ሥራ መስጠቱንና ግለሰቡም ስለ ተሰጠው ሥራ በቂ ግንዛቤ ማግኘቱን አረጋግጥ።

*3. የቡድንህ አባላት ግለሰባዊና የአመራር አገልግሎታቸውን* የሚያሳድጉበትን አካባቢ ፍጠር። የራስህን የወጣቶች አገልግሎት ችሎታ በአንዲት ጀንበር እንዳላሳደግህ ግልጽ ነው። አንድ ሰው በትዕግሥትና ዱሩ ግን በጥብቅ ወደዚህ የአገልግሎት ብቃት እንደመራህ አይጠረጠርም። በተመሳሳይ መልኩ፣ አንተም መሪዎችህ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሃላፊነት ተጥሎብሃል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰዱ ጠቃሚ ነው።

ሀ. በሚወድቁበት ጊዜ ደግፋቸው። አርኖልድ ግላሶው በትክክል እንደተናገሩት፣ «ጥሩ መሪ ከድርሻ የበለጠ ወቀሳና ከድርሻው ያነሰ ምስጋና ይቀበላል።» መሪዎችህ ውድቀታቸውን ለበለጠ ውጤታማነት እንዲጠቀሙ አግዛቸው።

ለ. ስኬታቸውን በአዎንታዊ መልኩ እየደገፍህ ደጋግመህ አበረታታቸው። አዎንታዊ ድጋፍ ወደ መልካም አቅጣጫ እንድንሄድ ያነሣሣናል... ይህም ሰዎች የምንፈልገውን እንዲያደርጉልን በሆን ብልሃት ከመጠቀም... ከማስፈራሪያ ዘዴዎች፣ ወይም የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማቸው ከማድረግ የበለጠ ሀይል ያለው ነው። እንዲያውም አዎንታዊ ድጋፍ የፊልሞና መልእክት ቀዳማይ መልእክት ይመስላል። *«በጌታ በኢየሱስ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ ዘንድ ስላለህ ስለ ፍቅርህና ስለ እምነትህም ሰምቼ፣ በጸሎቴ እያሳሰብሁ ሁልጊዜ አምላኬን አመሰግናለሁ... የቅዱሳን ልብ በአንተ ሥራ ስለ ዐረፈ፣ ወንድሜ ሆይ፣ በፍቅርህ ብዙ ደስታንና መጽናናትን አግኝቼአለሁና»* (ቁ. 4-5፣ 7)። ፊልሞን ከመሪው ከጳውሎስ እንዲህ ዓይነት የአዎንታዊ ድጋፍ መግለጫ በሚያገኝበት ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማው ትገነዘባለህ? ማበረታቻና አዎንታዊ ድጋፍ ከእውነተኛ ልብ በአክብሮት በሚፈልቁበት ጊዜ መሪዎችህ የሚያድጉበትን መልካም አካባቢ ይፈጥራሉ።

ሐ. የውሳኔ ሰጭነት ሂደት አካል አድርጋቸው። ጆን ናይስቢት "Megatrends" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንደገለጹት፣ «ውሳኔው የሚነካቸው ሰዎች ሁሉ በውሳኔ ሰጭነቱ ላይ መካፈል አለባቸው።» የውሳኔ ሰጭነቱ ሂደት አካል ተደርገው ካልተወሰዱ ውሳኔው «የራሳቸው» እንደሆነ አይሰማቸውም። ይህ ደግሞ ውሳኔውን ከልባቸው እንዳይደግፉት ያደርጋል። ስለሆነም፣ የቡድንህን አባላት ሆን ብለህ በውሳኔ ሰጭነት ሂደት ውስጥ ብታሳትፍ በመሪነት የሚያድጉበትን አካባቢ ትፈጥርላቸዋል።



# አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት መርሐግብር ማዘጋጀት

አሁን አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት ክፍሎች ስፍራ ስፍራቸውን እየያዙ እንደሆን ተስፋ እናደርጋለን። አንዳንድ ዓላማዎችንና ግቦችን አዘጋጅተሃል... አደረጃጀቱም መልክ እየያዘ ነው... የወጣቶች አገልግሎት አመራር አባላት ተመርጠው ለሥራ ተዘጋጅተዋል... ከዚህ ቀጥሎ ምን ታደርጋለህ? ይህ መነሣት ያለበት ትክክለኛ ጥያቄ ነው። ለመጀመር እና/ወይም ለመቀጠል ስለምትፈልጋቸው የወጣቶች መርሐግብሮች ለማሰብ ጊዜው አሁን ነው። መርሐግብር (ፕሮግራም) የወጣቶች አገልግሎት ስልት ተግባራዊ ተዛምዶ ነው። የምትጀምራቸውን መርሐግብሮች ከጠቅላላው የዕቅድ ሂደት በመነሣት ተግባራዊ ለማድረግ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ያሳያሉ።

**ምን መርሐግብሮች?**

አሁን የተጋፈጠብህ ትልቁ ጥያቄ ምናልባትም: በዚህ ጊዜ ምን የወጣቶችን መርሐግብሮች መጀመር እንዳለብን ይሆናል። ውጤት ሊያመጡ የሚችሉት የትኞቹ የወጣቶች መርሐግብሮች ናቸው? የሚያስፈልገን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር ነው? የወጣቶች ካምፕ ማዘጋጀት የቡድኑን ፍላጎቶች ያሟላ ይሆን? የወንጌል ስርጭት ጉዞ ወይም የአገልግሎት ፕሮጀክት ለቡድናችን ይጠቅም ይሆን? ይሆን ይሆናል... ላይሆንም ይችላል! ለማዕከላዊቷ ቤተክርስቲያን የሚሠራ መርሐግብር ለወጣቶች ቡድንህ ላይሠራ ይችላል። ከሦስት ዓመታት በፊት ለወጣቶች ቡድንህ የሠራ መርሐግብር አሁን ላይሠራ ይችላል። ለዚህም ነው ለወጣቶች መርሐግብር የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የሚኖርብህ።

1. *የወጣቶች አገልግሎት የረዥምና የአጭር ጊዜ ዓላማዎችህንና ግቦችህን እንደገና አጢናቸው።* መርሐግብሮችን ለማዘጋጀት በምታስብበት ጊዜ፣ ለወደፊቱ ዓላማዎቻችንንና ግቦቻችንን ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱን መርሐግብሮች የትኞቹ ናቸው? ብለህ ጠይቅ። ሁሉንም የወጣቶች መርሐግብር ለመምረጥ፣ ለመጀመርና ለመቀጠል ይህ መሪ መርህ ሊሆንህ ይገባል። ስለምታስባቸው መርሐግብሮች ከመጋቢህ ጋር ተነጋገር። ይህንንም የምታደርገው መርሐግብሮቹ መጋቢው ለቤተክርስቲያን ከወጠናቸው አጠቃላይ ግቦች ጋር እንደሚጣጣሙና እንደማይጎረብጡት በማረጋገጥ ነው። ምክንያቱም መርሐግብርህ ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ

የመጋቢውንና ሌሎች የቤተክርስቲያን ቁልፍ መሪዎችን ድጋፍ ማግኘት ስላለብህ፣ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው።

2. *ቡድንህ ምን እንደሚያስፈልገው መርምር።* በወጣቶች አገልግሎት መሪነት የተወሰነ ጊዜ ከቆየህ፣ የወጣቶችን ባህርይና ፍላጎቶች ለይተህ ታውቃለህ። ለቤተክርስቲያኒቱ ወይም ለማህበረሰቡ አዲስ ከሆንህ፣ ከቀደሙት የወጣቶች አገልጋዮች፣ ሌሎች የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች፣ የወጣቶች ወላጆችና ከአንዳንድ ወጣቶች ጋር ተገናኝተህ ተነጋገር። ከራሳቸው እይታ አንጻር ቡድኑ ምን እንደሚያስፈልገው ጠይቃቸው። የቡድኑ የብስለት ደረጃ የት ላይ ነው? ዕድሜያቸውስ? መንፈሳዊ፣ ሥጋዊና ስሜታዊ ፍላጎቶቻቸው ምን ምንድናቸው? ከዚያም እግዚአብሔር የወጣቶቹን ፍላጎቶች ለይተህ እንድታውቅ እንዲረዳህ ጸልይ። ፍላጎቶቻቸውን ለይተህ ማውጣት እንደጀመርህ ስትገነዘብ፣ እነዚያን ፍላጎቶች ሊያሟሉ የሚችሉትን መርሐግብሮች ማዘጋጀት ጀምር።

3. *የቡድንህን አባላት ብዛት ከግንዛቤ ውስጥ አስገባ።* አንዳንድ አብያተክርስቲያናት ብዙ አባላት የሚገኙባቸው የወጣቶች ቡድኖች ስላሏቸው ሰፊ የወጣቶችን መርሐግብሮች መዘርጋት ይችላሉ። ያም መልካም ነው! አብዛኞቹ አብያተክርስቲያናት ግን አነስተኛ የወጣቶች ቡድኖች አሏቸው። ያም መልካም ነው። የአባላት ቁጥር ብቻውን ፍሬያማ የወጣቶች ቡድን አይመሠርትምና። አነስተኛ የወጣቶች ቡድኖች የታላላቅ አብያተክርስቲያናትን ያህል ብዙ የወጣቶች መርሐግብሮችን ሊያካሂዱ እንደማይችሉና ይህንኑ ማድረግም የግድ እንደማያስፈልጋቸው መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። አንዳንድ መርሐግብሮችን ይኑሩን በሚል አሳብ ብቻ መንደፉ ጥቅም የለውም። አማካይ መጠን ያለው የወጣቶች ቡድን መሪ እንደመሆንህ፣ ያንተ ድርሻ ጥቂት መርሐግብሮችን መርጦ በጥሩ ሁኔታ ማካሄድ ይሆናል። የአነስተኛና ትልቅ ቡድኖች ልዩነት የተወሰኑ ዕቃዎችን ብቻ እንደሚሸጥ ሱቅና የትልቅ ገበያ ዓይነት ነው! ትልቅ ገበያ ብዙ ምርቶችን ለብዙ ሰዎች መሸጥ ይችላል። የተወሰኑ ዕቃዎች ብቻ የሚሸጡበት ሱቅ የጥቂት ሰዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ ሁለት ወይም ሦስት ዓይነት ምርቶችን ብቻ ያቀርባል። የወጣቶች መርሐግብር ውጤታማነት በአባላቱ ብዛት ወይም በመርሐግብሮቹ ውስብስብነት ሳይሆን፣ በአባላቱ መንፈሳዊ ዕድገት መለካት ይኖርበታል።

**አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት መሠረታዊ መርሐግብሮች-መግቢያ**
ለአጥቢያህ የወጣቶች መርሐግብር ትክክለኛ መርሐግብሮችን መምረጥ ነገሮችን የመገመት ጨዋታን ሊመስል ይችላል! ትክክለኛውን ነገር ከገመትህ፣ ስለምታሸንፍ መልካም ነው። ካልሆነ ግን ትሸነፋለህ!



በርግጥ ከፍተኛ «ውጤታማ» የሆኑት የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች በግምት የማይሠሩና የወጣቶች መርሐግብሮቻቸውን በአምስት የማይዐዘን ድንጋዮች ላይ የሚመሠርቱ ናቸው። እነዚህም የማየዘን ድንጋዮች አምልኮ፣ የወንጌል ስርጭት፣ ደቀመዝሙርነት፣ ህብረትና ሌሎችን ማገልገል ናቸው። እነዚህ ምትክ የሌላቸው አጠቃላይ የወጣቶች መርሐግብር አምስት ክፍሎች ናቸው። 6ም ሆነ 60 አባላት ያሉበት ቡድን ቢኖርህ መርሐግብርህ ሚዛናዊ እንዲሆን ከተፈለገ፣ እነዚህ አምስት መሠረታዊ መርሐግብሮች መሟላት አለባቸው።

ለዚህ ነው አጠቃላይ ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን የሚሰጠው። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የቡድንህ አባላት የቃሉ ተማሪዎች (ደቀመዛሙርት) እንዲሆኑና በዓለማቸው ውስጥ ለክርስቶስ የሚኖሩባቸውን መንገዶች እንዲያገኙ ለማገዝ የተዘጋጁ በውይይት ላይ ያተኮሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ግኝት ልምምዶች ናቸው። የከፍተኛ ጉልበትና የቡድን ውድድር መከሰቻዎች የሆኑትን የወጣቶች ስብሰባዎች በዚህ ውስጥ የምናካትተው ለዚህ ነው። እነዚህም አዳዲስ ወጣቶችን ወደ ቡድኑ በመሳብና የቡድንህን አባላት በማቀራረብ በወንጌል ስርጭት መሣሪያነት የሚያገለግሉ ናቸው። የወጣቶችን የአምልኮ አስተዋጽኦ የምናካትተው ለዚህ ነው። ይህም ወጣቶች ጠቅላላውን የቤተክርስቲያን ህብረት በአምልኮ እንዲመሩ የሚያስችሉ ናቸው።

አሁን ብዙ የወጣቶች መርሐግብር አማራጮች አሉህ። ነገር ግን የወጣቶች መርሐግብርህ ጠንካራና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ከተፈለገ እነዚህ ሦስቱ የግድ መኖር አለባቸው። ስለሆነም፣ የሚከተለውን በጥንቃቄ ማንበብ ይኖርብሃል። እነዚህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለሚገኙት መርሐግብሮች በመሠረታዊ መግቢያነት የሚያገለግሉ ናቸው።

<u>ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት</u>
ዛሬ ወጣቶች የሚወለዱት በጣም በተወሳሰበ ዓለም ውስጥ ነው። በትምህርት ቤት፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በጓደኞቻቸውና በወላጆቻቸው አካባቢ የሚመለከቷቸው እሴቶች የሚጋጩ ናቸው። ከነዚህ ሁሉ ምንጮች ለአንዱ ብቻ እንኳዋን ስለ ሕይወት ምንነትና አንድ ሰው እንዴት መኖር እንዳለበት ግራ የሚያጋቡና ብዙውን ጊዜ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ አሳቦችን ይሰማሉ።

ራስህን የሰጠህ የወጣቶች ሠራተኛ እንደመሆንህ መጠን፣ እግዚአብሔር ወጣቶች ትክክለኛና ከሁሉም የተሻሉ የህይወት ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ እንደሚመራቸው ትገነዘባለህ። ያም ምሪት ያለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ወደ

እውነት ሁሉ ይመራናል:: ስለሆነም፣ ወጣቶች የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናታቸው ወሳኝ ነው:: የወጣቶች አገልጋዮች እንደ ጳውሎስ ተማሪዎቻችን እውነትን እንዲያውቁ ለማገዝ ተጠርተናል:: ይህም እውነት እንደ ደህንነትና ቅድስና ያሉትን ሥነመለኮታዊ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን፣ በየዕለቱ የሚያጋጥሟቸውን ተግባራዊ የህይወት ጉዳዮች የሚመለከት ነው:: ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም እነዚህን ጉዳዮች ለመዳሰስ የታቀደ ነው::

ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የልማዳዊ ሥርዓተ ትምህርት ገጽታዎች አይደሉም:: ወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት ተሳታፊዎች በሚሆኑበት ጊዜ ይህ ፍላጎት ይሟላል:: እነዚህ ትምህርቶች በባህርያቸው ርእሰጉዳያዊ ናቸው:: የወቅቱን ክርስቲያን ወጣቶች ፍላጎቶች የሚያሟሉ ርእሶች ተመርጠው ትምህርቶች ይዘጋጃሉ:: ርእሶቹ የሚመረጡት ከሚከተሉት አራት ዐበይት ምድቦች ውስጥ ይሆናል::

1. *ወቅታዊ ለኅባቢ ጉዳዮች* (እነዚህም አልኮልና ዕፅ፣ ውርጃ፣ ጦርነትና ሰላም፣ ፍቺ፣ ወዘተ. ናቸው::)
2. *የግንኙነት ጉዳዮች* (እነዚህም ትጭጭት፣ ጋብቻ፣ ቤተሰባዊ ችግሮች፣ የዕድሜ እኩያዎች የሚያስከትሏቸው ውጥረቶች፣ ግንኙነቶች፣ ወዘተ. ናቸው::)
3. *የክርስቲያናዊ ዕድገት ጉዳዮች* (እነዚህም ራስን መስጠት፣ ፈተናዎች፣ ባህርያት፣ የሕይወት ውሳኔዎች፣ ወዘተ. ናቸው::)
4. *ሥነመለኮታዊ ጥያቄዎች* (እነዚህም ደህንነት፣ ቅድስና፣ ይቅርታ፣ የእግዚአብሔር ባህርያት፣ ወዘተ. ናቸው::)

**ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ግቦች**

ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች መሠረታዊ ግቦች የሚከተሉት ናቸው::

1. ለወጣቶች የደቀመዝሙርነትና የትምህርት ዕድሎችን መስጠት::
2. ከህይወት ጋር ተዛማጅነት ላለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሊሠራ የሚችል ሞዴል መስጠት::
3. ወጣቶች ጫና በማያሳድሩ ሁኔታዎች የግል እሴቶቻቸውን የሚያካፍሉበትን ዕድል ለመስጠትና እነዚህን እሴቶች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች ጋር ለማነጻጸር::
4. በወጣቶች ስብሰባዎችና ሌሎች የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ወደ ወጣቶች መርሐግብር ለሚገቡ አዳዲስ ወጣቶች ተፈጥሯዊ የክትትል ዕድል ለመስጠት::

ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የሚዘጋጁት በአማካይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ወጣቶችና የወጣቶች መሪዎች ነው:: ዓይነተኛ የወጣቶች መሪዎች ጊዜያቸውንና ችሎታቸውን ለቤተክርስቲያን



የሚሰጡ ምእመናን ሰዎች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ለዝግጅት በቂ ጊዜ የሌላቸው ሲሆን፣ በወጣቶች አገልግሎት መርሆች ብዙ «መደበኛ» ትምህርት የሌላቸው ናቸው:: ነገር ግን እግዚአብሔርንና ወጣቶችን በመውደዳቸው ምክንያት ልባዊ ሸክም ተጭኖባቸዋል:: ወጣቶች ከታላላቅ የህይወት ጉዳዮች ጋር በሚዛመድ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል አውቀው ህይወትን እንዲጋፈጡ ይፈልጋሉ:: ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የተዘጋጁት ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ነው::

**ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ቅርጽ**

ዓይነተኛ ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስምንት መሠረታዊ ክፍሎች ይኖሩታል::

1. *የመሪው መመሪያዎች::* ይህ ከትምህርቱ መጀመሪያ ላይ የሚመጣ ክፍል ነው:: ለመሪ የተዘጋጀ በመሆኑ፣ ይህ ክፍል የሚከተሉትን አሳቦች ይይዛል:: እነዚህም፣ ቁልፍ አሳብ፣ የትምህርቱ ዓላማ፣ የርእሰጉዳዩ አጠቃላይ አሳብ፣ ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎችና የሚገኙባቸው መንገዶች ናቸው::
2. *የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች::* ይህ ክፍል መሪው ትምህርቱን እንዴት እንደሚጀምር አንዳንድ አሳቦችን ይሰጠዋል:: እነዚህም የመክፈቻ አሳቦች የተለያዩ ጨዋታዎች፣ የብዙና አነስተኛ ቡድን ምርጫዎች፣ ፕሮጀክቶች፣ ዝማሬና የመጀመሪያ ደረጃ እንቅስቃሴዎች (ጸሎት፣ ማስታወቂያዎችና መባ) የሚገኙባቸው ናቸው::
3. *የትምህርት ክፍለ ጊዜ::* የዚህ ክፍለ ጊዜ ቀዳሚ ዓላማ ለውይይትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያገለግለውን ትምህርት መሪው ማቅረቡ ነው:: መሪው ትምህርቱን የሚያቀርበው ወጣቶች ራሳቸውን ከሚያገኙበት እውነተኛ የህይወት ገጠመኝ ጋር በሚመሳሰል መንገድ ይሆናል:: የመሪው ትምህርት ሲጠናቀቅ ወጣቶቹ በህይወታቸው ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ እሴቶች መኖራቸውን ይገነዘባሉ:: ይህም ውጥረትን ያስከትልባቸዋል:: ይህንኑ ውጥረት እንደገና መፍጠሩ የወጣቶቹን ህይወት በመግለጥ እምነታቸውን እንዲገመግሙ ያነሣሣቸዋል::
4. *የመወያያ ጥያቄዎች::* መሪው ትምህርቱን ካቀረበ በኋላ ውይይት ይደረግበታል:: ወጣቶች ለእውነተኛ የህይወት ገጠመኞቻቸው ጋር ለሚመሳሰል ታሪክ ምላሽ መስጠት ይፈልጋሉ:: ስለ ታሪኩ የሚሉት ይኖራቸዋል:: የመወያያ ጥያቄዎቹ ወጣቶቹ የራሳቸውን አሳቦችና ለነዚህም አሳቦች መከሰት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች እንዲናገሩ፣ በዚህም የእሴት ዘዴዎቻቸውን እንዲያሳውቁ ለማስቻል ታስበው የተዘጋጁ ናቸው:: የሚቀርቡት ጥያቄዎች እሴቶችን

የሚመዝኑ ይሆናሉ:: እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች በቀድሞዎቹ ገጠመኞቻቸው ላይ በመመሥረት ትክክለኛውን መስመር እንዲገነዘቡ ያስችሏዋል:: እነዚህ ግላዊ የእሴት መመዘኛ ጥያቄዎች ስለሆኑ፣ ስህተትነቱ ወይም ትክክልነቱ ፍንትው ብሎ በግልጽ የሚታይ መልስ ሊኖር አይችልም:: አንዳንድ ጊዜ ትክክል ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት መልሶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ የሚፈለገው በጥሩውና ከዚያ ከተሻለው ጉዳይ አንዱን መምረጥ ይሆናል::

5. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝት::* ለእሴት ጥያቄዎችና ውይይት በቂ ጊዜ ከተሰጠ በኋላ፣ መሪው ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝት ይሸጋገራል:: የሚመረጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከትምህርቱ ርእሰጉዳይ ጋር የሚዛመዱ ይሆናሉ:: ጥቂት አባላት ለሚገኙበት ቡድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝትም ሆነ ብዙ አባላት ለሚገኙበት የመጽሐፍ ቅዱስ ውይይት ምርጫዎች ይሰጣሉ:: ለእያንዳንዱ ምንባብ የጽንሰአሳብ ማብራሪያ ለመሪው ይሰጠዋል:: ማብራሪያውም በምንባቡ ውስጥ የሚገኘውን መሠረታዊ የሥነመለኮት እውነት ያስረዳል::
6. *ብዙ አባላት የሚገኙበት ቡድን የመወያያ ጥያቄዎች::* ተገቢዎቹ ምንባቦች ከተነበቡና ከተጠኑ በኋላ፣ ሌላ የጥያቄና መልስ ክፍለጊዜ ይቀጥላል:: ወጣቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍለጊዜያት የተካሄዱትን ሥነመለኮታዊ ጽንሰአሳቦች መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የእሴትና የጽንሰአሳብ ጥያቄዎች ይቀርባሉ:: እነዚህ ጥያቄዎች ወጣቶቹ የተገነዘቡትን አሳብ በቃላት እንዲገልጹ ለማስቻል የተዘጋጁ ናቸው:: ግቡም፣ (1) ወ ባቶች ግላዊ እሴቶቻቸውን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች ጋር ን ንዲያነጻጽሩና እንዲያወዳድሩ ማገዝ፣ (2) የሚይዟቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ እሴቶች ለይተው እንዲያውቁ ማስቻልና (3) ከወቅቱ ህይወት ጋር በሚጣጣም መልኩ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አኗኗር መመዘኛዎች መሠረት ሕይወታቸውን እንዲያሰናኙ መርዳት ነው::
7. *መዝጊያ::* መሪው አሁን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝት የተወሰዱትን አንዳንድ አሳቦች ከወጣቶቹ ህይወት ጋር በማዛመድ ትምህርቱን ያጠቃልላል:: የዚህ ክፍል ዓላማ መሪው ከትምህርቱ ጋር የሚዛመዱትን አምስት ወይም ስድስት መርሆች ለወጣቶቹ በቀላል አገላለጽ እንዲያቀርብ ማስቻል ነው:: እነዚህ መርሆች አሁንም ሆነ ወደፊት ወጣቶች ከሁሉም የላቀ ሥነምግባራዊና መንፈሳዊ ውሳኔዎችን እንዲሰጡ ሊያግዟቸው ይገባል::
8. *ከሁኔታው ጋር ማስማማት::* ትምህርቱ ከቡድኑ ሁኔታ ጋር ሊስማማ የሚችልባቸውን መንገዶች የሚጠቁሙ አሳቦች



የተዘጋጁ እንደመሆናቸው፣ የቡድኑን አባላት ብዛት፣ አማካይ ዕድሜና የብስለት ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከቡድኖቹ ሁኔታ ጋር የሚስማማ ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማቅረቡ ጠቃሚ ይሆናል::

**አጀማመር**

ለወጣቶች አገልግሎት ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ለመጠቀም ከወሰንህ፣ ለአጀማመር የሚረዱህ ነጥቦች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል::

1. **ለልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት** *ተስማሚ ጊዜ ምረጥ::* አንዳንዶች ምናልባትም አዋቂዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያካሂዱባቸውና ልጆች ልዩ መርሐግብሮቻቸውን የሚከታተሉበት ረቡዕ ምሽት ጥሩ ጊዜ እንደሆነ ያስባሉ:: ሌሎች ደግሞ ዓርብ ምሽት የተሻለ እንደሆነ ተገንዝበዋል:: ይሁንና፣ **ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት** ከሳምንቱ በየትኛ ውም ቀን ሊካሄድ እንደሚችል መገንዘቡ ጠቃሚ ነው::
2. *ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ምረጥ:* በዚህ መጽሐፍ ውስጥ 25 ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ተካተዋል:: ጥናቶቹ በርእሰጉዳይ ላይ ተመሥርተው የሚዘጋጁ በመሆናቸው፣ በፈለግኸው ቅደም ተከተል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ:: ቡድንህ የተወሰነ ፍላጎት እንዳለው ወይም የተወሰነ ትምህርት ልዩ ትኩረት እንደሚያገኝ ካሰብህ፣ ለዚያ ፍላጎት የሚስጥ **ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት** ምረጥ:: የምትመርጠው ከ25 ርእሰጉዳዮች ውስጥ መሆኑ ማቴሪያሉን በፈለግከው መንገድ የመጠቀምን ዕድል ይጨምራል::
3. *የመሪው መመሪያ የሚለውን ክፍል በጥንቃቄ አንብብ:*
4. *የመሰብሰቢያ ቦታ ምረጥ:* እያንዳንዱ ትምህርት የቡድን እንቅስቃሴዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀ መሆኑን አትዘንጋ:: ቡድኑ እንደ ልብ መጠቀም የሚችልበትን ስፍራ ምረጥ::
5. *ማስታወቂያ በመናገር ሰዎች ሁሉ የጥናቱን መጀመር እንዲያውቁ አድርግ:*
6. *በተቻለ መጠን ትምህርቱን በጥልቀትና በምልዓት አዘጋጅ:: መሪ* **በልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት** ውስጥ ወሳኝ ሚና አለው:: የአንድ ሰዓት ዝግጅት ለጥናቱ በቂ ሊሆን ይችላል!
7. **ጸልይ...** እግዚአብሔር በልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመጠቀም ወጣቶችህን እንዲለውጥ ጸልይ::

**ልምምዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት** በአጠቃላይ ከአንድ ሰዓት እስከ አንድ ሰዓት ተኩል ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ

ጥናት ነው። በየትኛውም የትምህርቱ ክፍል ውስጥ የፈለግኸውን ያህል ጊዜ የማጥፋት ነጻነት አለህ። የተሟላ ክፍለጊዜ ለመፍጠር የትምህርትህ ክፍሎች ተያይዘው መቅረባቸውን ማረጋገጥ ይኖርብሃል።

**አጠቃላይ የወጣቶች አገልግሎት አምልኮ**

ፈጠራ የታከለበት የወጣቶች አምልኮ ሚዛናዊና ሁለንተናዊ የሆነ የወጣቶች አገልግሎት ጠቃሚ ክፍል ነው። በዚህ ረገድ፣ ወጣቶች ከአዋቂዎች የተለዩ አይደሉም። እንደ አዋቂዎች ሁሉ ወጣቶች ተሳትፎአቸውን የሚያበረታታና ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲያቀርቡ ዕድል የሚሰጣቸውን አምልኮ ይፈልጋሉ። ይሁንና፣ የወጣቶች አምልኮ ብዙውን ጊዜ ከወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ማህበራዊ ክስተቶችና የአገልግሎት ፕሮጀክቶች በኋላ ይጠናቀቃል።

አዋቂዎች ያቀዷቸውና የሚመሯቸው የአምልኮ ልምምዶች ሁሉንም የአማካይ ወጣቶች ፍላጎቶች ያሟላሉ ብለን ልንገምት አንችልም። ወጣቶች ወደ አምልኮ ልምምዶች የሚያመጧቸው ፍላጎቶችና የሚጠብቋቸው ነገሮች ከአዋቂዎች የተለዩ ናቸው። ስለሆነም፣ በመደበኛነት የቤተሰብ አባላት አብረው ማምለካቸው ተገቢ ቢሆንም፣ ወጣቶች በተለይ ለራሳቸው የተዘጋጁ የአምልኮ ዕድሎች ቢሰጧቸው መልካም ነው።

የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት በይዘትና በመዋቅር ከቤተሰብ አምልኮ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን፣ በአቀራረብ ግን ይለያል። የወጣቶችም ሆነ የቤተሰብ የአምልኮ አገልግሎት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ውዳሴንና ምስጋናን ያካትታል። በሁለቱም ላይ የጉባኤና ልዩ መዝሙሮች ይኖራሉ። ሁለቱም በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ የሚመሠረቱ ይሆናሉ። ሁለቱም ተሳታፊዎቻቸው የቅድስናና የአገልግሎት ህይወት እንዲመሩ ያደፋፍራሉ። እነዚህ ትርጉም ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምልኮ ክፍሎች ናቸው። እነዚህ የዕድሜ ልዩነቶችን የሚያልፉ ነገሮች ናቸው። የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ከአዋቂዎች የሚለየው በወጣቶች ልዩ ፍላጎቶች ላይ የሚያተኩርና ሊረዱ በሚችሉት ቋንቋ የሚቀርብ በመሆኑ ነው። በወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ውስጥ የቡድን ዝማሬው የአዲሱን ትውልድ ስልቶች የሚያንጸባርቁትንና በጊዜ ርዝመት የተረጋገጡትን ታላላቅ መዝሙሮች የሚያካትት ይሆናል። በወጣቶች አምልኮ ላይ ልዩ መዝሙር በወጣቶች ተዘጋጅቶ የልባቸውን እምነት በሚንጸባርቅ መልኩ ይቀርባል። መልእክቱም ወጣቶች በሚረዱበት ቋንቋና ከህይወታቸው ጋር ለሚዛመዱ ጉዳዮች መልስ በሚሰጥ መልኩ ይቀርባል። በወጣቶች አምልኮ ላይ ወጣቶች ለደቀመዝሙርነት ህይወትና ሙሉ ለሙሉ ክርስቶስን ለመከተሉ ተግባር ራሳቸውን እንዲለዩ ጥሪ ይቀርብላቸዋል።



(በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ የወጣቶች አምልኮ የሚያመለክተው በወጣቶች ስፖንሰርነት ለሚካሄደውና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የወጣቶች አምልኮ አስተዋጽኦ ለሚከተል የአምልኮ አገልግሎት ያመለክታል።)

**ትርጉም ያለው የወጣቶች አምልኮ ልምምድ መሠረታዊ ነገሮች**

አምልኮ ውስብስብ ነገር ነው። ወጣቶችና አዋቂዎች ወደ አምልኮ የሚገቡት በተለያዩ የመንፈሳዊ ብስለት ደረጃዎች እንደመሆኑ፣ ፍላጎቶቻቸውም የተለያዩ ናቸው። ነገር ግን አምልኮው ትርጉም ያለው እንዲሆን ከተፈለገ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች ሊኖሩት ይገባል።

1. *የመንፈስ ቅዱስ መገኘት።* ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና» ብሏል (ማቴዎስ 18:20)። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአምልኮ የሚያቀጣጥለውና ኢየሱስ ክርስቶስን እውን አድርጎ የሚያቀርብልን መንፈስ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱሱ አማካኝነት በመካከላችን መኖሩን ማወቃችን መሠረታዊና ምትክ የሌለው የወጣቶች የአምልኮ ክፍል ነው። በጸሎት፣ በመዝሙራትና በቅዱሳት መጻሕፍት አ ነት፣ መንፈስ ቅዱስ ትኩረታችን ከራሳችን ወደ ክርስቶስ እንዲዞር ያደርጋል።
2. *ዝግጅት።* ፈጠራ የታከለባቸውና ትርጉም ያላቸው የወጣቶች የአምልኮ ልምምዶች እንዲሁ አይከሰቱም። የአምልኮ መሪው በጥንቃቄ ማቀድና መዘጋጀት አለበት። የአምልኮን ቅደምተከተል ማቀድና አስተዋጽኦ ማዘጋጀት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በፍጹም አይቀንሰውም። እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ በወጣቶች ህይወት ውስጥ በአግባቡ የሚሠራው ቅደምተከተሉን በጠበቀ፣ ምክንያታዊ በሆነና በሚገባ በታቀደ አምልኮ ውስጥ ነው። ሥርዓት-አልበኝነት የሰዎችን ትኩረት የሚስበው ወደራሱ እንጂ ወደ እግዚአብሔር አይደለም። ስለሆነም፣ የወጣቶችን የአምልኮ አገልግሎት በምናቅድበት ጊዜ የሚከተሉትን ቅደምተከተሎች መጠቀም ጠቃሚ ይሆናል።
   ሀ. አንድ ጭብጥ በመምረጥ ለአምልኮው የዓላማ መግለጫ ጻፍ።
   ለ. የጉባኤ መዝሙሮችን፣ ልዩ መዝሙር፣ ድራማና የጻፍኸውን የዓላማ መግለጫ የሚያንጸባርቅ መልእክት ምረጥ።
   ሐ. በነዚህ አያሌ የአምልኮ ተግባራት ላይ የሚሳተፉትን አገልጋዮች አነጋግር። በተቻለ መጠን ቀደም ብለህ አስታውቃቸው። ሁሉም ተሳታፊዎች መዘጋጀታቸውን ካረጋገጥህ በኋላ፣ የልምምድ/የዝግጅት የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅ።
   መ. የአምልኮ መሣሪያዎችን (የድምጽ መሣሪያዎች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ አልባሳት፣ መድረክ፣ መደገፊያዎች፣ የመዝሙር

ደብተሮች፣ የመዘምራን መዝሙር፣ አሽርሄድ ፕሮጀክተር፣ ወዘተ.) ማቅረብ፣ መፈተሽና የሚጠቀሙባቸውን ሰዎች ማግኘት እንዳለብህ አትዘንጋ።

ሠ ለሁሉም ተሳታፊ የአምልኮውን ዝርዝር ቅደምተከተል ጻፍ። እያንዳንዱ ተሳታፊ የዚህን ጽሑፍ ቅጂ ማግኘቱን አረጋግጥ።

ረ. ትርጉም ያለው የወጣቶች የአምልኮ ልምምድ እንዲካሄድ ጸልይ። አሁን ልታዘጋጅ የምትችለውን ሁሉ ስላደረግህ፣ ዘና ብለህ እግዚአብሔር የድርሻውን እንዲወጣ ተጠባበቅ።

3. *ተሳትፎ።* በወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ውስጥ የሚደረገው ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ነው። አብዛኞቹ ወጣቶች ቁጭ ብለው እንዲመለከቱ ብቻ በሚያደርግ የአምልኮ አገልግሎት አይረኩም። ለነሱ ተሳትፎ ቁልፍ ጉዳይ ነው። የወጣቶችን የአምልኮ አገልግሎት የሚያቅዱ ሰዎች ብዙ ወጣቶች ተሳታፊ የሚሆኑባቸውን መንገዶች ማመቻቸት አለባቸው። አማካዩ ወጣት ቁጭ ብሎ ያዳመጠውን መልእክት ይዘት ሊያስታውስም ላያስታውስም ይችላል። ነገር ግን ተሳታፊ የሆነበትን ድራማ፣ መዝሙር ወይም ሌላ እንቅስቃሴ መልእክት በአእምሮው ይዞ ሊኖር ይችላል። ወጣቶች መልእክቱን ሲሰሙ፣ ሲያዩ፣ ሲዳስሱትና ሲሠሩት መንፈሳዊ እውነቶችን ሊገነዘቡና የህይወት ለውጥ ሊያሳዩ ይችላሉ። አንድ ሰው እስካልተመገበ ድረስ የምግቡ ተሳታፊ ሊሆን አይችልም... እስካልተጓዘ ድረስ የሽርሽሩ ተሳታፊ ሊሆን አይችልም... በትጋት እስካልተሳተፈ ድረስ የአምልኮ ተካፋይ ሊሆን አይችልም።

የወጣቶች በአምልኮ ውስጥ መሳተፍ ከሚያስገኛቸው ውጤቶች አንዱ ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስቲያን ችሎታዎቻቸውን ማሳደጋቸው ነው። ወጣቶች የሚማሩት አንድን ነገር በማድረግ ነው። ይህንንም በማድረጋቸው፣ ለወደፊቱ የቤተክርስቲያን የዕድሜ ልክ ተሳትፎና አመራር ይሠለጥናሉ። የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት በቤተክርስቲያን ፊት ስጦታዎቻቸውንና ችሎታዎቻቸውን እንዲለማመዱ ብቻ ሳይሆን እንዲበረታቱም በማድረግ ለወጣቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል።

4. *የተለያዩ ምርጫዎችን ማቅረብ።* በአምልኮ ላይ ሰዎችን ማገልገል የሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። የወጣቶች የአምልኮ ልምምድ ለተለያዩ የአምልኮ እንቅስቃሴዎች ፍጹም ተስማሚ ነው። ወጣቶች ተሳታፊዎችን ሊያስደስትና ጠቅላላው የቤተክርስቲያን ማህበረሰብ ወደ ቤተክርስቲያን ተመልሶ እንዲመጣ የሚያደርገው አምልኮው ላይ የሚታየው የግርምትና ቀጥሎ ምን ይከሰት ይሆን? የሚል ጉጉት ነው። የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚደረጉት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ሲባል አይደለም። ስለሆነም፣ የተለያዩ ነገሮችን ማቅረብ ለፍሬያማ የወጣቶች አምልኮ ልምምድ የሚበጀው ትኩስነትና ፈጠራ የጎላበት እንደሆነ ነው።



በፈጠራ የታገዘ የወጣቶች አምልኮ

የሚከተሉት በወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ላይ ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ጠቃሚ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

ድራማ። ድራማ ለቤተክርስቲያን አዲስ ነገር አይደለም። ለብዙ መቶ ዓመታት ጉልህ የክርስቲያናዊ እምነት መግለጫና የአምልኮ መሣሪያ በመሆን ሲያገለግል ቆይቷል። የድራማ ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች በቡድንህ ውስጥ ካሉና አንተ ወይም ሌላ ፍላጎት ያለው መሪ ይህንኑ ከሥራ ጋር ለማዋል የሚያስችል ጊዜ ካላችሁ፣ በተከታታይነት የሚቀርብ ድራማ መጠቀሙ ሊታሰብበት የሚገባው ነው። ድራማ መድረክን፣ አልባሳትንና መብራትን ባሟላ መልኩ ወይም ቀለል ባለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ቃለ ምልልስ፣ የስብከት ንድፍ፣ ወይም የጋራ ንባብ መልክ ቢቀርብ፣ ወጣቶችን የሚስብ ፈጠራዊ የአምልኮ ተግባር መሆኑ እየተረጋገጠ በመሄድ ላይ ይገኛል።

አሻንጉሊቶች። እንደ ድራማ ሁሉ፣ አሻንጉሊቶችም (የአሻንጉሊቶች ትርኢት) ለብዙ ዘመናት ለሃይማኖታዊ ዓላማዎች ሲያገለግሉ ቆይተዋል። አንዳንድ የወጣቶች አገልግሎት መሪዎች አሻንጉሊቶችን የመዝናኛ መልኮች ብቻ አድርገው ቢመለከቱም፣ ሌሎች ግን የአሻንጉሊቶች አገልግሎት ለወጣቶች ጠቃሚ የፈጠራ አማራጭ፣ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን እውነተኛ አገልግሎት ሊሆን እንደሚችል ይገነዘባሉ። በቡድንህ ውስጥ በብዙ ህዝብ መካከል ቆመው ለመዘመር፣ ድራማ ለመጫወት የማይደፍሩ ወጣቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች በአሻንጉሊቶች መርሐግብር ውስጥ ተሳትፈው ደስ ሊሰኙና ሊጠቀሙ ይችላሉ። በርግጥ ጠቅላላው የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት በአሻንጉሊቶች ዝግጅት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ላይኖርብህ ይችላል። ነገር ግን አሻንጉሊቶች በሚገባ ለተዘጋጀ የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ላይ ህይወት ሊዘሩና ዓይነት ሊጨምሩ ይችላሉ።

ሙዚቃ። ሙዚቃ በወጣቶች ባሕል ውስጥ ዓቢይ ሚና ሲጫወት የኖረ ሲሆን፣ አሁንም ይህንኑ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛል። አንድ ወጣት በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት የሙዚቃ አስተዋጽኦ ሊቀንስ አይችልም። እንዲያውም በዘመኑ ክርስቲያን ወጣት ህይወት የሙዚቃ ድርሻ ሊጨምር ይችላል። ስለሆነም፣ የሙዚቃ አገልግሎት በወጣቶች አምልኮ ውስጥ ጠቃሚ ስፍራ ይኖረዋል። ፍሬያማ የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ወጣቶች የሙዚቃ ችሎታቸውን ለጠቅላላው ቤተክርስቲያን እንዲያካፍሉ ዕድል ይሰጣቸዋል። በመሣሪያ ብቻ የተዘጋጀም ይሁን በድምጽ፣ የቡድንም ይሁን የግል፣ በመዝሙር መልክ የሚቀርብ የወንጌል አገልግሎት ለወጣቶች ጥቅምና ለቤተክርስቲያን በረከት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ስብከት። ስብከት ብዙውን ጊዜ የአምልኮ ማዕከላዊ ክስተት ተደርጎ ይቆጠራል። በወጣቶች አምልኮ ውስጥም ይህ እውነት ነው። በመጋቢው፣ በወጣቶች መጋቢ፣ በምእመን የወጣቶች መሪ፣ ወይም ለስብከት አገልግሎት እንደተጠራ በሚገነዘብ ወጣት የሚቀርብ የእግዚአብሔር ቃል ስብከት የመጀመሪያውን ስፍራ ሊይዝና በአምልኮ ቅደም ተከተል ውስጥ በማዕከላዊነቱ መቀጠል አለበት። ስለሆነም፣ የወጣቶችን አምልኮ በተመለከተ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ ስብከት መካተት አለበት ወይ? የሚል ሳይሆን፣ እንዴት መስበክ አለብን? የሚል ሊሆን ይገባል።

**የድጋፍ ተግባራት።** ብቡድኑህ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ሁሉ የሙዚቃ መሣሪያ ሊጫወቱ፣ ሶሎ ወይም ከመዘምራን ቡድን ጋር አብረው ሊዘምሩ፣ በስላይድ የታገዘ ማብራሪያ ሊሰጡ፣ ወይም የአሸንጉሊት ትርኢት ሊያቀርቡ አይችሉም ይሆናል። ነገር ግን ሌሎች የድጋፍ ሰጭነት ተግባራት ሊያከናውኑና ከዚህም የተነሣ የአምልኮ መርሐግብሩ ጠቃሚ አካላት እንደሆኑ ሊገነዘቡ ይችላሉ። አምልኮውን ለሰዎች በማስተዋወቅ፣ የድምጽ እና/ወይም የመብራት መሣሪያዎችን በማዘጋጀት፣ ለመድረክ ትዕይንት የሚያገለግሉትን ነገሮችና አልባሳት በማሰናዳት፣ የአምልኮ ጽሑፎችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት፣ መባ በመሰብሰብ፣ በጉባኤ ላይ በመጸለይ፣ ወዘተ. ሊያገለግሉ ይችላሉ። እነዚህ ወጣቶች በወጣቶች አምልኮ ወቅትና ቀደም ብለው ሊያከናውኗቸው የሚችሏቸው ነገሮች ናቸው። ዋናው ነገር እያንዳንዱን ወጣት የመርሐግብሩ ተካፋይ ማድረግህና ከዚህም የተነሣ የተፈላጊነትና የጠቃሚነት ስሜት እንዲያድርባቸው ማድረግህ ነው።

**የወጣቶችን የአምልኮ መርሐግብር መጀመር**

1. *መጀመሪያ ከወጣቶች አገልግሎት የአመራር አባላት ጋር (መጋቢህን ጨምሮ) ጋር በመሰባሰብ፤ በወጣቶች የሚካሄድና በወጣቶች የሚመራ የአምልኮ አገልግሎት እንዲኖር መፈለግህን ግለጽላቸው።* ምናልባት ለዚህ ዓይነቱ አገልግሎት አመቺው ጊዜ እሑድ ምሽት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ፣ አልፎ አልፎ እሑድ ጠዋት ወይም ረቡዕ ምሽት ማድረጉም ተስማሚ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት በወር ወይም በስድስት ሳምንታት አንድ ጊዜ ማካሄዱ በቂ ሊሆን ይችላል።
2. *ቀኑ ከተቆረጠ በኋላ አገልጋዮችን አፈላልግ።* በግል ወይም በቡድን የመዘመር ፍላጎት ያላቸው በቂ ወጣቶች አሉህ? የድራማ ቡድን የመጀመር ፍላጎት ያላቸው ወጣቶች አሉህ? የመገናኛ ብዙሃን ወይም የአሻንጉሊት ትርኢት ለማቅረብ የሚፈልጉ ወጣቶች አሉህ? ለነዚህ ቡድኖች አመራር ለመስጠት የሚችሉና የሚፈቅዱ



2. *ቀኑ ከተቆረጠ በኋላ አገልጋዮችን አፈላልግ።* በግል ወይም በቡድን የመዘመር ፍላጎት ያላቸው በቂ ወጣቶች አሉህ? የድራማ ቡድን የመጀመር ፍላጎት ያላቸው ወጣቶች አሉህ? የመገናኛ ብዙሃን ወይም የአሻንጉሊት ትርኢት ለማቅረብ የሚፈልጉ ወጣቶች አሉህ? ለነዚህ ቡድኖች አመራር ለመስጠት የሚችሉና የሚፈቅዱ
መሪዎች አሉህ? ከእነዚህ ሁሉ ወገኖች ጋር በመነጋገር፣ በወጣቶች አምልኮ አገልግሎት ላይ እንዲሳተፉ ጠይቃቸው።
3. *ለምሽቱ ጭብጥ ምረጥ።* የአገልግሎቱን ጭብጥ ለመወሰን የተወሰነ ወቅት ልትመርጥ ትችላለህ (ገና፣ ፋሲካ፣ በዓለሃምሳ፣ የአድዋ በዓል፣ የሴቶች ቀን፣ የአርበኞች ቀን፣ ወዘተ.)። ወይም እንደ ቤተሰባዊ ግንኙነቶች፣ ምስክርነት፣ ወይም ይቅርታ የመሳሰሉትን ርእሰጉዳዮች ልትመርጥ ትችላለህ። የትኛውንም ጭብጥ ብትመርጥ፣ ጭብጡ የአምልኮውን አገልግሎት ይዘት እንዲወስን አድርግ። ይህም መልእክቱንና መዝሙሩን የሚጨምር ይሆናል።
4. *የሚያስፈልግህን ሁሉ ሰብስበህ በተቻለ ፍጥነት ለአገልግሎቱ መዘጋጀት ጀምር።*
5. *በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የአምልኮ አስተዋጽኦ ተመልከትና ለዓላማህ ሊጠቅሙ ወይም ተስማምተው ሊቀርቡ የሚችሉትን ምረጥ።*

**ጸጋዬ ይበቃሃል!**

**2ኛ ቆሮንቶስ 12፡9**

# ልምምዳዊ

# የመጽሐፍ ቅዱስ

# ጥናቶች



## ይቅርታ

ከዳግ ራንያን

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና (ቁልፍ) አሳብ .. የእግዚአብሔር ይቅርታ ለእኔ ነው!
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲቀበሉና ራሳቸውን ይቅር እንዲሉ መርዳት።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ብዙ ወጣቶች ከሐጢአታቸው ንስሐ ከገቡ፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከጠየቁና ከሐጢአት መንገዳቸው ከተመለሱ በኋላ፣ አሁንም ስለ ቀድሞው ሐጢአታቸው የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማቸዋል። ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው። 1) ያገኙትን ይቅርታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች ይልቅ በስሜታቸው ላይ ስለሚመሠርቱና 2) ከራሳቸው ጋር መቀያየማቸው እግዚአብሔር ይቅር ሊለኝ አይችልም ብለው እንዲያምኑ ስለሚያደርጋቸው ነው።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ አሳቦች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተጠቅሰዋል።)

1. እንደ ቡድንህ አባላት ብዛት፣ ይህ እንቅስቃሴ በአንድ ቡድን ወይም በሁለቱና ከዚያ በሚበልጡ ቡድኖች መካከል በማደረግ ውድድር ሊካሄድ ይችላል። «ከአሁን ጀምሮ በተቻለ ፍጥነት በቁመታችሁ ተሰለፉ» በላቸው። በተጨማሪም፣ በልደት ቀናቸው፣ በስማቸው የፊደል ተራ (አልፋቤት)፣ ከተንበረከኩ በኋላ በቁመታቸው ቅደም ተከተልና ከዚያም በመቆም .. በዚህ ጊዜ ከረዣዥሞች ወደ አጫጭሮች እንዲሰለፉ ማድረግ ትችላለህ። (ይህ ከ4 እስከ 6 ቡድኖች መካከል ሊደረግ ይችላል።)
2. የሚከተሉትን አምስት ጥያቄዎች ድምጽህን ከፍ አድርገህ በማንበብ ወጣቶቹ መልሳቸውን ከወረቀት ላይ እንዲያሰፍሩ አድርግ። አራቱን ጥያቄዎች በትክክል እንዲመልሱና ሆን ብለው ለአንደኛው የተሳሳተ መልስ እንዲጽፉ ንገራቸው። ወጣቶቹ መልሶቻቸውን በሚያነቡበት ጊዜ፣ ሰሚዎቹ የተሳሳተውን ለይተው እንዲያወጡ ጠይቃቸው።
    1. ሙሉ ስምህ ማነው?
    2. የተወለድከው የት ነው?
    3. የምትወደው ምግብ ምንድው?
    4. የምትወደው ጨዋታ/ስፖርት ምንድነው?
    5. ትልቅ ስትሆን ምን ዓይነት ሥራ ለመሥራት ታስባለህ?
    6. የህይወት ዓላማህ ምንድነው?

3. የቡድን ዝማሬ

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ ቋንቋ አቅርበው)
ልጆች ሳላችሁ የጓደኛችሁን አሻንጉሊት ሰብራችሁ ታውቃላችሁ? ምን ዓይነት ስሜት ተሰማችሁ? የጓደኛችሁስ ምላሽ ምን ነበር? ጓደኛችሁ ይቅር ይቅር ይላችኋል? ብለህ ጠይቃቸው።
ከዚያም የሚከተለውን ወይም እሱን የሚመስል የራስህን ታሪክ ንገራቸው። ልጅ ሳለሁ፣ ከአሻንጉሊቶቹ አንዱን ስለሰበርሁበት ጓደኛዬ ይቅር እንዲለኝ መጠየቄን አስታውሳለሁ። ልጁ የኋላ ኋላ እያመነታ፣ «ይቅር ብዬሃለሁ» ሲል ይቅርታዬን እንደተቀበለ ገለጸልኝ። ነገር ግን ይቅርታ የማግኘት ስሜቴ ብዙም ሊቆይ አልቻለም። ለረዥም ጊዜ፣ ጓደኛዬ በጨዋታ ሲቀድመኝ ወይም መንገድ ሲያልፍ ሲፈልግ፣ ስለዚያ አሻንጉሊት ያስታውሰኝ ጀመር። ጓደኛዬ ይቅርታ ያደረገልኝ ቢሆንም፣ ያ የተሰበረው አሻንጉሊት ያስከተለው የጥፋተኝነት ስሜት ከአእምሮዬ ሊፋቅ አልቻለም። ዛሬም ሳይቀር ይቅርታ አግኝቻለሁ ብዬ ባስብም፣ ቀደም ሲል የፈጸምኋቸው የተሳሳቱ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ ይረብሹኛል። አንዳንድ ጊዜ ራሴን ይቅር ለማለት እቸገራለሁ።
ስለ እግዚአብሔር ይቅርታም አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ ስሜቶች ያድሩብናል። እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን ከጠየቅን በኋላ ሳይቀር፣ የቀድሞ ሐጢአቶቻችንን ለመዘንጋት የምንቸገረው ለምንድነው?
እስኪ ስለዚህ ምሳሌ ትንሽ እስቡ። ዳንኤል በክርስቶስ ካመነ ብዙም አልቆየም። ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ዳንኤልና ጓደኞቹ ከካፍቴሪያ ምግብ በልተው ሳይከፍሉ ወጡ። ዳንኤል እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ከጠየቃቸው ሐጢአቶች አንዱ ይኼ ነበር። ከዚያም ዳንኤል ወደ ካፍቴሪያው ተመልሶ ሃላፊውን ይቅርታ መጠየቅና ሂሳቡን መክፈል እንዳለበት አሰበ። ይህንን ባደረገበት ሰዓት ግን የካፍቴሪያው ሃላፊ ገንዘቡን ከወሰደ በኋላ ተቆጥቶ ይቅርታውን ሳይቀበል ቀረ። ከዚህም በላይ፣ ከአያሌ ሳምንታት በኋላ ዳንኤል ከቤተክርስቲያን ጓደኞቹ ጋር ወደ ካፍቴሪያው ሲሄድ ሃላፊው ወንጀለኛ ነህ በማለት ዳንኤልን አሳፈረው። ዳንኤል አሁንም ይቅርታ ለመጠየቅ ሞከረ። ነገር ግን ሃላፊው ይቅርታውን ባለመቀበል አሁኑኑ ከካፍቴሪያው ወጥቶ እንዲሄድና ከእንግዲህም ዝር እንዳይል አዘዘው። የሃላፊው ይቅርታን መንፈግ ዳንኤል እግዚአብሔርስ ይቅር ብሎኝ ይሆን? ብሎ እንዲያስብ አደረገው።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ከተወያያችሁ በኋላ፣ እንደገና አንድ ላይ ሆናችሁ ተወያዩ።)

1. አንተ በዳንኤል ቦታ ላይ ብትሆን ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል?
2. ዳንኤል ሁኔታውን ስላስተናገደበት ሁኔታ ምን ይሰማሃል?



3. ከዳንኤል ጋር ወደ ካፍቴሪያው ከሄዱት ልጆች አንዱ ብተሆን ለዳንኤል ምን ትነግረው ነበር?
4. ለዳንኤል እየተናገርህ ያለህ ሰይጣን ብትሆን ስለዚህ ጉዳይ ምን ትለዋለህ?
5. ለዳንኤል እየተናገርህ ያለህ አምላክ (እግዚአብሔር) ብትሆን ስለዚህ ጉዳይ ምን ትለዋለህ?
6. ዳንኤል ሃላፊው ይቅር እንዲለው መጠየቁን መቀጠል አለበት?
7. ዳንኤል ከእግዚአብሔር የሚያገኘው ይቅርታ ከሃላፊው በሚያገኘው ይቅርታ ላይ ይመሠረታልን?
8. አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስጠየቅንባቸው የቀድሞ ሐጢአቶች ራሳችንን ይቅር ለማለት የምንቸገረው ለምንድነው?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝት (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው)
እስኪ ስለዚህ ጉዳይ የሚናገሩትን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንመልከት። (በራስህ ቃላት ግለጽ።)
1. 1ኛ ዮሐንስ 1:9 .. *«በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።»* የምንቀበለው የሐጢአት ይቅርታና መንጻት የሚመሠረተው በኑዛዜያችን እውነተኛነትና ጥልቀት ላይ ነው። ከሐጢአታችን የተነሣ ጥልቅ የጥፋተኝነትና ያለመንጻት ስሜት ከተሰማንና እግዚአብሔር ብቻ ይህንን ከልባችን ሊፍቅ እንደሚችል ተገንዝበን በፊቱ ራሳችንን ዝቅ በማድረግ ሐጢአታችንንና ንጹሕ ያልሆነ ሁኔታችንን ከተናዘዝን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ይቅርታን እናገኛለን። ስለ ሐጢአታችን ለእግዚአብሔር ከልባችን ከተናዘዝን ይቅርታና መንጻት የራሳችን ይሆናል። እርሱ ይቅር ስለሚለን፣ እኛም ራሳችንን ይቅር ማለት አለብን። ኢየሱስ ቅጣታችንን ስለወሰደ፣ እኛ ራሳችንን መቅጣት የለብንም።
2. መዝሙር 103:10-12 .. *«እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም። እንደ በደላችንም አልከፈለንም። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ። ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።»* በኃጢአታችን ምክንያት ዘላለማዊ ሞት ተፈርዶብን ነበር (ሮሜ 6:23)። ነገር ግን እግዚአብሔር ሞታችንን በክርስቶስ ላይ አኖረ። ከልባቸው ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙት ሰዎች፣ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ምዕራብ ከምሥራቅ እንደሚርቅ አድርጎ ያስወግድላቸዋል። በሌላ አገላለጽ፣ ከኃጢአታቸው ጋር ሊገናኙ አይችሉም ማለት ነው። አእምሯችን ኃጢአታችንን ሊያስታውስ ቢችልም፣ እግዚአብሔር ግን

ከእይታው አርቆታል። ከእንግዲህ ስለነዚህ ኃጢአቶች በኃላፊነት እንጠየቅም።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ከተወያያችሁ በኋላ፣ እንደገና አንድ ላይ ሆናችሁ ተወያዩ።)

1. የኃጢአትን ይቅርታ ለማግኘት ምን ልናደርግ ይገባናል?
2. ይቅርታው ሊመሠረት የሚችልባቸው ሌሎች ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉን?
3. እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ከጠየቅነው በኋላ፣ ለዚያ ኃጢአት እንደገና በኃላፊነት ልንጠየቅ እንችላለን?
4. «ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ» የሚለው ቃል ይቅርታን ካገኙት ኃጢአቶች ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

ሰ. መዝጊያ

እግዚአብሔር ኃጢአትህን ይቅር ማለቱን በርግጠኝነት ካሳወቅህ፣ ኃጢአቶችህን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ይቅር እንዲልህ ጠይቀው። ከዚያም በ1ኛ ዮሐንስ 1:9 ላይ በተሰጠው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት ይቅርታን እንዳገኘህ እመን። «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።» እርሱ ይቅር እንዳለህና ከኃጢአትህ እንዳነጻህ እመን! የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከጠየቅህ በኋላ፣ ራስህን ይቅር ማለት ካቃተህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለራስህ አቅርብ።

1. በበደሌ ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ያስከተልሁትን ችግር ለማስተካከል የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ?
2. የክርስቶስ ሥቃይና ሞት ለኃጢአቶቼ በቂ አይደለምን? ራሴን መቅጣቴ ጥቅም ይኖረው ይሆን?
3. 1ኛ ዮሐንስ 1:9 እንደሚለው፣ እግዚአብሔር ይቅር ካለኝ ዘንዳ፣ እኔስ ራሴን ይቅር ማለት የለብኝም?
4. ይቅር አልለውም ያልሁት ሰው አለ?

ይህንን ጸሎት ጸልይ፡ ውድ አባታችን ሆይ፣ ኃጢአቶቻችንን ለአንተ ብንናዘዝ ይቅር እንደምትል ቃል ስለገባህልን እናመሰግንሃለን። ከአንተ ጋር ኅብረት እንዳላደርግ የሚከለክሉኝን ኃጢአቶቼን አሁኑኑ ለአንተ እናዘዛለሁ። (ለእግዚአብሔር መናዘዝ ያለባቸው ኃጢአቶች ካሉ ለርሱ እንዲነግሩት አስታውሳቸው።) በ1ኛ ዮሐንስ 1:9 መሠረት ይቅር እንዳልኸን እናምናለን። ኃጢአቶቻችንን ከኛ ስላስወገድህ እናመሰግንሃለን። ራሳቸውን ይቅር ለማለት የተቸገሩትን ሁሉ እንድትረዳቸው እንጠይቅሃለን። በዚህ ጊዜ ሁላችንም ይቅር እንዳልኸን እርግጠኞች ሆነንና ራሳችንንና ሌሎችን ይቅር ለማለት ችለን እንድንሄድ እርዳን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጸልያለን። አሜን።



## የቤተሰብ ችግሮች
### ከሚካኤል ፒትስ

ሀ. የመሪው መመሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. እግዚአብሔር የሚወዱንና የሚንከባከቡን ቤተሰቦች እንዲኖሩን ዐቅዷል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች በተሻለ ሁኔታ ከቤተሰብ አባላት ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ ማስተማር።
3. የትምህርት አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶች ሌሎች ሳይቆጣጠሯቸው ራሳቸውን ችለው ለመኖር ይፈልጋሉ። ከዚህ ፍላጎት የተነሣ ውስጣዊ እና/ወይም ውጫዊ ጸቦችና ችግሮች ይጋፈጡባቸዋል። ለወጣቶች ራሳቸውን ለመቻልና በተመሳሳይ ጊዜ የተቀሩትን የቤተሰብ አባላት ስሜቶች ለመረዳት መሞከሩ ጠቃሚ ነው። ወጣቶች በቤተሰባቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለሚያሳዩበት መንገድ ሊማሩ ይችላሉ።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ አሳቦች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተጠቅሰዋል።)

1. ይህን ዓረፍተነገር ጨርሱልኝ፡ ወጣቶቹ ዓረፍተነገሩን እንዲጨርሱልህ ጠይቃቸው። «እናቴ ወይም አባቴ ብትሆን ኖሮ...» ዓረፍተነገሩን በፈለጉት መንገድ እንዲጨርሱ ፍቀድላቸው። በዚህ ላይ ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆነ መልስ ማግኘት አይቻልም።
2. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው)

አብዛኞቻችን አንዳንድ ቤተሰባዊ ችግሮች ያጋጥሙናል። በተለይ ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የማይግባቡባቸው ጊዜያት አሉ። አሁን የምንማራችሁን ታሪክ ስሙና ምን ልታደርጉ እንደምትችሉ አስቡ።
ሴሲል በቤተክርስቲያን የወጣቶች አገልግሎት ቡድን ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶች አንዱ ነው። ወላጆቹም የቤተክርስቲያን አካል ናቸው። ሴሲል ለወጣቶች ቡድን የቅዳሜና እሑድ የካምፕ መርሐግብር ለማቀድ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል። እንዲያውም፣ ከትምህርት ቤት ጓደኞቹ አንዱ አብሮት ወደ ካምፕ አገልግሎት ለመሄድ ተስማምቶ ነበር። ሴሲልም ጓደኛው በካምፕ በክርስቶስ እንዲያምን እየጸለየለት ነበር። ይህም ሆኖ አንድ ችግር ነበር። ሴሲል በካምፑ ዕቅድ ላይ ብዙ ሲሠራ ስለቆየ በትምህርት ቤት ለአንድ ትምህርት ማዘጋጀት የነበረበትን ሪፖርት አላጠናቀቀም ነበር። የሴሲል አባት ሪፖርቱን ዓርብ ዕለት ካላጠናቀቀ ቅዳሜ ወደ ካምፑ ሊሄድ እንደማይችል ነገረው። ሴሲል ሪፖርቱን በዚህ ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ እንደማይችል ስለተገነዘበ፣ ምን ማድረግ

እንዳለበት መወሰን ቸገረው። አባቱ ሪፖርቱን ስለመጨረሱ እንደሚጠይቀው ያውቃል። ሴሲል እውነቱን ከተናገረ አባቱ ወደ ካምፕ እንዲሄድ አይፈቅድለትም። ይህ ከሆነ ደግሞ ጓደኛውም ከካምፕ ለመቅረት ይገደዳል ማለት ነው። ሪፖርቱን ጨርሻለሁ ካለው ግን ወደ ካምፕ መሄድ ይችላል። ጓደኛውም አብሮት በመሄድ ምናልባት ደኅንነትን ሊያገኝ ይችላል። ሴሲል ሪፖርቱን ለመምህሩ ሰኞ ዕለት መስጠት ይችላል። እስካሁን የትምህርት ቤት ውጤቱ ጥሩ ስለሆነ፣ እስከ ሰኞ አዘግይቶ ቢሰጥም እንኳዋን ጥሩ ማርክ ሊያገኝ ይችላል።

*መ. የመወያያ ጥያቄዎች* (በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ከተወያያችሁ በኋላ፣ እንደገና አንድ ላይ ሆናችሁ ተወያዩ።)
1. በሴሲል ቦታ ላይ ብትሆን ምን ዓይነት ስሜት ያድርብሃል?
2. ሴሲል ለምክር አንተ ጋ መጥቶ ቢሆን ኖሮ ምን ትመክረው ነበር?
3. የሴሲል አባት የወሰደው እርምጃ ትክክል ነው? ለምን?
4. በሴሲል ቦታ ላይ ብትሆን አብሮህ ሊሄድ ለነበረው ጓደኛህ ምን ትለዋለህ?
5. ሴሲል ይህን ችግር ለማስወገድ ምን ሊያደርግ ይችል ነበር?
6. ለአንድ አፍታ የሴሲል አባት ነኝ ብለህ አስብ። ሴሲል ሪፖርቱን እንዳልጨረሰ ቢነግርህ፣ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል? ለሴሲል ምን መልስ ትሰጠዋለህ?

*ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝት* (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)
በዚህ ትምህርት ላይ እገዛ እንዲያደርጉልን እስኪ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንመልከት።
1. ቆላስይስ 3:20 .. *«ልጆች ሆይ፣ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ።»*
የእግዚአብሔር ቃል ልጆች ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙ ያዛል። እግዚአብሔር ነገሮችን ያቀደው በዚህ መልኩ ነው። ልጆች (እና ወጣቶች) ለወላጆች አለመታዘዛቸው ብዙውን ጊዜ ችግሮችን፣ ግራ መጋባትንና ጥላቻን በቤተሰብ ውስጥ ይፈጥራል።
2. ፊልጵስዩስ 2:3-4 .. *«ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳዋን አታድርጉ። ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር። እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።»* ወጣቶች እንደመሆናችን፣ ለሌሎች የሚጠቅመውን እንድንመለከት ተነግሮናል። «ሌሎች» የሚለው ወላጆቻችንን ይጨምራል። ለወላጆቻችን ከፍቅር ይልቅ ራስወዳድነት በገዘፈበት ሁኔታ ምላሽ በምንሰጣቸው ጊዜ፣ ለሥቃይ እንዳርጋቸዋለን። ሐዋርያው ጳውሎስ



አንድን ሰው ከልባችን መውደዳችን የሚታወቀው ከራሳችን አብልጠን ስናስተናግዳቸው እንደሆነ ያስተምራል።
3. ቆላስይስ 4:6 .. *«ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን።»* በቅርቡ ወላጆችህ «አይሆንም» ያሉህ መቼ ነበር? ምላሽ በጨው የተቀመመ ነበር ወይስ በእሳት የተቀመመ ነበር? የእግዚአብሔር ቃል ለወላጆቻችን ጥንቃቄ የተሞላበትን ምላሽ እንድንሰጥ ያስተምረናል። ለወላጆቻችን አሉታዊ ወይም ሐሰተኛ ምላሽ መስጠት የለብንም።

*ረ. የመወያያ ጥያቄዎች* (በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ከተወያያችሁ በኋላ፣ እንደገና አንድ ላይ ሆናችሁ ተወያዩ።)
1. ወላጆችን መታዘዝ ሁልጊዜም ቀላል ነውን? ቀላልስ ሆኖ ያውቃል? እግዚአብሔር ወላጆቻችንን እንድንታዘዝ ይፈልጋል? ለምን?
2. ክርስቲያን ወጣቶች ወላጆቻቸውን በማይታዘዙበት ጊዜ ምን ይከሰታል? ይኼ ኃጢአት ነውን?
3. አንድ ክርስቲያን ኃጢአትን ከፈጸመ ምን ማድረግ አለበት?
4. ራስወዳድነት ቤተሰባዊ ችግሮችን ያስከትላል? ለምን?
5. ለወላጆቻችን የምንናገረውና የምንሰጠው ምላሽ አስፈላጊ ነውን? ለምን?
6. የወጣቶች ወላጆቻቸውን አለመታዘዝ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን የሚያገኝበት ጊዜ ሊኖር ይችላል? እንዲህ ዓይነት አለመታዘዞች ትክክል ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ በምሳሌዎች አስረዳ።

*ሰ. መዝጊያ*
የቤተሰብ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያግዙ አንዳንድ መመሪያዎች እነሆ።
1. ታዛዥነት ኃላፊነትህ እንደሆነ አስታውስ። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን እንደ ስርቆትና ነፍስ ግድያ ዓይነት ተግባር እንድትፈጽም እስካልጠየቁህ ድረስ፣ ለወላጆችህ ሥልጣን መታዘዝህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።
2. ልብህን መርምር። ከወላጆችህ ጋር የማትስማማው በራስወዳድነትህ ምክንያት ይሆን?
3. ስለ ችግሩ ከወላጆችህ ጋር ተነጋገር።
4. ታማኝና ቃልህን የምታከብር ሁን። ለወላጆችህ አንድ ነገር አደርጋለሁ ካልህ በኋላ ሌላ ነገር አድርገህ ብትገኝ፣ በቃልህ ላይ እምነት ያጣሉ።
5. ወላጆችህ እንደምትወዳቸው እንዲያውቁ አድርግ። እንደምትወዳቸው ንገራቸው።

በጸሎት ፈጽም።

ምድር ብትናወጥ...
ውኆቻቸውም ሞገዱ ተናወጡም
ፀራሩ፣ **እኔም አምላክ እንደሆንሁ እወቁ**
መዝሙር 46



## ውሳኔዎችን ማሳለፍ

ከዳግ ራንያን

*ሀ. የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና አሳብ .. እግዚአብሔር ክርስቲያናዊ ተቀባይነት ያላቸውን ውሳኔዎች እንድታሳልፍ ይፈልጋል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች የህይወት ግቦቻቸውንና ዓላማዎቻቸውን ለመወሰን በሚፈልጉበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቃል መመልከት እንዳለባቸው ሊያስገነዝባቸው ይገባል። ይህም አስተዋይነት የጎላባቸውን ውሳኔዎች እንዲያሳልፉ ይረዳቸዋል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶች እንደሌላው ችግር ሁሉ ስለ ውሳኔ አሰጣጥም እገዛ ያስፈልጋቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ስለ አንድ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቁ የማይቻል ሊመስል ይችላል። ይህ ትምህርት ወጣቶች የክርስቶስን የሚመስል ውሳኔ እንዲያሳልፉ ያግዛቸዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ለእያንዳንዱ ተማሪ እርሳስና ወረቀት፣ ለመክፈቻ እንቅስቃሴዎች የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. የወጣቶችን አገልግሎት መሪ ምስል ሣሉ - ይህንን ተግባር ሦስት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ አከናውኑት። በአንድ ቡድን ውስጥ ከሚገኙት ሦስት ልጆች አንዱ የመሪውን (ወይም የፈለጋችሁትን የሌላ ሰው) ራስና አንገት በወረቀት ላይ ይሣል። በተመሳሳይ ጊዜ ሁለተኛው ልጅ ከትከሻው እስከ ወገቡ፣ ሦስተኛው ልጅ የተቀሩትን የአካል ክፍሎችና እግሮች በራሱ ወረቀት ላይ ይሣል። (ሁሉም ልጆች የሚሥሉት በተመሳሳይ ጊዜ በየራሳቸው ወረቀት ላይ ይሆናል።) ሦስቱም ሠርተው ሲጨርሱ፣ ወረቀቶቹን ሰብስበህ በማያያዝ ሙሉውን ሥዕል በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ልጆች አሳይ።
2. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው)

ውሳኔዎችን ማሳለፍ የእያንዳንዳችን መደበኛ የህይወት ክፍል ነው። ብዙዎቻችን እነዚህን ውሳኔዎች በእግዚአብሔር ቃል ፈቃድ ተመሥርተን ልናሳልፍ እንሻለን። አንዳንድ ጉዳዮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱ በመሆናቸው ስለነሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ

ማጠቁ ቀላል ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ከዳቦ ቤት ሂሳቡን ሳልከፍል አንድ ዳቦ ይገኤ ልወጣ እችላለሁ? አሥርቱ ትእዛዛት መስረቅን ስለሚከለክሉ ይህንን ሳደርግ አልችልም።

ሌሎች ውሳኔዎች ግን እንደዚህ ቀላል አይደሉም። ለምሳሌ፣ ትምህርቴን መከታተል ያለብኝ አስተማሪ ለመሆን ነው ወይስ ነጋዴ? መጽሐፍ ቅዱስ የትኛው የተሻለ ምርጫ እንደሆነ አይነግረንም። እንደዚህ ዓይነት ውሳኔዎች አስቸጋሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እስኪ እንደዚህ ካሉት ውሳኔዎች አንዱን ቀረብ ብለን እንመርምር።

ወጣቷ ዳልስ ትባላለች። ዳልስ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር ስለምትችል አስተማሪዋ ሌሎች ተማሪዎች የቤት ሥራዎቻቸውን አስተካክለው እንዲሠሩ እንድታግዛቸው ጠየቃት። ይህንን ማድረጉ አንዳንድ ጊዜ ቢያስቸግራትም፣ እሷ የምትረዳቸው ልጆች ከፍተኛ መሻሻል ያሳዩ ጀመር። በዚህ ጊዜ ዳልስ በተማሪዎች የአመራር ካውንስል ውስጥ በመሪነት እንድታገለግል ተጠይቃ ነበር። ካውንስሉ የስብሰባ ዕለቱን እሷ ተማሪዎችን ወደምታስጠናበት ቀን በመለወጡ፣ ዳልስ ችግር ገጠማት። በተማሪዎች ካውንስል ውስጥ መሥራቱ ምስክርነቷን ሊያሳድግ እንደሚችል ታውቅ ነበር። ነገር ግን ጓደኞቿ እንዳይርቋት ስለፈራች ክርስቲያን ነኝ ለማለት አልደፈረችም። ይሁንና የአስጠኚነት አገልግሎቷን ብትቀጥል ምስክርነቷን ልታካፍላቸው ትችል ነበር። ስለ ጉዳዩ ለተወሰኑ ቀናት ካሰበችበት በኋላ ዳልስ በተማሪዎች ካውንስል ውስጥ በመሪነት ማገልገሉን መረጠች። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ በተማሪዎች ካውንስል ውስጥ በመሪነት ለማገልገል ከተመረጠች፣ እግዚአብሔር ለአስጠኚነቱ ሥራ ሌላ ሰው እንደሚያዘጋጅ አሰበች።

*መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው* አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ስለ ዳልስ ችግር ምን ታስባለህ?
2. ዳልስ ትክክለኛ ውሳኔ ያደረገች ይመስልሃል?
3. ዳልስ በምርጫው ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ጥረት አድርጋለችን?
4. ዳልስ ለምክር ወደ አንተ መጥታ ብትሆን ኖሮ፣ ምን ትላት ነበር?

*ሠ. የመጽሐፍ ቅዱስ ግኝት (የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ።)*

1. ሮሜ 12:1-2 — *«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ። እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።»*



የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመረዳታችን በፊት፣

ሀ. ራሳችንን (ነፍሳችንን፣ ሥጋችንን፣ መንፈሳችንን) ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ አሳልፈን መስጠት አለብን።

ለ. ሌሎችን ለመምሰል መሞከራችንን ማቆም አለብን።

ሐ. የክርስቶስን ዓይነት ሕይወት መኖር መጀመር አለብን። የራስወዳድነትን ሕይወት እየኖርህ በሕይወትህ እግዚአብሔር ታላቅን ነገር እንዲፈጽም ልትጠይቀው አትችልም። ሌሎችን እያገለገልህ ዕሰታዊ ሕይወትህን ለርሱ እንድትኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ለመንግሥቱ የሚጠቅመው ምርጫህ የትኛው እንደሆነ እግዚአብሔርን ልትጠይቀው ትችላለህ።

2. ቆላስይስ 1:9-12 — *«ስለዚህ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ጊዜ ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን እንዲሞላባችሁ እየለመንን፣ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም። በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ፣ በእግዚአብሔር እውቀት ሁሉ እያደጋችሁ፣ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፣ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፣ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።»*

ፊልጵስዩስ 2:3-5፣ 7፣ 8 — *«ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር። እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን... [እርሱ] ራሱን ባዶ አደረገ፣ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።»* ትሑታንና ታዛዦች፣ ሌሎችንና ፍላጎቶቻቸውን የምናስቀድም መሆን አለብን። በባሕርይና በተግባር ክርስቶስን በመምሰል እግዚአብሔርን የማስደሰት ዓላማ ካለህ (2ኛ ቆሮ. 5:9)፣ ውሳኔዎችህን ከዚሁ ዓላማ አንጻር ልታከናውን ትችላለህ። እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ መልካም ከሆነውና ከዚያ ከላቀው ነገር መካከል አንዱን እንድንመርጥ ያደርገናል።

*ረ. የመወያያ ጥያቄዎች* (በቡድኖች ተከፋፍለው ወይም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምን ያስተምሩሃል?
2. አኗኗራችን በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳናውቅ የሚያደርገው እንዴት ነው፡
3. ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ቁርጥ ያለ ነገር አለ? ያልሆነስ?

4. በራሳችን አስተሳሰብ ውሳኔዎችን የመስጠት ነጻነት አለን?
5. የክርስቲያን የምርጫ ዘዴ ክርስቲያን ካልሆኑት ሰዎች የሚለየው እንዴት ነው?
6. የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት እናውቃለን?

ሰ. መዝጊያ (ለተማሪዎች እርሳስና ወረቀት አድል።)

1. ህይወትህ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዙሪያ ያመከለ ነውን?
2. የምትኖረው ለራስህ ብቻ ነው ወይስ ሌሎችንም እያገለገልህ?
3. ባሕርይህ ከክርስቶስ ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው? ትሑት፣ ታዛዥ፣ የሌሎችን ፍላጎቶች ከራስህ የምታስቀድም ነህን?
4. የበለጠ ክርስቶስን እንድትመስል በሕይወትህ ውስጥ መለወጥ ያለባቸውን ነገሮች ዘርዝር።
5. ልታሳልፋቸው የሚገባህን ውሳኔዎች ዘርዝር። እነዚህን ውሳኔዎች ሌሎችን በማገልገል ክርስቶስን ከማገልገሉ ዓላማ ጋር አነጻጽር።

እግዚአብሔር እነዚያን ውሳኔዎች በማስተላለፉ በኩል እንዲረዳን በጸሎት እንጠይቀው።

**በእኔ ብትኖሩ**
**ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ**
**የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ**
**ይሆንላችሁማል።**

ዮሐንስ 15:7



## ሌሎች በኛ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መቆጣጠር

ከሱዚ. ሽለንበርገር

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. እግዚአብሔር ህይወትህን ለመቆጣጠር ይፈልጋል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች እግዚአብሔር እንዲሆን የሚፈልጋቸውን የመሆን ድፍረት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ሌሎች የሚያስከትሉት ተጽዕኖ በወጣቶችህ ቡድንህ ውስጥ ባሉት ሰዎች ሁሉ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ለዚህ ችግር መፍትሔ ለመስጠት የሚወስዱት እርምጃ የወደፊት ማንነታቸውን ሊወስን ይችላል።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. ቁጭ .. ብድግ። ሁሉም ወጣቶች ተነሥተው እንዲቆሙ አድርግ። የሚከተለውን ዓረፍተነገር ስታነብና ዓረፍተነገር ለነሱ እውነት ሲሆን ቁጭ ይላሉ። ሌላ ዓረፍተነገር ስታነብና (ከተቀመጡ በኋላ) እሱም ለነሱ እውነት ከሆን ተነሥተው ይቆማሉ። ስለሆነም፣ ዓረፍተነገሮቹ እውነት እንደሆኑላቸው ያህል ሲቀመጡና ሲነሡ ይቆያሉ።
   1) ወደዚህ የወጣቶች ስብሰባ የመጣኸው ግዴታ ስለሆነበህ ነው። 2) ትምህርት ቤት የምትሄደው በንደኛህ ግፊት ነው። 3) ባለፈው ሳምንት በራስህ ፍላጎት ሳይሆን በሌላ ሰው ገፋፊነት አንድ ነገር አድርገሃል። 4) ዛሬ አንድ ጓደኛህ አንድ የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ ገፋፍተኸዋል። 5) በዚህ ወር ውስጥ ሌላ ነገር ለማድረግ ስትል ከቤተክርስቲያን ቀርተሃል። 6) ዛሬ ከአንድ ብርጭቆ በላይ ቀዝቃዛ ነገር ጠጥተሃል። 7) ባለፈኸው ሳምንት ባልተናገርሁ ብለህ የተጸጸትህበትን ነገር ተናግረሃል። 8) ለነገው ትምህርት ቤት የቤት ሥራህን አላጠናቀቅህም። 9) ትናንት የሆነ ቦታ ለመሄድ ስለቸኮልህ አልጸለህይም።
2. ተጽዕኖ። ከስብሰባው በፊት ይህን ጨዋታ ለማካሄድ እንደዲያግዙህ አራት ወጣቶች ምረጥ። ስብሰባው በሚጀመርበት ጊዜ ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንድ ፈቃደኛ ወጣት ጠይቅና ቀደም ሲል ከመረጥሃቸው አራት ወጣቶች ጋር ወደ ውጭ እንዲወጣ አድርግ። ቀደም ሲል የመረጥሃቸው አራቱ የጨዋታ ዕቅድህን ያውቃሉ።

አምስተኛው ልጅ ግን አያውቅም። ከቡድኑ አባላት አንዳንዶቹ ጫማዎቻቸውን (ወይም ሌላ ነገር) አውልቀው ከክፍሉ ፊት ለፊት እንዲከምሩ አድርግ። የተከመሩትን ጫማዎች ቁጠር። ወደ ውጭ የሄዱት ልጆች ወደ ክፍሉ እንዲመጡ ጥራቸው። በፍጥነት የተከመሩትን ጫማዎች እንዲቆጥሩ ጠይቃቸው። (በ30 ሰከንዶች ውስጥ ጫማዎቹን ቆጥረው እንዲጨርሱና ከዚያ በኋላ ወደ ጫማዎቹ እንዳይመለከቱ ጠይቃቸው።) ከስብሰባው በፊት የመረጥሃቸው አራቱ ልጆች በተገኘው የጫማ ቁጥር ላይ አንድ ቁጥር መደመር እንዳለባቸው ያውቃሉ። ለምሳሌ፣ የቆጠሯቸው ጫማዎች አሥር ከሆኑ፣ አሥራ አንድ ብለው ይመልሳሉ ማለት ነው። የዚህ ጨዋታ ዓላማ አምስተኛው ግለሰብ ምን እንደሚል ለማወቅ ነው። ጫማውን ቆጥሮ አሥር መሆናቸውን ያውቃል። አሥር ጫማዎች እንዳሉ በመግለጽ ከሌሎቹ የተለየ አቋም ይይዛል ወይስ እንደ ሌሎቹ እሱም አሥራ አንድ ብሎ ይመልሳል? ጨዋታው ሰወጣቶች ሌሎች ሰዎች እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩብን ለማሳየት የታቀደ ነው።

3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው)

ዮሴፍ ከአሥራ ሁለት ልጆች መካከል አሥራ አንደኛው ነበር። ወንድሞቹ ከሱ ስለሚበልጡ ዮሴፍ ገና ከቤት ሳይወጣ በመስኮች ላይ ይሠሩና የአባታቸውን በጎች ይጠብቁ ነበር። የዮሴፍ አባት የሆነው ያዕቆብ ከቤት የሚውል ልጅ ስላለው ደስተኛ ነበር። ከዮሴፍ ጋር መጫወትና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሲሄድ መመልከት ያስደስተው ነበር። ዮሴፍ ያዕቆብ እንደገና የወጣትነት ስሜት እንዲሰማው ረዳው። ያዕቆብ ዮሴፍን በጣም ከመውደዱ የተነሣ አዲስ ኮት ገዛለት። ኮቱ በህብረቀለማት ያሸበረቀና በውድ ዋጋ የተገዛ ልዩ ዕቃ ነበር። ይህም የዮሴፍን ወንድሞች አስቀናቸው። ዮሴፍ ወደ ሥራ ሳይሄድ ከቤት ቁጭ ብሎ እየዋለ ግሩም ኮት መሸለሙ ትክክል አይደለም ብለው አሰቡ።

ዮሴፍ እንግዳ የሆኑ ሕልሞች የሚያይ ሰው ነበር። አንድ ቀን ቤተሰቡ እንደሰገዱለት፣ ነዶ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሄዱ ጊዜ የሱ ነዶ ከሌሎቹ ሁሉ በቁመት ልቆ እንደሚገኝ ማለሙን ተናግሯል። ዮሴፍ ሁልጊዜም ሕልሞቹን ለወንድሞቹ ይነግራቸው ነበር። አንድ ቀን አሥሩ ታላላቅ ወንድሞቹ በሕልሞቹ ምክንያት ተበሳጩ። በዚህም ጊዜ ዮሴፍ በህብረቀለማት ያሸበረቀ ኮቱን ለብሶ ሲመጣ አዩት። በዚህ ጊዜ ዮሴፍን ገፍተው ጉድጓድ ውስጥ ከተቱት።

ዮሴፍን ለመጉዳት የፈለጉ ወንድሞቹ በሙሉ አልነበሩም። ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ ከልባቸው የሚጠሉት ፡ ዮሴፍን የሚወዱት ወንድሞቹ በጥላቻ የተሞሉ ወንድሞቻቸውን ተጽዕኖ ለመቋቋም ባለመቻላቸው



የከፋ ድርጊታቸው ተሳታፊዎች ሆኑ። ወንድሞቹ በመጨረሻው ዮሴፍን ከጉድጓድ አወጡት። ውብ ኮቱን በፍየል ደም አሰነከሉ። ከዚያም ዮሴፍን ለባሪያ ነጋዎች ሸጡት።

ዮሴፍ ወደ ግብጽ ተወሰደ። በዚያም ጲጥፋራ ለተባለ ሰው በባርነት ተሸጠ። የጲጥፋራ ቤተሰብ ዮሴፍን በጣም ስለወደዱት በጥሩ ሁኔታ አስተናገዱት። እንዲያውም የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ስላፈቀረችው ከሱ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ፈለገች። ዮሴፍ ግን ከዚህ የበለጠ ጠንካራ ፍላጎት ነበረው። ዮሴፍ ትክክለኛ ባልሆኑት ሰዎች ተጽዕኖ የማይንበረከክ ቅዱስ ወጣት ለመሆን ፈለገ። ዮሴፍ የፈለገችውን ስላላደረገላት የጲጥፋራ ሚስት በቁጣ ጦፈች። በመሆኑም ልብሷን ቀዳ ዮሴፍ አስገድዶ ሊደፍራት እንደፈለገ ለባሏ ተናገረች። ጲጥፋራም ዮሴፍን አሳሰረው። ዮሴፍ ላልፈጸመው ጥፋት በእንግድነት አገር ውስጥ ታሰረ!

ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ሰዎች ዮሴፍ ሕልም መፍታት እንደሚችል አወቁ። ከንጉሡ ሕልሞች አንዱን በፈታ ጊዜ፣ ንጉሡ ከወኅኒ ቤት አስወጥቶ በቤተመንግሥት ውስጥ ሾመው።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. በዮሴፍ ቦታ ላይ ብትሆን ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል? ወንድሞችህ ጉድጓድ ውስጥ ቢከቱህ፣ በጲጥፋራ ሚስት ብትፈተን፣ በቤተመንግሥት ውስጥ ብትሠራ...
2. ከዮሴፍ ወንድሞች አንዱ ብትሆን ስለ ዮሴፍ ኮት ምን ይሰማሃል? ስለ ሕልሞቹስ? ያዕቆብ ለሚያደርግለት እንክብካቤ?
3. የሚከተሉትን ሰዎች ከጥሩነት ወደ መጥፎነት በቅደምተከተል አስቀምጥ። ቅደምተከተሉን ከሠራህ በኋላ፣ የመጀመሪያው ከሁሉም የተሻለ፣ የመጨረሻው ከሁሉም የከፋ ይሆናል ማለት ነው። ዮሴፍ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍን ለመጉዳት የፈለጉት ወንድሞቹ፣ ዮሴፍን ለመጉዳት ያልፈለጉት ወንድሞቹ፣ ባሪያ ነጋዎች፣ የጲጥፋራ ሚስት። ለመልስህ ማብራሪያ ስጥ።
4. በዚህ ታሪክ ውስጥ በሌሎች ተጽዕኖ የማይፈልገውን ያደረገው ማነው? ሁኔታውን በጥሩ ሁኔታ የተቆጣጠረው ማነው? ይህንኑ ያላደረገውስ?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንብቡና ተወያዩባቸው።)

እስኪ ሌሎች ሰዎች በኛ ላይ የሚያሳድሯቸውን ተጽዕኖዎች ስለመቆጣጠር የሚናገሩትን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንመልከት።

1. ማቴዎስ 6:25፣ 33 - አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ቁሳዊ ነገሮችን በተመለከተ ተጽዕኖ ያሳድሩብናል:: ይህም አዲስ ፋሽን ልብስ መልበስ፣ ከታዋቂ ሰዎች ጋር አብሮ መታየትና የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ ሊሆን ይችላል:: ችግሩ የሚከሰተው እነዚህ ነገሮች ከመንፈሳዊ ነገሮች በላይ ተፈላጊዎች ሆነው ሲገኙ ነው:: እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገው ሰዎች እንድናደርግ ከሚፈልጉት መብለጥ አለበት::
2. ሮሜ 12:1-2 - አንዳንድ ጊዜ ተጽዕኖ ሊያሳድሩብን ወይም የማንፈልጋቸውን ነገሮች እንድናደርግ የሚገፋፉን ሰዎች ያጋጥሙናል:: የነዚህን ሰዎች ምክር መስማት የለብንም:: በኛ ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ልንቋቋም እንችላለን:: እግዚአብሔር በዚህ ዘመናዊ ዓለም ውስጥ እንዳሉት ሰዎች እንዳንሆን ይፈልጋል:: ይልቁንም መለወጥ አለብን:: እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ የሚከሰተው ሁሉንም ነገር ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈን በምንሰጥበት ጊዜ ነው::
3. 1ኛ ተሰሎንቄ 5:23-24 - ሁሉንም ነገር ለኢየሱስ ክርስቶስ ብንሰጥ፣ እግዚአብሔር ሌሎች የሚያደርሱብንን ተጽዕኖዎች እንድንቋቋም ይረዳናል:: እግዚአብሔር አንድ ሰው አንድን ነገር እንድናደርግ በሚያስገድደን ጊዜ ዝም ብሎ አይመለከትም:: በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ወደኛ የሚመጡትን ፈተናዎችና ችግሮች የምናሸንፍበትን ኃይል እንደሚሰጠን ቃል ገብቷል:: በፍጹም ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አያደርግም:: እግዚአብሔር እጅግ በከፋት ሁኔታዎች ውስጥ ሳይቀር በቅድስና የምንመላለስ ወጣቶች እንድንሆን የሚፈልግ ሲሆን፣ በዚህም ሁሉ እንደሚረዳን ቃል ገብቶልናል:: ለፈተና ራሳችንን አሳልፈን ልንሰጥ አይገባንም:: እግዚብሔርን በመታዘዝ በድልነሺነት ልንመላለስ እንችላለን::

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (በቡድን ተከፋፍለው ወይም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ::)

1. ሌሎች ሰዎች ሁልጊዜም ተጽዕኖ ያሳድሩብናል? ለምን?
2. እግዚአብሔር ልጆቹ ለሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ ምን ዓይነት ምላሽ እንዲሰጡ ይጠብቃል?
3. ድልነሺ ክርስቲያኖች ሆነን ለመኖር ከፈለግን ምን ልናደርግ ይገባናል?
4. ሁሉንም ነገር ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈን ብንሰጥ፣ የሌሎች ሰዎችን ተጽዕኖ እንድንቋቋም የሚረዳን እንዴት ነው?

ሰ. መዝጊያ

በሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ በምትፈተንበት ጊዜ ሊረዱህ የሚችሉ አንዳንድ ነጥቦች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል::



1. ጓደኞችህ እንድታደርግ የሚፈልጉትን ከማድረግህ በፊት፣ ተግባርህ ምን ዓይነት ውጤቶችን እንደሚያስከትል አስብ::
2. ያንን ተግባር ማድረግህ ክርስቲያናዊ ምስክርነትህን ይጎዳዋል? ከእግዚአብሔር ጋር ያለህንስ ግንኙነት ይጎዳዋል?
3. ጓደኞችህ የፈለጉትን በሉ፣ ትክክል ነው ብለህ ያላመንሃቸውን ነገሮች አታድርግ::
4. የሌሎች ሰዎችን ተጽዕኖ ለመቋቋም ቆራጥነትን ይጠይቃል:: ነገር ግን ክርስቲያኖች ሊያደርጉት የሚገባው ይህንኑ ነው::
5. ሁኔታው አስቸጋሪ ከሆነብህ በጸሎት ለጌታ አሳልፈህ ስጥ:: እርሱም የሰዎችን ፈተናና ተጽዕኖ የምትቋቋምበትን ብርታት ይሰጥሃል::
6. ሃላፊነት የሚሰማህ ሰው እንድትሆን የሚያግዝ፣ የሚያበረታታና የሚጸልይልህ ጓደኛ አብጅ::

## ቅድስና፡ የራሴን ወይም የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል

ከአለን ስኮት

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የቅድስና ህይወት መኖር ማለት በእግዚአብሔር እርዳታ ለሰዎችና ለሁኔታዎች እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ምላሽ ለመስጠት መወሰን ነው።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ቅድስና በሁሉም የህይወት ክፍሎች እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ነገሮች ማከናወን እንደሆነና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እግዚአብሔር እንደሚያግዛቸው ለወጣቶች ማስተማር።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶች በየቀኑ በዙሪያቸው ላሉት ሰዎች ምላሽ ለመስጠት ውሳኔዎችን ይሰጣሉ። ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ፍቅርና ገደድ የሚያሳዩት ሰዎች ከሚያሳድሩባቸው ተጽዕኖዎች፣ ከሚያሳድሩባቸው ስሜቶች፣ ወይም ከተወሰነ ሁኔታ አንጻር ነው። ህይወቱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፎ ለመስጠት የሚፈልግ ወጣት በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ምላሽ ለመስጠት ይወስናል። ይህም ሁለንተናዊ ቅድስና የምንለው ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ወጣቶች በእግዚአብሔር እርዳታ ሌሎች ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ተጽዕኖዎች በሚሰጧቸው ምላሾች ላይ ለውጥ እንዲያስከትሉ አያደርጉም። «እግዚአብሔር ሆይ፣ ለዚህ ሁኔታ ምላሽ የምትሰጠው እንዴት ነው?» ብለው ይጸልያሉ። ከዚያም በእግዚአብሔር ብርታትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ትክክለኛውን ተግባር ያከናውናሉ።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. መጽሐፍ ቅዱሶች፣ ወረቀት፣ እርሳሶች ወይም እስክብሪቶዎች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. የክፍሉን ወጣቶች በቡድን ከፋፍል። የቡድኑ አባላት ቁጥር በጠቅላላው የአባላት ቁጥር የሚወሰን ይሆናል። (በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ቢያንስ ከ4-5 ወጣቶች ሊኖሩ ይገባል።) ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ወረቀትና አንድ እርስሳስ እድል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ሰው ወደ መሪው በመሄድ ቡድኑ ምን እንደሚሥል ይሰማል። (ለምሳሌ፣ ካልሲ፣ ቅርጫት፣ ጫጩት፣ ዛፍ፣ ወዘተ.) ከየቡድኑ ወደ መሪው የሄዱት ሰዎች ምን እንደሚስሉ ከሰሙ በኋላ



ወደ ቡድኑ ሩጠው በመመለስ የታዘዙትን ይሥላሉ። ምንም ዓይነት ቃላት መናገር ወይም መጻፍ የለባቸውም። በመጀመሪያ የተሣለውን ነገር የገመተ ቡድን ነጥብ ያገኛል።

2. የምትወደኝ ከሆነ ፈገግ በልልኝ። ሁሉም ክብ ሠርተው እንዲቀመጡና አንድ ሰው እንዲመርጡ አድርግ።

የተመረጠው ሰው ከክቡ መሀል ተቀምጦ አንድ ሰው ፈገግ እንዲልለት ማድረግ አለበት። ፈገግ ያለው ሰው ወደ ክቡ መሀል በመሄድ ያስፈገገውን ግለሰብ ቦታ ይወስዳል። እሱም በተራው በክቡ ዙሪያ ወዳሉት ሰዎች በየተራ እየሄደ፣ «የምትወደኝ ከሆነ እባክህን ፈገግ በልልኝ» በማለት ምላሽ ለማግኘት ይጥራል። (ፈገግ ለማስባል የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል።) የተጠየቀው ሰው ከክቡ መሀል ወዳለው ግለሰብ በመመልከት፣ «እወድሃለሁ። ግን ፈገግ ማለት አልችልም» ሲል ሳይስቅና ፈገግ ሳይል ይመልስለታል። መሀል ላይ ያለው/ያለችው ልጅ ግን ጥረቱን መቀጠል ይኖርበታል/ባታል።

3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (የሚከተለውን መረጃ በራስህ አገላለጽ ለቡድንህ አካፍል።)

ለማን ጥሩዎች መሆን እንዳለብን የምንወስነው እንዴት ነው? በአንድ በተወሰነ ቀን፣ ጊዜ ልናሳልፍ የምንችለው ከጥቂት ሰዎች ጋር ብቻ ነው። ይህም ከማን ጋር ማሳለፍና እነዚህን ሰዎች እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባን መምረጥ እንዳለብን ያመለክታል። የሚከተለው ታሪክ በአካባቢያችን ላሉት ሰዎች ምላሽ ልንሰጥ የምንችልባቸውን የተለያዩ መንገዶች ያሳያል።

ናትናኤል፣ አለን፣ ግሪግና ሻን በአንድ የእግር ኳስ ቡድን ውስጥ ይጫወታሉ። በቡድኑ ውስጥ ናትናኤል ከሁሉም የላቀ ችሎታ ያለው ተጨዋች ነበር። ከጨዋታ ችሎታው በተጨማሪ ናትናኤል በትምህርቱም ጎበዝ ነበር። አለን ጎበዝ ተማሪ አልነበረም። ሁልጊዜም የማይችለውን ነገር ለማከናወን የሚጥር ሰው ይመስል ነበር። ብዙ ጓደኞችም አልነበሩትም። ግሪግና ሻን በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ልጆች ነበሩ። በቡድኑ ውስጥ እንዴት በተሻለ ሁኔታ ሊጫወቱ እንደሚችሉ ስላሳያቸው ናትናኤልን ይወዱታል። ከሌሎች የናትናኤል ጓደኞች ጋር አብሮ መሆኑም ያስደስታቸዋል።

አንድ ቀን መሪያቸው ቡድኑ ለአራት ሳምንታት የእግር ኳስ ጨዋታ ልምምድ እንደሚያደርግ አስታወቀ። መጫወት ሲጀምሩ፣ አለን ከዚህ በፊት የእግር ኳስን ጨዋታ አይቶ እንደማያውቅ ተረጋገጠ። በዚህም ጊዜ ናትናኤል መሪው ራቅ በሚልበት ጊዜ በአለን ላይ ይቀልድና ይስቅ ጀመር። ብዙም ሳይቆይ ሌሎም ልጆች በአለን ላይ መሳቅ ጀመሩ። ግሪግ ቀልዶቹ ለጨዋታ ጥሩዎች ቢሆኑም አለንን ሊጎዱት እንደሚችሉ

ተገነዘበ። የናትናኤልን ጓደኝነት ለማጣት ስላልፈለገ፣ ግሪግ በአለን ላይ እንዳይቀልድ ለማረግ ሞከረ።
ሻንም ቢሆን በአለን ላይ መቀለዱ ተገቢ ነው የሚል ግምት አልነበረውም። በዚህ ጊዜ ሁኔታውን ዝም ብሎ ቢመለከት አለን የበለጠ እንደሚጎዳም ተገነዘበ። ስለሆነም፣ አለን የናትናኤልን ጓደኝነት ለማጣት ቆርጦ ወደ አለን በመሄድ እንዴት እንደሚጫወት ለማሳየት ወሰነ። አለንም ረዳት በማግኘቱ ደስ ተሰኘ።

*መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)*
በነዚህ ጥያቄዎች አማካኝነት የቡድንህ አባላት በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ያሳለፏቸውን ውሳኔዎች እንዲገመግሙ አድርግ።
1. እነዚህ ልጆች እያንዳንዳቸው ለአለን እንዲህ ዓይነት ምላሽ የሰጡት ለምን ይመስልሃል?
2. አንተ በግሪግ ወይም በሻን ቦታ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?
3. ሻን አለንን በመርዳቱ የናትናኤልን ስሜት የጎዳው ይመስልሃል? ለምን?
4. ከነዚህ አራት ልጆች አንዱን ለቡድንህ ለመምረጥ ብትፈልግ ማንን ትመርጣለህ? ለምን?

*ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)*
ሉቃስ 10:25-37 አንብብ። በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ ክርስቶስ ለማን መቆም እንዳለብን ስለመወሰን ይናገራል። እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን ልንወድና ሌሎችንም እርሱ እንደሚወዳቸው መውደድ እንዳለብን ያስተምራል። ሰዎቹ በዚህ መንገድ ማንን መውደድ እንደሚገባቸው ጠየቁት። እርሱም ሊወደድ የሚገባውን ሁሉ መውደድ እንዳለባቸው ገለጸላቸው። ይህ ፍቅር ደጉ ሳምራዊ ጊዜውንና ገንዘቡን ቢያስከፍለውም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን እንዲመሠርት አድርጎታል። የተቀደሰ ክርስቲያን በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ እንደ ሰው ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ለመውደድ ይመርጣል።

*ረ. የቡድን መወያያ ጥያቄዎች*
1. ይህ ታሪክ ከማን ጋር እንደምንወዳጅ ስለ መምረጥ ምን ያስተምረናል?
2. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ከእነ አለን ቡድን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?



3. ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካነበብህ በኋላ፣ በእነ አለን የጨዋታ ቡድን ውስጥ ብትሆን ኖሮ እግዚአብሔር ምን እንድታደርግ የሚፈልግ ይመስልሃል?
4. ክርስቶስ ሳምራዊው እንዳደረገው እንድናደርግ የሰጠንን ትእዛዝ ላለመፈጸም የሚያስችሉ ማመካኛዎች አሉን? ካሉ፣ ጥቂቶቹን ዘርዝር።
5. ባልንጀራችን ማነው? (መልስ: እርዳታችንን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው።)

*ሰ. መዝጊያ*
ስብሰባውን ከማጠቃለልህ በፊት፣ ወጣቶቹ በወረቀት ላይ አንድ ክብ እንዲሥሉ ጠይቃቸው። ከክቡ ውስጥ የቅርብ ጓደኞቻቸውን ስሞች፣ ከክቡ ውጭ የሌሎች ጓደኞቻቸውንና የሚያውቋቸውን ሰዎች ስሞች ይጻፉ። ሥለው ከጨረሱ በኋላ እንደ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ማንን ወደ ክቡ መሀል እንድናመጣ እንደሚጠይቅ ሁልጊዜም መጠየቅ እንዳለብን ግለጽላቸው። የተቀደሰ ህይወት መምራት አዳዲስና ችግር ያለባቸውን ሰዎች ወደ ክቡ መጋበዝን ይጠይቃል። በመዝጊያ ጸሎቱ ወቅት እያንዳንዱ ወጣት የጓደኝነት ግንኙነቶቹን ለእግዚአብሔር አሳልፎ እንዲሰጥ አበረታታቸው። እግዚአብሔር እንዲወዷቸው የሚፈልጋቸውን ወገኖች ሁሉ እንዲወዱ ጠይቃቸው። መንፈስ ቅዱስ እንደ ክርስቶስ ሰዎችን የሚወዱበትን ኃይል እንዲሰጣቸው ጸልይላቸው።



## ውርጃ: የህይወትና የሞት ጉዳይ!

ከሚካኤል ኤ. ፐትስ

*ሀ. የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና አሳብ .. ውርጃ ዛሬ በዓለም ውስጥ በዋንኛነት ከሚታዩት ችግሮች አንዱ ነው:: ስለሆነም፣ ወጣቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ/ክርስቲያናዊ የውርጃን ጽንሰአሳብ እንዲገነዘቡ መርዳቱ ጠቃሚ ነው::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ክፍል መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የህይወት አቋምና ቅድስና ያሳያል:: ትምህርቱ ወጣቶች በውርጃ ጥያቄ ላይ የክርስቲያን አቋም ምን ሊሆን እንደሚገባ የበለጠ በግልጽ ያሳያል::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. የብዙ አገሮች ህጎች አዋቂዎች በተረገዘው ልጅ የወደፊት መኖር ወይም አለመኖር ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት እንዳላቸው ያስረዳል:: ሰዎች እርግዝናው ችግሮችን እንደሚያስከትል ወይም ከራሳቸው ግላዊ ዓላማዎች ጋር እንደሚጣረስ ወይም እንዲሁ የልጁን መወለድ ካልፈለጉ፣ ውርጃን በመፍትሔነት ይጠቀማሉ:: ውርጃ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎች ህይወት ክቡርነት የሚያስተምረውን እውነት ይቃረናል:: ጽንስ ከተከሰተ በኋላ ከማስወረድ ይልቅ፣ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ይቻላል:: ሰዎች እርግዝናው ከመከሰቱ በፊት ኃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ ሊወስኑ ይገባል::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ጥቁር ሰሌዳ ወይም ሰፊ ወረቀት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ መቀሶች፣ ኮላ ወይም ሌላ ማያያዣ ነገር::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. ከመጽሔት በተገኘ ሥዕል የተሳለ ሰው:: ቡድኑን ከ3-5 አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ከፋፍል:: ለእያንዳንዱ ቡድን መጽሔቶች እና/ወይም ጋዜጦች፣ ሰፋፊ ወረቀቶች፣ መቀሶችና ኮላ/ማያያዣ አድል:: ቡድኖች በመጽሔቶቹ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ሥዕሎች እጆች፣ እግሮች፣ ራሶች፣ ወዘተ. በመጠቀም ራሳቸውን እንዲሥሉ 10 ደቂቃ ያህል ስጣቸው:: ሥራውን ከፈጸሙ በኋላ፣ ቡድኖቹ በየተራ የሣሉት ሰው ለምን ለዓለም ይጠቅማል ብለው እንደሚያስቡ እንዲያብራሩ 60 ሰኮንድ ወይም ከዚያ ያነሰ ጊዜ ስጣቸው::
2. የቡድን ዝማሬ:: ትምህርቱ በሚቀርብበት ጊዜ ቡድኑ በጸጥታ ማዳመጥ ይኖርበታል:: ከዚያ በፊት እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ፍቅር የሚወስ አዝማቾችን ዘምሩ::



የተለያዩ ሰዎች ውርጃን እንደሚፈጽሙ ሁላችንም እናውቃለን:: ብዙዎቻችችሁ ስለ ውርጃ የተወሰነ ግንዛቤ ይኖራችኋል:: አንዳንዶቻችሁ ስለዚህ ጉዳይ ግልጽ ግንዛቤ ላይኖራችሁ ይችላል:: በዚህ ትምህርት የክርስቲያን ኃላፊነት ምን መሆን እንዳለበት እንመለከታለን::

የስታስቲክስ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ብዙ ያላገቡ ሴቶች በየዓመቱ ያረግዛሉ:: ከነዚህም መካከል አብዛኞቹ ውርጃን በመፍትሔነት ይጠቀማሉ:: ትምህርት ከመጨረሳችሁ በፊት፣ አንዲት የምታውቁት ልጅ አርግዛ የማስወረዷ እድል ሰፊ ነው:: ማስወረድ (ውርጃ) ማለት አንድን ጽንስ የሚወለድበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ከእናቱ ማኅፀን ማስወገድ ማለት ነው:: ዋናው ጥያቄ፣ «ህይወት የሚጀምረው መቼ ነው?» የሚል ይመስላል:: ህይወት የሚጀምረው ልጁ በተፀነሰ ጊዜ ነው ወይስ ሲወለድ? (መፀነስ ማለት የወንዱ አባለዘር ከሴቷ እንቁላል ጋር የሚዋሃድበት ጊዜ ነው::) ብዙዎች ህይወት ከፅንስ እንደሚጀምር ያምናሉ:: ሳይንሳዊ መረጃዎችም እነዚህን ድምዳሜዎች ያግዛሉ:: አንድ ልጅ ከተፀነሰ በኋላ ከ12 እስከ 28 ቀናት ውስጥ ልቡ መምታት ይጀምራል:: ከአራት እስከ ስድስት ሳምንታት ውስጥ የተፀነሰውን ልጅ የአእምሮ ሞገዶች (brain waves) መለካት ይቻላል:: በስምንተኛው ሳምንት አጥንቶቹ፣ አሻራዎቹ፣ የደም ዑደቱና የጡንቻ ሥርዓቱ ይሟላል::

እስኪ የሚከተለውን ሁኔታ እንመልከት:: ማንዲ አንተ በምትማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ የምትገኝ ተማሪ ነች:: ምንም እንኳዋን ለአያሌ ዓመታት በተመሳሳይ ክፍሎች ውስጥ በተመሳሳይ መምህራን አብራችሁ ብትማሩም፣ ከልጅቱ ጋር ጓደኛሞች አልነበራችሁም:: ላለፉት ጥቂት ወራት ካሜሩን ከሚባል ልጅ ጋር ፍቅር መሥርታለች:: ዛሬ ጠዋት፣ ማንዲ ካንተ ጋር ለመነጋገር መፈለጓን ትነግርሃለች:: እንደምታምንህና ካላንተ ማንም የሚረዳት እንደሌለ በመግለጽ እያለቀሰች ችግሯን ታጫውትሃለች:: ችግሯም ማርገዟ እንደሆነ ትገልጽልሃለች::

ማንዲ ካሜሩንን በጣም እንደምትወደውና ዳሩ ግን እንደማታፈቅረው ትናገራለች:: ወደ ዩኒቨርስቲ ገብታ ዶክተር የመሆን ዕቅድ እንዳላትም ትገልጽልሃለች:: ካምሩንን ማግባቱንም ሆነ ልጅ መውለዱን አትፈልግም:: እነዚህ ነገሮች ዶክተር የመሆን ዕቅዷን ያጨናግፉባታል:: ከዚያም ፅንሱን ለማስወረድ እያሰበችበት እንደሆነ ትጠቁምሃለች:: ትክ ብላ ወደ አንተ በመመልከት፣ «ምን ማድረግ ያለብኝ ይመስልሃል?» ስትል ትጠይቅሃለች::

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ::)

1. አንተ በማንዲ ቦታ ብትሆን ምን ይሰማሃል?
2. ማንዲ ምን አማራጮች ያሏት ይመስልሃል?

3. ማንዲ ፅንሷን ለማስወረድ ከወሰነች ይህንን እንድታደርግ የሚያስገድዷት ምክንያቶች ምን ምን ይሆናሉ?
4. የማንዲ ጓደኛ ብትሆን ምን ምክር ትሰጣታለህ? ለምን?
5. እንደ ማንዲ ያሉ ልጆች ውርጃን የሚመርጡት ለምን ይመስልሃል?
6. ማስወረድ እንደ ማንዲ ባሉት ሴቶች ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ የሚያስከትል ይመስልሃል?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (ወጣቶቹን በአነስተኛ ቡድኖች ከከፋፈልሃቸው በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማደል እንዲያነቧቸው አድርግ።)
እስኪ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች በመመርመር መጽሐፍ ቅዱስ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ትምህርት እንመልከት።

| | |
|---|---|
| 1. ሉቃስ 1:41<br>2. መዝሙር 22:9-10<br>3. ፍጥረት 25:21-24<br>4. ኤርምያስ 1:45 | እነዚህ ምንባቦች ህይወት የሚጀምረው ልጁ በሚወለድበት ጊዜ ሳይሆን በፅንስ ጊዜ እንደሆነ ያስረዳሉ። |
| 5. ኢሳይያስ 44:2<br>6. ዘጸአት 21:22-25<br>7. መዝሙር 139:13-16 | እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር ከመወለዳችን በፊት በህይወታችን ውስጥ በትጋት እንደሚሠራ ያስተምራሉ። |
| 8. ዘፍጥረት 1:26<br>9. መዝሙር 119:73<br>10. መዝሙር 127:3 | እግዚአብሔር ለሰው ሕይወት በሚሰጠው ዋጋ ላይ የሚነሣ ጥያቄ አለን? የለም |



ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)
1. ህይወት የሚጀምረው መቼ ነው? በማህፀን ውስጥ ነው ወይስ ልጁ ለመጀመሪያ ጊዜ አየር በሚስብበት የልደት ጊዜ?
2. በእግዚአብሔርና ገና ባልተወለደ ፅንስ መካከል የሚካሄድ ግንኙነት አለን? እግዚአብሔር በህይወታችን ውስጥ ጣልቃ የሚገባው ከመወለዳችን በፊት ነው ወይስ በኋላ?
3. ውርጃ እግዚአብሔርን ያሳስበዋል? ለምን? እግዚአብሔር በሰው ልጅ ህይወት ላይ ያኖረው ዋጋ ምን ያህል ነው?
4. ይህንን ክፍለጊዜ ወደጀመርንበት ሁኔታ መለስ ብለህ አስብ። በትምህርት ቤት የምታውቃት ልጅ እንዲህ ዓይነት ችግር እንደደረሰባት አጫውታሃለች እንበል። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው አንጻር ምን ዓይነት ምክር ትሰጣታለህ?

ሰ. መዝጊያ
እንደ ማንዲ አንድ ሰው ድንገት ስለ ውርጃ ቢጠይቅህ፣ የሚከተለውን ምክር ልትሰጥ ትችላለህ።
1. ህይወት የሚጀምረው በልደት ጊዜ ሳይሆን በፅንስ ጊዜ ነው። ስለሆነም፣ ውርጃ የሰውን ህይወት ማጥፋት ነው… ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ያልሆነ ተግባር ነው።
2. እግዚአብሔር ለሰው ህይወት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣል። ለኛ ትልቅ ዋጋ ከመስጠቱ የተነሣ የዘላለምን ህይወት እናገኝ ዘንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ላከልን።
3. በውርጃ ምትክ ልታደርጋቸው የምትችላቸው ነገሮች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ልጅ መውሰድ የማይችሉ ባለትዳሮች የማንዲን ዓይነት ልጅ በማደጎነት ለመውሰድ ሊፈልጉ ይችላሉ።

በማጠቃለያም፣ ስለዚህ ትምህርት ምን ዓይነት ጥያቄ ካለህ ወይም ለማስወረድ የሚፈልግ ሰው ካወቅህ፣ ሁኔታውን ለአንድ ሰው፣ ለወጣቶች አገልግሎት መሪ ወይም ለመጋቢህ ተናገር።
በጸሎት ፈጽሙ።

መጠጊያችንና ብርታታችን ነው

## ቁጡ የምትሆነው ለምንድነው?

### ከአለን ስኮት

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ቁጣን ወደ መንፈሳዊ ዕድገት እንዲለውጡ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚረዳቸው ካላወቁ፣ ቁጣ ለክርስቲያን ወጣቶች ችግር ሊፈጥር ይችላል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች የቁጣን ምንጭ ፈልገው እንዲያገኙና እግዚአብሔር ለቁጣ ችግር ምን ዓይነት ምላሽ እንዲሰጡ እንደሚፈልግ እንዲገነዘቡ ለማገዝ።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ቁጣ ኃያል የሚገነፍል ስሜት ነው። የቁጣን ገሃዳዊ እውነታ መካድ ወይም ማዳፈን ስሜታዊና አካላዊ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ከመፍራታቸው የተነሣ እነዚህ ስሜቶች እንዳሉባቸው አምነው አይቀበሉም። ነገር ግን የቁጣ ስሜቶችን ሳንደብቅ በእግዚአብሔር እርዳታ ከተቆጣጠርን፣ ቁጣው እየቀነሰ እንደሚሄድና ወደ መንፈሳዊ ዕድገት እንደምንደርስ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ክርስቲያን ወጣት ቁጣ መንፈሳዊ ጉድለት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አዲስ እውነት ሊያስተምረው እንደሚፈልግ የሚያሳይ ምልክት እንደሆነ መገንዘብ አለበት።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ወረቀት፣ እርሳሶች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. በግምት ማወቅ። እያንዳንዱ ወጣት ለሌሎች ሳያሳይ ራሱ ብቻ የሚያውቃቸውን የራሱን ምሥጢሮች (ለምሳሌ፣ ለሞኑን አንድ ከአሜሪካ የመጣ ሰው አጋጥሞኛል። አንድ ጊዜ አንድ ዶሮ ወጥ ብቻዬን ግጥም አድርጌ በልቻለሁ) በወረቀት ላይ እንዲጽፍ አድርግ። ወረቀቶቹን ሰብስብና እያንዳንዱ ሰው የጻፈውን አንብብ። ከዚያም የክፍሉ ወጣቶች ዝርዝሮቹን ማን እንደጻፋቸው እንዲገምቱ ጠይቃቸው።
2. ቃለ ምልልስ። ቡድኑን በሁለት ወይም በሦስት አነስተኛ ቡድኖች ከፋፍል። የእያንዳንዱ ቡድን አባላት ስለተቆጡባቸው ጊዜያት ይወያዩ። ቡድኖቹ ምሳሌዎቻቸውን ለጠቅላላው ቡድን ያካፍሉ። ከዚያም፣ «ለምን ነበር የተቆጡት? በዚህስ ጊዜ ምን አደረጉ?» በማለት ጠቅላላውን ቡድን ጠይቅ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)



እዚህ ውስጥ ተቆጥቶ የማያውቅ ሰው ይኖር ይሆን? ተቆጥተን ማወቃችንን ብናምን! ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች እርስ በርሳችን በግልጽ ልንነጋገር እንችላለን። ቁጣችን ራሳችንን ሊያስፈራን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ቁጣችንን እንዴት እንደምናቆም ስለማናውቅ ያልተቆጣን ለመምሰል እንሞክራለን። ቁጣችንን ለመቆጣጠር አለመቻሉም ለችግሩ መፍትሄ አይሆንም።

ብዙውን ጊዜ ቁጣ አንድ ነገር ከተከሰተ በኋላ የሚሰማን ሁለተኛው ስሜት ነው። መጀመሪያ የመጎዳት ስሜት ይሰማናል። ቁጣችን ደግሞ ከተጨማሪ ጉዳት እኛን ለመታደግ ይጥራል። ለቁጣ የምንሰጠውን ምላሽ መምረጥ አለብን። (1) ገንፍሎ እስኪወጣ ድረስ አምቆ ማቆየት። (2) በበቀል ሌላ ሰው መጉዳት። (3) ያ ሁኔታ ለምን እንደጎዳህ እስክትገነዘብ ድረስ ምንም ነገር አለማድረግ። በምንቆጣበት ጊዜ ምላሽ መስጠት ያለብን እንዴት ነው? እስኪ አንድን ሁኔታና ሁለት የቁጣ ምላሾችን እንመልከት።

ሌንሲ የትምህርት ቤት ሰዓቷ ረፍዶ ነበር። ቀኑ ከጠዋት ጀምሮ አልቀናትም ነበር። ከተለመደው በላይ አርፍዳ ነበር ከአልጋዋ ላይ የተነሣችው። ጸጉሯ አልተበጠረም። ጫማዋን ለማሰር ስትሞክር ማሰሪያው ተበጠሰባት። መጽሐፎቿን ለማንሣት ስትሞክር የቤት ሥራዋን የሠራችበት ደብተር ተቀደደባት። ወደ ትምህርት ቤት እየሮጠች ሳለ ጓደኛዋ ዳንኤል በአጋጣሚ መጽሐፎቿን ከክንዷ ላይ ገፍቶ ጣለባት።

ምላሽ ሀ፡ ሌንሲ የወደቁባትን መጻሕፍት ስትሰበስብ ተቆጥታ ነበር። ነገር ግን ምንም አልተናገረችም። በኋላ ሌንሲ በቁጣዋ አፍራ ለምን በዚህ አጋጣሚ እንደተናደደች ታስባለች። ከዚያም በዚያን ዕለት በተፈጸመው ነገር ሁሉ መጎዳቷን ትገነዘባለች። ወደ ትምህርት ቤቷ በጊዜ ለመድረስ ብትፈልግም፣ አርፍዳ መነሣቷ፣ የጫማ ማሰሪያዋ መበጠሱና የመጽሐፎቿ ከመሬት ላይ መውደቅ ዕቅዷን አበላሹባት። ሌንሲ ቀደም ሲል ለሁሉም ነገር በሰዓቱ በመገኘቷ ምን ያህል ኩራት ይሰማት እንደነበር አትገነዘብም ነበር። ኩራቷ ነበር ይህንን ቀን ያበላሸባት። እግዚአብሔር ለዚህ ኩራቷ ይቅር እንዲላት ለመነችው። እግዚአብሔር ሳይሆን ኩራቷ ተግባሮቿን እንዲቆጣጠር አድርጋ ነበር።

ምላሽ ለ፡ ሌንሲ ዳንኤል መጽሐፎቿን ስለበተነባት ጮኸችበት። ዳንኤልም መልሶ ጮኸባት። በዚህ ዓይነት ሲጣሉ ከቆዩ በኋላ የመግቢያ ደወሉ ሲያቃጭሉ ወደክፍላቸው ሮጡ። በዚያን ዕለት ማታ በቤተክርስቲያናቸው ወደሚገኘው የወጣቶች ስብሰባ ሲሄዱ፣ ሌንሲ አሁንም በዳንኤል ላይ እንዳኮረፈች ቆየች።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ሌንሲ ከምላሽ ለ በኋላ ምን ዓይነት ስሜት የተሰማት ይመስልሃል? ዳንኤልስ?
2. ለሌንሲ የሚሻለው የትኛው ምላሽ ይመስልሃል? ሀ ወይስ ለ? ለምን?
3. በሁለቱ ምላሾች መካከል ያለው እጅግ ጠቃሚ ልዩነት ምን ይመስልሃል?
4. ያንተን ምላሽ የማይመስለው የትኛው ነው? ለምን?
5. የሌንሲ ጓደኛ ብትሆን ኖሮ ከምላሽ ሀ ወይም ለ በኋላ ምን ትመክራት ነበር?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ኤፌሶን 4:26-27፡፡ *«ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ። በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ። ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።»* በዚህ ክፍል ቁጣ እንደ ኃጢአት አልታየም። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በምንቆጣበት ጊዜ ኃጢአትን መፈጸሙ ቀላል ነው። ቁጣህን ወደ እግዚአብሔር አቅርበው። እርሱም ችግሩን ያስይሃል። አንድ ሰው በኛ ላይ የሚፈጽመው ኃጢአት በራሳችን ሕይወት ውስጥ ቅንዓትን፣ ኩራትን፣ እግዚአብሔርን መጠራጠርን ወይም የራስ ፈቃድ ማስቀደምን ሊገልጥ ይችላል።
2. መዝሙር 37:7-9፡ *«ለእግዚአብሔር ተገዛ ተስፋም አድርገው። መንገድም በቀናችለትና ጥመትን በሚያደርግ ሰው አትቅና። ከቁጣ ራቅ መዓትንም ተው። እንዳትበድል አትቅና። ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉና እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ።»* ለእግዚአብሔር ስለ ቁጣችን ለመናገር ስንመርጥ፣ የቁጣችን መንስኤ የሆነውን ነገር እንረዳለን። እግዚአብሔር የቁጣችንን መንስኤ እንዲያሳውቀን እስካልጠየቅነው ድረስ የቁጣ ምላሾችን ማዘግየቱ ብዙም ጠቃሚ አይሆንም።
3. ማቴዎስ 5:22-24፡፡ *«በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል። ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሀነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል። እንግዲህ መባህን በእግዚአብሔር ፊት ብታቀርብ፣ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ ብታስብ፣ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፣ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፣ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።»* ይህ ክፍል ቁጣችንን ወደ እግዚአብሔር ካላመጣን የኋላ ኋላ መንፈሳዊ ሕይወታችንን እንደሚጎዳ ያስገነዝበናል። ቁጣ በአንተና በእግዚአብሔር መካከል የተከሰተን አንድ ነገር ሊገልጥ ይችላል።



ረ. የመወያያ ጥያቄዎች - አያሌ ወጣቶች ከላይ የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ አድርግ። ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርብላቸው።

1. እግዚአብሔር በፍጹም እንዳንቆጣ ይጠብቅብናል? (መልስ፡ አይጠብቅብንም። ቁጣ እግዚአብሔር ራሱ የሰጠን ስሜት ነው።)
2. በዚህ ስፍራ ስለ ቁጣ የተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ምን ምንድናቸው?
3. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሌንሲን እንዴት ሊረዳት ይችላል?
4. አንድ ክርስቲያን የቁጣ ጊዜውን በመንፈሳዊ ህይወቱ የሚያድግበት አጋጣሚ አድርጎ ሊጠቀምበት የሚችለው እንዴት ነው? (መልስ፡ ብዙውን ጊዜ ቁጣ በአንተና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጠረውን ችግር ይገልጣል።)

ሰ. መዝጊያ

ቁጣ አንድ ሰው በኛ ላይ የሚፈጽመው ኃጢአት ውጤት ብቻ እንዳልሆነ ስንመለከት ቆይተናል። ቁጣችን በራሳችን ህይወት ውስጥ የሚገኙ እንደ ቅንዓት፣ ኩራት፣ እግዚአብሔርን መጠራጠርና የራስን ፈቃድ ማስቀደም ዓይነት ኃጢአቶች ውጤት ነው።

በምንቆጣበት ጊዜ የቁጣ ስሜቶቻችንን አዘግይተን ለእግዚአብሔር የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማቅረብ አለብን።

1. ለምንድነው የተቆጣሁት?
2. የተጎዳሁት ወይም ተስፋ የቆረጥሁት በምንድነው?
3. ቀናተኛ፣ ኩሩ፣ የእግዚአብሔርን ኃይል የምጠራጠር ወይም የራሴን መንገድ የምፈልግ ሰው ነኝን?
4. እግዚአብሔር ስለዚህ ቁጣ ምን እናደርግ ይፈልጋል?

ለእግዚአብሔር በመታዘዝ በቁጣህ ላይ ድልን ተቀዳጅ። እነዚህን ጊዜያት የማደጊያ አጋጣሚዎች አድርገህ ተጠቀም።

የመዝጊያ ጸሎት። ወጣቶቹ ቁጣቸውን ለመቆጣጠርና ትምህርት ለማግኘት ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ጸልይላቸው።

## በወንድማማች መዋደድ
## እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ

**ሮሜ 12:10**

## መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ከዲ ኬሲ

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የእግዚብሔርን ፈቃድና ምሪት ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ማግኘት ይቻላል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች መደበኛና የግል የጽሞና ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የማሳለፍን አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ ለማገዝ።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ብዙ ክርስቲያን ወጣቶች ከእግዚአብሔር ጋር የጽሞና ጊዜ ማሳለፍ ይቸግራቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ የጽሞና ጊዜያችን ጠቃሚ ክፍል ነው። ይህ ጥናት ወጣቶች የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና የግል የጽሞና ጊዜ ማካሄድ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ሊያስገነዝባቸው ይገባል።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. በጥቁር ሰሌዳ ወይም በወረቀት ላይ በተዛቡ የፊደላት አቀማመጥ የተጻፉትን ስሞች በክፍል ለ ውስጥ ደርድር።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. በተዛቡ የፊደላት አቀማመጥ የተጻፉ ስሞች። ከጥቁር ሰሌዳው ሁለት ክፍሎች ወይም በተለያዩ ወረቀቶች ላይ የሚከተሉትን በሁለት ምድብ የተቀመጡ ስሞች ደርድር። ወንዶች በወንዶች ስሞች ላይ፣ ሴቶች ደግሞ በሴቶች ስሞች ላይ እንዲሠሩ አድርግ። በቀዳሚነት 14ቱንም ስሞች አስተካክሎ የሚጨርስ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

| የመጽሐፍ ቅዱስ ወንዶች | | | የመጽሐፍ ቅዱስ ወንዶች |
|---|---|---|---|
| ኅኖ | (ኖኅ) | ልቤልኤዛ | (ኤልዛቤል) |
| ሱስኢየ | (ኢየሱስ) | ናሐ | (ሐና) |
| ንሮአ | (አሮን) | ዋሔን | (ሔዋን) |
| ፓስሎው | (ጳውሎስ) | ድሊያ | (ሊድያ) |
| ሁዳይ | (ይሁዳ) | ሎስይ | (ሎይስ) |
| ዊትዳ | (ዳዊት) | ያማምር | (ማርያም) |
| ንኤልዳ | (ዳንኤል) | ኒዩስ | (ዩኒስ) |
| | | | |
| ማስቶ | (ቶማስ) | ያሊ | (ሊያ) |
| ስጶልፊ | (ፊልጶስ) | ሄራል | (ራሄል) |
| ዳምአ | (አዳም) | ራሣ | (ሣራ) |
| ዊሌ | (ሌዊ) | ርቃዶ | (ዶርቃ) |
| ሮድሄስ | (ሄሮድስ) | ትሩ | (ሩት) |
| ሮስጥጴ | (ጴጥሮስ) | ሚኃኒኑ | (ኑኃሚን) |
| ሴሙ | (ሙሴ) | ዳሮ | (ሮዳ) |



2. የቡድን ዝማሬ።
3. ጥያቄዎች። ይኼኛው የትምህርት ክፍል ውይይትን ሊያስከትልና ወጣቶች የራሳቸውን አሳብ ለሌሎች እንዲያጋሩ እድል ሊሰጣቸው ይገባል። በመልሶቹ ትክክለኛነት ወይም መሳሳት ላይ አስተያየት አትስጥ።

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር የጽሞና ጊዜ ማደረግ ያለበት ማነው?
ለ. የጽሞና ጊዜ ምንድነው?
ሐ. በጽሞና ጊዜ ወቅት ምን ማድረግ ያሻል?
መ. የጽሞና ጊዜ ማካሄድ ያለብህ መቼ ነው?
ሠ. የጽሞና ጊዜ ማካሄድ ያለብህ የት ነው?
ረ. የጽሞና ጊዜ ማካሄድ ያለብህ ለምንድነው?

ወጣቶቹ መልሶቻቸውን ከሰጡ በኋላ የራስህን መልስ ስጣቸው። የጽሞና ጊዜያቸው እንደሚለብሱት ልብስ ሁሉ የግላቸው እንደሆነ አስገንዝባቸው። ጥያቄዎችን ከጠየቅህ በኋላ፣ ቡድኑ የራሱን የጽሞና ጊዜ ትርጉም ሊወስን ይችላል። ትርጉሙም፣ «የጽሞና ጊዜ እግዚአብሔርን ለማምለክና ቃሉን ለማጥናት የምንለየው የተወሰነ ጊዜና ቦታ ነው» የሚል ዓይነት ሊሆን ይችላል።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

ሲቡሲሶ እንደ አንተ ያለ ወጣት ነበር። አንድ ቀን እጉል ሁኔታ አጋጠመው። በዚህ ጠዋት ሲቡሲሶ ከወትሮው አርፍዶ ነበር የተነሣው። በዚህ ጊዜ የሸሚዙ ቁልፍ ተበጠሰበት። ጫማውን የት እንዳደረገው ማግኘት ተሳነው። ከቤት ወጥተን ስንሄድ የተቋጠረ ውኃ ውስጥ በመግባቱ ካልሲው ተበላሸ።

ሲቡሲሶ ከካልሲው ውኃ ለማስወጣት ቁጭ አለ። ሲቡሲሶ የሚወዳት ሚፎ የምትባል ልጅ ነበረች። ሚፎ በዚያ ግድም ስታልፍ እንደዚያ ሆኖ ስላየችው የተዋረደ መስሎ ተሰማው። በዚያን ቀን ሲቡሲሶ የእንግሊዝኛ ፈተና የነበረበት ቢሆንም በሚገባ አልተዘጋጀም ነበር። ከማጥናት ይልቅ ከጓደኞቹ ጋር ሲጫወት ነበር ያሳለፈው። ወደ ቤት በሚመለስበት ጊዜ መጽሐፎቹ ከእጁ ላይ አፈትልከው በመውደቃቸው ነፋሱ የቤት ሥራውን የሠራባቸውን ወረቀቶች ይዞ ሄደ። ሚፎ አይታው ሳቀችበት።

ሲቡሲሶ በጣም ተጨነቀ። በዚህ ጊዜ የሆነ ማበረታቻና የጥበብ ቃል ያስፈልገው ነበር። ሚፎ አሁንም እንደምትወደው ማወቅ ያስፈልገው ነበር። ስለሆነም፣ ሲቡሲሶ መጽሐፍ ቅዱሱን አወጣ። ሲቡሲሶ ለተወሰነ ጊዜ መጽሐፉ ቅዱሱን ባያነብም፣ እርዳታ በሚያስፈልገው ጊዜ ሁሉ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ዞር ሲል እንደሚችል ተምሮ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የማበረታቻ ምንጭ ስለሆነ፣ የትኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ገልጠህ የእግዚአብሔርን ምሪት ልታገኝ ትችላለህ። ሲቡሲሶ ምሪት

ያስፈልገው ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ ለሱ ምን ነበር? ሲቡሲሶ መጽሐፍ ቅዱሱን ገልጦ ከማቴዎስ 27:5 የሚከተለውን አነበበ። «ሄደና ታንቆ ሞተ።» ይህ ለሱ የተሰጠው የእግዚአብሔር መልእክት ሊሆን አይችልም። ሲቡሲሶ አንድ የተሳሳተ ነገር እንዳደረገ አሰበ። ከዚያም ሌላ ክፍል አወጣ። ሉቃስ 10:37ን ገልጦ ሲያነብ፣ «ኢየሱስም፣ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው» ይላል።
የሆነ ችግር መኖር አለበት። እግዚአብሔር ይህንን መልእክት ሊያስተላልፍ አይችልም። ሲቡሲሶ አንድ ተጨማሪ ጊዜ ለመሞከር ወሰነ። እስጨናቂውን ቀን፣ ካልሲውን ያበላሸውን ውኃ፣ ፈተናውንና የሚፎን ሳቅ ለመርሳት እየሞከረ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲገልጥ፣ «የምታደርገውን በቶሎ አድርግ» ይላል።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ሲቡሲሶ «የጽሞና ጊዜውን» ሲጨርስ ምን የተሰማው ይመስልሃል?
2. ሲቡሲሶ የፈጸመው ስህተት ምን ይመስልሃል?
3. እንደ ሲቡሲሶ መጽሐፍ ቅዱስን በዘፈቀደ እየገለጥህ አንብበህ ታውቃለህ?
4. ለሲቡሲሶ ስለ የጽሞና ጊዜው ምን ምክር ትሰጠዋለህ?
5. የጽሞና ጊዜህ እንዴት እየተካሄደ ነው?
6. መጽሐፍ ቅዱስህን ማንበቡ አስፈላጊ ነው? ለምን?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. መዝሙር 119:9 - መኖር እንደሚገባኝ መኖር ካለብኝ፣ ይህንን የማደርገው የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘኝ መሠረት በመመላለስ ነው። ብዙዎቻችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለህይወታችን ምን እንደሆነ ለማወቅ እንፈልጋለን። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናገኘው ከየት ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለምንጋፈጣቸው አንዳንድ ችግሮች ቁርጥ ያለ መልስ ላይሰጠን ይችላል። ለምሳሌ፣ ከሜሪና ከኪም ማናቸው አብረውህ ጨዋታ እንዲያዩ መጠየቅ እንዳለብህ የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም። እንደዚያ ዓይነት መልሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኙም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች የምትወስንባቸውን መርሆች ይሰጥሃል። እነዚህ መርሆች ለሚያጋጥሙህ ሁኔታዎች ሁሉ ሊሠሩ ይችላሉ።



2. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:15-16 - እነዚህ ጥቅሶች በጣም ውስኖች ናቸው። አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሞችን ብቻ ዘርዝረዋል። እነዚህም የደኅንነት ዝግጅት፣ ማስተማር፣ መገሰጽ፣ ማረምና በጽድቅ ማሰልጠን ናቸው።

   * ቁጥር 15 - ደኅንነት፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእምነታችን መሠረት ነው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነው እውቀት የመነጨው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

   * ቁጥር 16- ማስተማር፡ መጸሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ማንነትና እግዚአብሔር ምን እንዳደረገልን በግልጽ ያስተምራል። መጸሐፍ ቅዱስ የእምነታችን ማረፊያ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምራል።

   * ቁጥር 16 - መገሰጽና ማረም፡ ይህ ማለት የሌሎችን ጥፋት ፈልጎ ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም አለብን ማለት አይደለም። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል መመላለሳችንን ለማረጋገጥ <u>የምናደርገውንና</u> የምንናገረውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ማነጻጸር አለብን ማለት ነው።

   * ቁጥር 16 - በጽድቅ ማሰልጠን፡ መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናታችን ውጤት እግዚአብሔር ይጠቀምብን ዘንድ ለመዘጋጀትና ለመሰልጠን እንድንችል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ሕይወት እንድንኖር መምራት ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎችን እንድንረዳም ያዘጋጀናል።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. የጽሞና ጊዜ እንዴት ሊረዳህ ይችላል?
2. የጽሞና ጊዜ ለአንተ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?
3. እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ምን ዓይነት ነገሮችን ሊያስተምርህ ይችላል?
4. በየቀኑ የምትማራቸውን ነገሮች እውነተኛነት ለመፈተን መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ልትጠቀም ትችላለህ?
5. መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያሰለጥንህ ፈቃደኛ ነህን?
6. መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያጋጥሙን ሁኔታዎች ሁሉ መልሶችን ይሰጣልን? ለምን?

ሰ. መዝጊያ - ወጣቶቹ መጽሐፍ ቅዱስን ከየት ጀምረው እንደሚያነቡ ለማወቅ ከፈለጉ፣ ከወንጌላት (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ) ወይም ከጳውሎስ መልእክቶች አንዱን መርጠው እንዲያነቡ ግለጽላቸው።

በጸሎት ፈጽም።

## ቆሻሻን ብንዘራ...
## ቆሻሻን እናመርታለን
ከአለን ስኮት

ሀ. *የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና አሳብ .. የምናነበውና የምናደርገው የማንነታችን አካል በመሆን ለእግዚአብሔር ባለን ጠቀሜታ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች የሚያነቡትን እንዲገመግሙና እግዚአብሔርን የሚያስደስት መሆን አለመሆኑን እንዲገመግሙ ማበረታታት።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ፖርኖግራፊ (ወሲባዊ ስሜቶችን የሚቀሰቅሱ ጽሑፎችና ሥዕሎች) ለወጣቶች አደገኞች እየሆኑ መጥተዋል። ፖርኖግራፊ በብዙ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ ፊልሞች፣ የኢንተርኔት መረቦች፣ ወዘተ. ውስጥ በቀላሉ ይገኛል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፖርኖግራፊ እየታየ ያለው በእርቃን ገላ መልክ ብቻ ሳይሆን፣ አሸባሪና አሳፋሪ ተግባራትን በማካተት ጭምር ነው። ፖርኖግራፊና ወንጀል ጎን ለጎን የሚሄዱ ተግባራት ናቸው። ፖርኖግራፊ የሰዎችን አእምሮ በማጥፋት በትክክል እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል። ወጣቶቻችን የሕይወትን አስከፊ ተጽዕኖዎች እንዴት እንደሚቋቋሙ ማስተማር ይኖርብናል። ለአእምሮ ንጹሕና መልካም የሆነውን ብቻ እንዲቀበሉ ልናበረታታቸው ይገባል።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. መጽሐፍ ቅዱሶች፣ አሮጌ መጽሔቶች ወይም ጋዜጦች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)
ከሚከተሉት የመክፈቻ ተግባራት አንዱን ወይም ሁሉንም መርጠህ ተጠቀም።

1. ታሪክ። የመክፈቻ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት፣ ከመጽሔቶች ወይም ጋዜጦች የሰዎችንና የቦታዎችን ሥዕሎች ቆርጠህ በመውጣት በወረቀቶች ላይ ለጥፋቸው። አንድ ሥዕል በአንድ ወረቀት ላይ ለጥፍ። ወጣቶቹን በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል ለእያንዳንዱ ቡድን ስምንት ሥዕሎችን አድል። እያንዳንዱ ቡድን ስምንቱንም ሥዕሎች ተጠቅሞ አንድ ታሪክ እንዲያዘጋጅ ንገራቸው። እያንዳንዱ ቡድን በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ያዘጋጀውን ታሪክ እንዲናገርና ከሁሉም የተሻለው ታሪክ በድምጽ ብልጫ እንዲመረጥ አድርግ።
2. በድምጽ ብቻ መመራት። የቡድንህን አባላት ሁለት ሁለት አድርገህ ክፈል። ከሁለቱ የአንዱን ዓይን በመሸፈን ሌላኛው እንዲመራው አድርግ። መሪው ለጓደኛው የት መሄድ እንዳለበት ይነግረዋል እንጂ በእጁ ሊነካው አይችልም። በክፍሉ ውስጥ ወይም ከክፍሉ ውጭ የሆነ መሰናክል አስቀምጥ። ከሁሉም በፊት መንገዱን የሚጨርስ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።
3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. *መሪው የሚያቀርበው ትምህርት* (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)
የምናነባቸውን፣ የምንሰማቸውንና የምናያቸውን ነገሮች እናስታውሳለን። እንደ እውነቱ ከሆነ የምንናገረውና የምናደርገው ሁሉ ወደ አእምሯችንና ወደ ልባችን ያስገባነው አሳብ ውጤት ነው። በየቀኑ ወደ አእምሮህና ልብህ የምትጨምረውን አሳብ መምረጥ አለብህ። አንዳንድ ነገሮችን ትቀበላለህ። አንዳንዶችን ግን አትቀበልም። እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎችን የምትሰጠው እንዴት ነው? ይህንን ስለ ምርጫ የቀረበውን ታሪክ አዳምጥ።
ትሼፖ እና ሮጀር የኖሩት ሁልጊዜም በወዳጅነት መንፈስ አልነበረም። ሮጀር ትሼፖ ወደሚኖርበት ከተማ የሄደው ትምህርት ቤት ሊከፈት ሲል ነበር። በዚህ ጊዜ ትሼፖ የሮጀር የመጀመሪያው ጓደኛ በመሆን ሌሎች ጓደኞችንም እንዲያፈራ ረዳው። በመካከላቸው የተከሰተው ችግር ቢኖር ትሼፖ ሁልጊዜም ሮጀርን እንደ ትንሽ መቁጠሩ ነበር። ከገጠር ወደ ከተማ መሄዱ ሮጀር ከዚህ በፊት የማያውቃቸውን አዳዲስ ነገሮች እንዲለማመድ አድርጎት ነበር።
አንድ ቀን የትምህርት ሰዓት ከመድረሱ በፊት ሮጀር ትሼፖን አየው። አንዳንድ ልጆች በትሼፖ ላይ በመቀለድና በመሳቅ ላይ ነበሩ። ትሼፖ ሮጀርን ጠርቶ፣ «አንተ የባላገር ልጅ፣ ይህን ማየት አለብህ» አለው። በዚያ ጊዜ ሮጀር ትሼፖ አንድ ጥሩ ያልሆነ መጽሔት እንዳገኘና በዚያን ማታ እንደሚያየው ተገነዘበ። ትሼፖ ሮጀር ወደ ቤቱ መጥቶ በዚያን ማታ ሥዕሉን እንዲያይ ቢጋብዘውም ፈቃደኛ አልሆነም። ትሼፖ ሮጀር ሥዕሉን ለማየት ካልመጣ እንደ እንግዳ ወይም እንደ ሕጻን ልጅ እንደሚቆጥር ነገረው።
ሮጀር ቀኑን ሁሉ በትምህርት ቤት ስለዚሁ ጉዳይ ሲያስብ ዋለ። የወጣቶች ቡድን መሪው ከትሼፖ እንዲርቅ እንደሚፈልግ ያውቃል። ነገር ግን ሮጀር ወደዚያው ካልሄደ ትሼፖና ጓደኞቹ ችግር እንደሚፈጥሩበት ተገነዘበ። ትሼፖ ጥሩ ጓደኛው ስለነበር ሮጀር ሊጎዳው አልፈለገም። ሮጀር አንድን መጽሔት ማየት ወይም አለማየት ማንንም አይጎዳም ሲል አሰበ። ነገር ግን ትሼፖ ባለፈው ወር ከቆሻሻ ውስጥ ያገኘውን አንድ መጽሔት ከተመለከተ በኋላ ምን ዓይነት የድንጋጤ ስሜት እንዳደረበት ታወሰው። ሮጀር ምን እንደሚያደርግ ጨነቀው።

መ. *የመወያያ ጥያቄዎች* (*መጀመሪያ* የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ሮጀር ምን ዓይነት ስሜት የሚሰማው ይመስልሃል?

2. ከትሼፖ ጋር የመሄድ ፈተናው ምን ያህል ጠንካራ ነበር? ፈተናው እንዲህ የጠነከረበት ለምንድነው?
3. ሮጀር ምን ማድረግ ያለበት ይመስልሃል?
4. ሮጀር ካልሄደ ለትሼፖ ምን ብሎ መናገር አለበት?
5. በሮጀር ቦታ ብትሆን ለምክር ወዴት ትሄዳለህ?
6. አንድ ጊዜ ብቻ ሥዕሉን መመልከቱ ችግር አለው? ለምን?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ሉቃስ 6:45-49። *«መልካም ሰው ከልብ መልካም መዝገብ መልካሙን ያወጣል። ክፉ ሰውም ከልብ ክፉ መዝገብ ክፉውን ያወጣል። ስለ ምን፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ ትሉኛላችሁ። የምለውንም አታደርጉም? ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገው፣ ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ። ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል። ጎርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን ቤት ገፋው። በዓለት ላይም ስለተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም። ሰምቶ የማያደርገው ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል። ወንዙም ገፋው። ወዲያውም ወደቀ። የዚያ ቤት አወዳደቅም ታላቅ ሆነ።»* በልባችን ውስጥ የምናስቀምጠው ነገር ክርስቶስን በቀዳሚነት ያሳስበዋል። ፍሬያችን የሚመጣው ከምናጠራቅመው ነገር ነው። በመጥፎ ነገሮች ላይ ጠንካራ ክርስቲያናዊ ሕይወት ልትገነባ አትችልም። አእምሮህን በመጥፎ ነገሮች ሞልተህ ስታበቃ፣ ፈተና በሚመጣበት ጊዜ ብርቱ ነኝ ልትል አትችልም።
2. 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:20-21። *«በትልቅም ቤት የእንጨትና የሸክላ ዕቃ ደግሞ አለ እንጂ የወርቅና የብር ዕቃ ብቻ አይደለም። እኩሌቶቹ ለክብር፣ እኩሌቶቹም ለውርደት ይሆናሉ። እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነጻ፣ ለክብር የሚሆን የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል።»* አንዳንድ ጊዜ መጥፎ ነገሮችን ወደ ሕይወታችን ፈቅደን እናስገባለን። አንዳንድ ጊዜ የምንጠቀምባቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ መጻህፍትና መጽሔቶች ጥሩዎች አይደሉም። ጥያቄው እንግዲህ፣ ለጌታህ የምትጠቅም ሰው ለመሆን ትፈልጋለህ ወይ? የሚለው ነው። ከሆነ፣ መጥፎ ነገሮችን ከሕይወትህ አራግፈህ ማስወጣት አለብህ።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. የማየው ነገር ሁሉ ተጽዕኖ ያሳድርብኛልን? ለምን? እንዴት?
2. መጽሐፍ ቅዱስ የማየውን ወይም የማነበውን ነገር በተመለከተ ምን መምሪያ ይሰጣል?
3. ከላይ የቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሮጀር ካለበት ሁኔታ ጋር ይዛመዳሉ? ከሆነ፣ እንዴት?



4. እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ፣ ለሮጀር ምን ዓይነት ምክር ትሰጠዋለህ?
5. ይህ ጥናት አእምሮህን የለወጠው እንዴት ነው? ምን ዓይነት አዳዲስ ትምህርቶችን ተምረሃል?

ሰ. መዝጊያ

በዚህች ዓለም ውስጥ በምንመላለስበት ጊዜ፣ ለአእምሯችንና ለልባችን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የሚከተሉትን ዓይነት መርሆች መከተል አለብን።

1. ሁሉም ነገሮች ለእኔ የሚበጁ አለመሆናቸውን መገንዘብ። አንዳንድ ነገሮች ለአእምሮዬ ጥሩዎች አይደሉም። አንዳንንድ ትውስታዎች አእምሮዬ ውስጥ ዘልቀው ከገቡ በኋላ አልዘነጋ ይሉኛል።
2. እግዚአብሔር የሚጠቀመው በአእምሮህ ውስጥ ያስቀመጥኸውን ነገር ነው።
3. ከሁሉም የሚሻለውን ነገር ብቻ በአእምሮህ ውስጥ አስቀምጥ።
4. ለአእምሮህ ጥሩ ካልሆኑ መጽሔቶች፣ መጻሕፍት፣ ፊልሞች፣ ቴሌቪዥኖች፣ የኢንተርኔት መረቦች፣ ሙዚቃዎች፣ ጓደኞች፣ ወዘተ. ራቅ።

## የምትናገረውን



## ኑር

## ብቸኝነትን መቋቋም
### ከማርክ ፒቸር

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ብቸኝነት የፈጠረውን ባዶነት ሊሞላ ይችላል። ይሞላልም።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወደ ሌሎች በመቅረብና በብቸኝነታቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት የብቸኝነትን ስሜት እንዲያሸንፉ ሊያግዛቸው ይገባል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ብዙ ወጣቶች በብቸኝነት ይሠቃያሉ። ብቸኝነት በተለያዩ መልኮች ይመጣል። ከነዚህም መካከል ጓደኞችህ በሙሉ አብረው ወደ አንድ ስፍራ ከሄዱ በኋላ ቤት ውስጥ ስትቀር፣ አብሮህ የሚመገብ ሰው ሳይኖር ሲቀር፣ ፍቅረኛ ስታጣ፣ ከትምህርት ቤት ወይም ከቤተክርስቲያን ቀርተህ ሳለ ማንም አለመኖርህን ልብ ሳይል ሲቀር፣ ብቸኝነት ሊሰማህ ይችላል። ትልቁ አደጋ የሚከሰተው ወጣቶች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚረዳቸው ከማሰብ ይልቅ ስለ ብቸኝነታቸው በሚያስቡበት ጊዜ ነው። ስለሆነም፣ ወጣቶች እግዚአብሔር ስለ ጓደኝነት የሰጠውን የተስፋ ቃልና እያንዳንዱ ሰው ለሌላው ራሱን እንዲሰጥ የሚፈልግ መሆኑን እንዲገነዘቡ መርዳት ይኖርብናል። ይህ ጥናት ወጣቶች እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና እነሱም በምላሹ እርሱንና ሌሎችን እንዲወዱ የሚፈልግ መሆኑን እንዲገነዘቡ እንዲያግዛቸው ጸሎታችን ነው። ይህንን መረዳት እግዚአብሔር ለብቸኝነት የሰጠውን መድኃኒት ማግኘት ነው።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ወረቀቶችና እርሳሶች፣ የሙዚቃ መሣሪያ ወይም ማጫወቻ።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. ቡድኖች። ሙዚቃ እያጫወትህ ወጣቶቹ በሙሉ ክብ ሠርተው በክፍሉ ዙሪያ እንዲንቀሳቀሱ አድርግ። ጨዋታው በሚካሄድበት ጊዜ መሪው ሙዚቃውን በማስቆም የሆነ ነገር (ለምሳሌ፣ ቆርቆሮ) ጮክ አድርጎ ይመታል። በዚህ ጊዜ ወጣቶቹ በፍጥነት የተመታውን ቁጥር ያህል አባላት የሚገኙባቸውን ቡድኖች ይሠራሉ። ለምሳሌ ያህል፣ የወጣቶቹ ቁጥር 15 ቢሆንና መሪው ቆርቆሮውን ሰባት ጊዜ አከታትሎ ቢደበድብ፣ 7 አባላት የሚገኙባቸው ሁለት ቡድኖች ይፈጠሩና አንድ ሰው ይተርፋል። የተረፈው ሰው ከጨዋታ ውጭ



ይሆናል። ሁለት ሰዎች ብቻ እስኪቀሩ ድረስ ጨዋታው ይቀጥልና ከጨዋታ ውጭ ሳይሆኑ የቆዩት ሁለቱ አሸናፊዎች ይሆናሉ።
2. ወደ ሙዚቃው መሄድ። ወንበሮችን በክብ ቅርጽ ደርድር። የወንበሮች ቁጥር ከወጣቶቹ በአንድ ማነስ እንዳለበት አረጋግጥ። ይህ ቀላል ጨዋታ ነው። ሙዚቃው እየተጫወተ ሳለ (የቴፕ መዝሙር የሚጀምርና የሚያስቆም አንድ ሰው መድብ።) ሁሉም ሰው በወንበሮቹ ዙሪያ ይጓዛል። ሙዚቃው በሚቆምበት ጊዜ ሁሉም ሰው መቀመጥ አለበት። ሙዚቃው በቆመ ጊዜ ሁሉ አንድ ሰው ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ሙዚቃው በቆመ ጊዜ ሁሉ አንድ ወንበር መቀነስ እንዳለብህ አትዘንጋ። ጨዋታው አንድ ሰው ብቻ እስኪቀር ድረስ ይቀጥላል። ለአሸናፊው ሽልማት ወይም ለቡድኑ ነጥብ ስጥ።
3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

አንዳንድ ጊዜ ሁላችንም የብቸኝነት ስሜት ይጫነናል። ብቻህን ሆነህ ወይም ሰዎች በሞሉበት ቤት ውስጥ ሆነህ በብቸኝነት ልትሠቃይ ትችላለህ። ምናልባት አንዳንዶቻችሁ አሁንም ብቸኝነት እየተሰማችሁ ይሆናል። እንዳንዶቻችን በቀረው ዘመናችን ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ከብቸኝነት ጋር መታገል ይኖርብናል። በእኔ በኩል፣ ከሁሉም በላይ ለብቸኝነት የምጋለጠው አዲስ የትምህርት ቤት ዓመት ሲጀመር፣ ወደ አዲስ ትምህርት ቤት ስገባ፣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቼ ወደ አንድ ቦታ ሲሄዱ አብሬአቸው ልሄድ ሳልችል ሲቀር ነው። ይህን ችግር እንዴት መቋቋም እንዳለብን መማር አለብን። እስኪ አንድ ምሳሌ እንመልከት።

ናላዲ ለምን የብቸኝነት ስሜት እንደሚሰማት አልገባትም። ከሰዎች ጋር አብራ ለመሆን ጥረት አድርጋለች። ናላዲ በቤተክርስቲያን የወጣቶች ካውንስል አባል ከመሆኗም በላይ ቅዳሜ ዕለት ሰዎችን ትጎበኛለች። በትምህርት ቤትም የተማሪዎች ካውንስል አባል ነች። የኮሌጅ ተማሪ እንደመሆኗ መጠን፣ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ስድስት ተማሪዎች ጨምሮ ከሁሉም ጋር ጓደኛ ለመሆን ጥረት ታደርጋለች። ደግ፣ የወዳጅነት መንፈስ የሚታይበትና ተግባቢ ለመሆን ትሞክራለች። ነገር ግን ናላዲ ወደ ልዩ እንቅስቃሴዎች ግብዣ ተደርጎላት ስለማያውቅ፣ ታዝናለች። ቤት አካባቢ ወላጆቿ ሊያጽናኗት ቢሞክሩም፣ አልጠቀማትም። ሁኔታዋ ስላሳሰባቸው ከቤተክርስቲያን የወጣቶች አገልግሎት መሪ ጋር እንድትነጋገር ቀጠሮ ያዙላት። መሪው መጸሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሁልጊዜም ከኛ ጋር መሆኑን እንደሚናገር ጠቅሶ፣ ሙሉ በሙሉ ራሷን ለጌታ የሰጠች ክርስቲያን ብትሆን ኖሮ ኃዘን አይገባትም ነበር ሲል ገለጸ። ይህም ቢሆን ናላዲ ጥሩ ስሜት እንዲሰማት

አላደረገም። ምክንያቱም እሷ ሁልጊዜም ራሴን የሰጠሁ ክርስቲያን ነኝ ብላ ነበርና የምታስበው።

ናላዲ በመጨረሻም፣ ስለ ስሜቶቿ ለአንዳንድ የትምህርት ቤት ጓደኞቿ ተናገረች። ሜሪ ስለ ናላዲ ብቸኝነት ስትሰማ ተገረመች። ምክንያቱም ናላዲ ለተመልካች ተግባቢ ትመስል ነበርና። ሼረን ናላዲ የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ስትል የተጋነነ እንቅስቃሴ ታደራጋለች ብላ ስታስብ እንደነበር ገለጸች። ጂምስ አንዳንድ ወንድ ልጆች ናላዲ ከሚገባው በላይ ተግባቢ ስለሆነች፣ ምሳ ብንጋብዛት በተሳሳተ መንገድ ትረዳን ይሆናል ብለው እንደሚያስቡ ገለጸላት። በትምህርት ቤቱ ውስጥ አዲስ ተማሪ የሆነችው ፔሲሳ፣ «ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማሽ ይገባኛል» አለች።

ናላዲ ከትምህርት ቤቱ አማካሪ ጋር ተገናኝታ የብቸኝነት ስሜቷን ለማካፈል ወሰነች። አማካሪውም ችግሩ በጊዜ ሂደት ውስጥ መፍትሔ እንደሚያገኝ ገልጾ፣ «ናላዲ፣ ጊዜ ከሰጠሽው ብቸኝነትሽ የሚያልፍ ነገር ይሆናል» ሲል ተናገረ።

*መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)*

1. ለናላዲ ትልቁን መጽናኛ የሰጣት ማነው? ለምን?
2. ትልቁን ተስፋ መቁረጥ የፈጠረባት ማነው? ለምን?
3. ለናላዲ ምን ዓይነት ምክር ትሰጣት ነበር?
4. ከፍተኛ ብቸኝነት የተሰማህ መቼ ነበር?
5. ብቸኝነት በተሰማህ ጊዜ ያጽናናህ ምን ነበር?
6. ራሱን የሰጠ ክርስቲያን በጭራሽ ብቸኛ ሊሆን አይችልም ብለህ ታምናለህ? ለምን?

*ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)*

1. ማቴዎስ 22:36-39 .. *«ከሕግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት?... ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ነፍስህም፣ በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች። እርስዋም፣ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።»* ስለ ራሳችን ሁኔታ የምናስብ ከሆነ፣ ብቸኝነት ችግሮችን ያስከትላል። ይህም ለራሳችን እንድናዝን፣ ዋጋ የለኝም ብለን እንድናስብ፣ ከሰዎች እንድንርቅና በዙሪያችን ግንብ እንድንገነባ ያደርጋል። ይህ ምንባብ ምንም ሳናስቀር በሙሉ ልባችን እግዚአብሔር መውደድ እንዳለብን ያስተምረናል። ይህም ዓይኖቻችንን ከራሳችን አንሥተን በጌታ ላይ እንድናደርግ ያበረታታናል። እግዚአብሔርን በሕይወታችን ውስጥ ከሁሉም ካስቀደምን፣ እርሱን ለማስደሰት እንጥራለን። እርሱን እጅግ ደስ የሚያሰኘው እኛ እርስ በርሳችን ስንዋደድ መመልከት ነው። የሌሎችን ፍላጎቶች ከማሟላት የበለጠ ብቸኝነትን ማስወገድ የሚቻልበት መንገድ የለም።
2. ማቴዎስ 14:22-23 .. *«ወዲያውም ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ፣ ደቀመዛሙርቱ በታንኳይቱ ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው። ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፡ በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።»* ኢየሱስ ከሰው ጋር የሚሆንበትና ብቻውን የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ ያውቅ ነበር። ብቻችንን መሆንና ብቸኛ መሆን ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ይሁንና፣ ብዙውን ጊዜ ብቻዬን ከሆንሁ አንድ ችግር አለ ማለት ነው ከሚል ግምት በመነሣት፣ ብቻችንን በምንሆንበት ጊዜ ለብቸኝነት እንጋለጣለን። ኢየሱስ ብቻውን የሆነበትን ጊዜ በፍሬያማ መልኩ ተጠቅሟል። ስለራሱ የብቻነት ሁኔታ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ለማሰብ ፈለገ። ደቀመዛሙርቱ ብቻቸውን ከእግዚአብሔር ጊዜ እንዲያሳልፉ አስተምሯቸዋል (ማቴዎስ 17:1፣ ሉቃስ 9:10)።

*ረ. የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ለእግዚአብሔር ያለህን ፍቅር ለማሳየት የምታደርጋቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
2. እርስበርሳችን ልንዋደድ የምንችልባቸው መንገዶች ምን ምንድናቸው?
3. ብቻህን በምትሆንበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመመሥረት የሚያስችል ምን ተግባር ታከናውናለህ?
4. ጓደኛህ የብቸኝነት ስሜት ቢሰማው እንዴት ትረዳዋለህ?

*ሰ. መዝጊያ*

በዚህ ጊዜ አንዳንዶቻችሁ ከብቸኝነት ጋር እንደምትታገሉ እርግጠኛ ነኝ። እግዚአብሔር ባላችሁበት ስፍራ ሊረዳችሁ ይፈልጋል። ነገር ግን ይህንኑ እንዲያደርግ ልትፈቅዱለት ይገባል! የሚከተሉትን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አድምጡ። ዘዳግም 31:8፡ *«በፊትህም የሚሄድ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ከአንተ ጋር ይሆናል። አይጥልህም፣ አይተውህም፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ አለው።»* ከአዲስ ኪዳን ደግሞ ማቴዎስ 28:20፣ *«እነሆም፣ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።»* እግዚአብሔር በብቸኝነትህ እንዲረዳህ ከፈለግህ፣ ይህንን ጸሎት ጸልይ፡ *ውድ አባቴ ሆይ፣ እንዲሁ እንዳለሁ ስለምትወደኝ አመሰግንሃለሁ። ሌሎችን መውደድ እጀምር ዘንድ አንተን በፍጹም ልቤ፣ ነፍሴና አሳቤ እንድወድህ እርዳኝ። ብቻዬን በምሆንበት ጊዜ እንድጸልይ፣ ቃልህን እንዳጠናና የሰጠኸኝን መልካም ነገሮች*

*እንዳስብ እርዳኝ:: እኔም አንተን የሚያስደስት ሕይወት ለመኖር እጥራለሁ:: አሜን::*

**እነሆም፣ እኔ**
**እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ**
**ሁልጊዜ**
**ከእናንተ ጋር ነኝ**
**ማቴዎስ 28:20**



# የማበረታታት ስጦታ
## ከማርክ ፒቸር

*ሀ. የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና ሐሳብ .. እግዚአብሔር «አንዳችን ሌላውን እንድናበረታታ (እንድናጽናና)» ይፈልጋል::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች የማበረታታትን አስፈላጊነት እንዲገነዘቡና እርስ በርሳቸው የሚበረታቱባቸውን መንገዶች እንዲፈልጉ ሊረዳቸው ይገባል::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ ሐሳብ .. ወጣቶች በየቀኑ ጥሩና መጥፎ ተጽዕኖዎች ያጋጥሟቸዋል:: ወላጆቻቸው፣ አስተማሪዎቻቸውና ጓደኞቻቸው ለውጤታማነት እንዲጥሩ በመጠየቅ፣ በማነሣሣትና በመገፋፋት ጫና ይፈጥሩባቸዋል:: ለስኬት እንዲህ ዓይነት ከፍተኛ ትኩረት ስለሚሰጥ፣ ወጣቶች የማበረታታትን ስጦታ መቀበላቸውና ለሌሎች መስጠታቸው አስፈላጊ ነው:: ወጣቶች ሌሎችን እንዴት ማበረታታት እንደሚችሉ ካወቁ፣ (1) የክርስቶስን አካል አንድ አድርገው ያስተሳስራሉ:: (2) ባለማቋረጥ እርስ በርሳቸው ይተናነጻሉ:: (3) «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ ይፈጽማሉ:: (4) ስለራሳቸው የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸዋል::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. በትንንሹ የተቆራረሰ ዳቦ፣ ወረቀቶች፣ እርሳሶች፣ በጥርሶች መካከል የሚቀር ምግብ ለማስወጣት የሚረዱ ስተኪኒዎች::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. አፍ ውስጥ ዳቦ ማጨቅ:: አራት ወንዶችና አራት ሴቶች ወጣቶች ምረጥ:: ወንዶቹ ጎን ለጎን ቆመው ወደተቀሩት ወጣቶች ፊታቸውን ማዞር ይኖርባቸዋል:: ሴቶቹ ለወንዶቹ ዳቦ ያጎርሳሉ:: ወንዶቹ ዳቦ ወደ አፋቸው በተጨመረ ቁጥር፣ «ጸጉራም ጥንቸል» ማለት አለባቸው:: «ጸጉራም ጥንቸል» ማለት ካልቻሉ፣ የጎረሱትን ዳቦ ከተፉ ወይም ከዋጡ ከጨዋታው ውጭ ይሆናሉ:: በመጨረሻው ላይ ብዙ ዳቦ በአፉ ውስጥ ይዞ የተገኘ ልጅ ያሸንፋል:: ከዚያ በኋላ ወንዶቹ ሴቶቹን እንዲያጎርሱ በማድረግ፣ ሴቶቹ ምን ያህል ምግብ በአፋቸው ሊይዙ እንደሚችሉ ልትመለከት ትችላለህ::
2. ዳቦ በስተኪኒ የማስተላለፍ ጨዋታ:: ከተቻለ፣ እኩል አባላት የሚገኙባቸውን ሁለት ቡድኖች መርጠህ አሰልፋቸው:: ለሁለቱም ቡድኖች አባላት በሙሉ ስተኪኒዎችን አድልና ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ አነስተኛ ዳቦ ሰጣቸው:: ይህንን ጨዋታ ማካሄድ የሚቻለው በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚገኙት ልጆች በሙሉ

ስተኪኒዎቻቸውን በአፋቸው እንዲይዙ በማድረግ ነው። አብዛኛው የስተኪኒው አካል ከአፍ ውጭ ይሆናል። ዳቦው በመጀመሪያው ልጅ ስተኪኒ ላይ ይሰካል። እሱም እጁን ሳይጠቀም ዳቦውን ወደሚቀጥለው ልጅ ስተኪኒ ላይ ያስቀምጣል። ዳቦውን ለቀጣዩ ልጅ በሚያስተላልፍበት ጊዜ ስተኪኒውም አብሮ ይሄዳል። ሁለተኛው ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ ዳቦውን ለቀጣዩ የቡድኑ አባል ያስተላልፋል። አሸናፊው ቡድን ዳቦውን ወደ መጨረሻው የቡድኑ አባል በቀዳሚነት ያስተላለፈ ይሆናል። በዚህም ጊዜ የመጨረሻው ልጅ ዳቦውን ብቻ ሳይሆን የቡድኑን አባላት ስተኪኒዎች ሁሉ ከዳቦው ላይ ያገኛል።

3. የዳቦ ውርወራ። አራት ጥንድ ወጣቶችን ምረጥ። ከእያንዳንዱ ጥንድ ቡድን አንደኛው ልጅ ዳቦ ወርዋሪ፣ ሁለተኛው የተወረወረውን ዳቦ የሚቀበል ይሆናል። ዳቦ ወርዋሪዎቹ ጎን ለጎን እንዲሰለፉ አድርግ። ዳቦ ተቀባዮቹ ቢያንስ ሦስት ሜትር ያህል ከወርዋሪዎቹ ርቀው ይሰለፋሉ። ለወርዋሪዎቹ ለእያንዳንዳቸው 10 ዳቦዎች ስጣቸው። ዳቦ ተቀባዮቹ የሚወረወሩላቸውን ዳቦዎች በአፋቸው ይይዛሉ። እጆቻቸውን መጠቀም አይችሉም። አሸናፊው ቡድን ብዙውን ዳቦ የያዘው ይሆናል።
4. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾች ሆናችሁ ታውቁ እንደሆነ፣ መሪው ከወዲያው ወዲህ እየሮጠ በጨዋታው ላይ ትኩረት ለማድረግና አምንታዊ ዝንባሌ ለመያዝ የሚያደርገውን ጥረት ታውቃላችሁ። ይህ ካልሆነ፣ ጨዋታውን መጫወት አይቻልም።

ባለማቋረጥ፣ «ተግታችሁ እያጠናችሁ አይደላችሁም። እናም ራሳችሁን በሥራ በመወጠር ተግባራችሁን መወጣት አለባችሁ» የሚል አስተማሪ በሚያስተምርበት ክፍል ውስጥ ሆናችሁ ታውቃላችሁ?

እንዲህ ዓይነት የግደታ ጫናዎች ብዙም አልረዱኝም። እንዲያውም የባሱ ችግሮችንና ተስፋ መቁረጥን አስከትለውብኛል። የምፈልገው የማበረታቻ ቃላትን ነበር።

ስለ ክርስቶስ የመሰከረልኝ ግለሰብ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ እንዳምን አበረታቶኛል። በዚህም ጊዜ ክርስቶስን ማመን ያለብኝ ወደ ሲኦል ላለመሄድ ሳይሆን፣ ክርስቶስ እንዲሁ እንዳለሁ ስለወደደኝና ስለተቀበለኝ መሆኑን ገልጾልኛል። ከክርስቶስ ጋር አዲስ ሕይወት ለመጀመር የሚያስፈልገኝ ማበረታቻ ይኼው ነበር። ማበረታቻ ሁላችንም የምንፈልገው ነገር ነው።

እስኪ ስለሚከተለው ምሳሌ አስቡ። የሮናልድ ልብ በፍርሃት ተሸብሯል። ነገ ታላቅ የታሪክ ትምህርት ፈተና ይጠብቀዋል። በእግር



ኳስ ቡድኑ ውስጥ መጫወቱን መቀጠል የሚችለው በትምህርቱ ቢያንስ «ሲ» ካመጣ ብቻ ነበር።

ጆን የሮናልድ ጥሩ ጓደኛ ከመሆኑም በላይ፣ የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋችም ነው። ጆን በታሪክ ትምህርትም ምርጥ ከሚባሉት ተማሪዎች አንዱ ነበር። ጆን ሮናልድ ለቡድኑ ጠቃሚ ተጫዋች እንደሆነና እሱ ከጎደለ ቡድናቸው ሊሸነፍ እንደሚችል ያውቅ ነበር። ሮናልድ ከሌሎች ልጆች እስካልኮረጀ ድረስ በፈተናው ጥሩ ውጤት ሊያመጣ እንደማይችል ለጆን ነገረው። ጆን ራሱ ሊያስኮርጀው እንደሚችል ገለጸለት። ሮናልድ የተስፋ መቁረጥ ስሜት እየተሰማው የጆንን ግብዣ ለመቀበል ተዘጋጀ።

ከትምህርት ቤት መልስ ሮናልድ የቤተክርስቲያን ጓደኛው ከነበረው ከአለን ጋር ተነጋገረ። ፈተናው ተስፋ እንዳስቆረጠው ገለጸለት። በዚህ ጊዜ አለን አበረታታው። ተግቶ ካጠና ጥሩ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል አብራራለት። አለን በዚያን ማታ ከሮናልድ ጋር ለማጥናትና በጥሩ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ለማገዝ ተስማማ።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ሮናልድ ምን የሚያደርግ ይመስልሃል?
2. የአለን ማበረታቻ ከጆን የሚለየው እንዴት ነው?
3. ሮናልድ ጆን የሚፈልገውን ካደረገ ምን ይከሰታል?
4. ሮናልድ አለን የሚፈልገውን ካደረገ ምን ይከሰታል?
5. የሮናልድ ጓደኛ ብትሆን እንዴት ታበረታታዋለህ?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ፊልጵስዩስ 2:1-4: *«በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን፣ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፣ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፣ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፣ ደስታዬን ፈጽሙልኝ። በአንድ አሳብ ተስማሙ። አንድ ፍቅር፣ አንድም ልብ፣ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ። ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ። ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር። እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት። ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።»* ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን በምናምንበት ጊዜ፣ ከርሱ ጋር ወደሚፈጠር አዲስ ግንኙነት እንዘልቃለን። እርሱም መጽናናትን፣ ፍቅርን፣ ኅብረትንና በዙሪያችን ስላሉት ነገሮችና የኛ እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ሰዎች አዲስ ግንዛቤን ይሰጠናል። ልክ እንደ ኢየሱስ ማሰብና ማፍቀር እንጀምራለን። ወንጌሉን ለሰዎች ሁሉ

እንድናካፍል የሚጠይቅ ዓላማውን እንቀበላለን። ለዚህ ሁሉ ቁልፉ የኢየሱስን ባሕርይ መከተል ነው። ይህም የአገልጋይነት፣ ሌሎችን ከራሴ የማስቀደም፣ ስለ እነርሱና እግዚአብሔር ለእነርሱ ስለሚያደርገው ነገር ግድ የመሰኘት ዝንባሌ ነው። የዚህም ውጤቱ የአካል ክፍሎች አንድነት ነው። በዚህ አንድነት ውስጥ ሁሉም ሰው በተመሳሳይ ደረጃ ላይ፣ ማለትም ሌሎችን ለማገልገል በመፈለግ እንጂ ሌሎች እንዲያገለግሉት በማይፈልግበት ደረጃ ላይ መድረስ ይሆናል።

2. ዕብራውያን 10:24-25: *«ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ። በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው፣ መሰብሰባችንን አንተው። እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።»* የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ስደትን ተቋቁመው ወንጌሉን እንዲያሰራጩ ካስቻሏቸው ምክንያቶች አንዱ ባለማቋረጥ ኅብረት ማድረጋቸውና እርስ በርስ መበረታታታቸው ነበር። አማኞች በአንድነት ተሰባስበው ይጸልዩ፣ ያጠኑ፣ ችግሮቻቸውን ይካፈሉና እርስ በርሳቸው ይበረታቱ ነበር።
3. ዮሐንስ 13:34-35: *«እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። እር በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፣ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።»* ክርስቶስ ትእዛዝ ሰጥቶናል። ይህንንም ትእዛዝ መጠበቅ ይኖርብናል። ይህ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ክርስቲያኖች ከሆንን፣ እርስ በርሳችን ልንዋደድና ልንበረታታ ይገባል። ሰዎች ክርስቲያን መሆንህን የሚያውቁበት ትልቁ መመዘኛ ፍቅር ነው።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች።
1. ማበረታታት ለክርስቲያን አማራጭ (ቢተው ለውጥ የሚያመጣ) ነው?
2. የወጣቶች ቡድንህ አባላት እርስ በርሳቸው ቢበረታቱ ምን ይከሰታል?
3. እርስ በርሳችን ልንበረታታ የምንችልባቸው ውስን መንገዶች ምን ምንድናቸው?
4. ሰዎች ሌሎችን እንዳያበረታቱ የሚከለክላቸው ምንድነው?

ሰ. መዝጊያ - ማበረታቻ/ማጽናኛ በሕይወት ውስጥ ለሚያጋጥሙን ብዙ ጉዳቶችና ቅይማቶች መድኃኒት ነው።
እያንዳንዳችን በዙሪያችን ለሚገኙ ሰዎች የማበረታቻን ስጦታ ልናበረክት እንችላለን። ሰዎችን ማጽናናት ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንዳለው ከተገነዘብህና ይህንኑ ለማድረግ ከፈለግህ፣ የሚከተሉትን መርሆች እጢን።



**መርህ አንድ፡ ማበረታታት ፈውስን ያመጣል**
አንዳንድ ጊዜ መድኃኒት ለውጥ ሳያመጣ ሲቀር፣ ተራ፣ አፍቃሪ፣ አድማጭና ግድ የሚላቸው ወጣት አማኞች የሚሰጡት ማበረታቻ/ማጽናኛ ልባቸው የቆሰለባቸውን ሰዎች በመፈወስ ያጽናናቸዋል። አበረታች ቃላት ቁስል ላይ እንደሚጨመር ቅባት ናቸው። ማበረታታት አንድ ሰው ስለራሱ መልካም ስሜት በማይሰማው ሰዓት ክብሩንና ዋጋ አለኝ የሚል ስሜት መልሶ እንዲያገኝ መርዳት ነው።
**መርህ ሁለት፡ ሁሉም ሰው የማበረታቻን ቃላት ይሻል**
ሁላችንም በቤት፣ በትምህርት ቤትና በቤተክርስቲያን መበረታታትን የሚፈልጉ ጓደኞችና ወዳጆች አሉን። ተስፋ የቆረጡና የደካማነት ስሜት የራቃቸው በሚመስልበት ጊዜ፣ ልናበረታታቸው ይገባል። ነገር ግን ሁልጊዜም የማበረታቻ ቃላት የሚያስፈልጓቸውን እንደ መጋቢ፣ ወላጆቻችንና የቅርብ ጓደኞቻችንን ሁልጊዜም አናስታውሳቸውም። ማንኛውም ሰው ከጊዜ ወደ ጊዜ የማበረታቻ ቃላትን ይሻል።
**መርህ ሦስት፡ ማበረታታት የሚጀምረው ሕይወትን ሌላው ሰው በሚያይበት መንገድ ስንመለከት ነው።**
አንድ ሰው የሚፈልጋቸውን ነገሮች እስካላወቅህ ድረስ ልታበረታታው አትችልም። ይሁንና፣ ብዙውን ጊዜ የማበረታቻ ቃላት የሚያስፈልጓቸው ሰዎች ፍላጎቶቻቸውን ይፋ እያወጡም። አበረታች የሰዎችን ፍላጎቶች የሚረዳና ስሜታቸውን ለማወቅ የሚጥር ሰው ነው። የማበረታቻ/የማጽናኛ ስጦታ ተግባራዊ የሚሆነው ሰዎችን ክርስቶስ በሚያያቸው መልኩ ስናያቸው ነው።
**መርህ አራት፡ ማበረታታት በሁሉም ቀለሞች፣ ቅርጾችና መጠኖች ሊገለጽ ይችላል**
እርስ በርሳችን ልንበረታታ የምንችልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። በዋናነት የማበረታቻ ቃላት የሚተላለፉት በንግግር ነው። ነገር ግን የጽሑፍ ማስታወሻዎች፣ የስልክ ጥሪዎችና ፈገግታም ሳይቀር የማበረረታቻ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከአንድ ሰው አጠገብ መገኘት ብቻ ራሱ የማበረታቻ ምንጭ ሊሆን ይችላል።
**መርህ አምስት፡ ማበረታታት አገልግሎት ነው**
ብዙውን ጊዜ እንደ አገልግሎት የምንቆጥረው ስብከትን ብቻ ነው። ነገር ግን ስብከት ጠቃሚ አገልግሎት ቢሆንም፣ ሰዎችን የምናገለግልበት ብቸኛው መንገድ አይደለም። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የማበረታታትን አገልግሎት ሰጥቷል።
ወጣቶቹ አራት ወይም አምስት አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች እንዲከፋፈሉ ጠይቃቸው። ለእያንዳንዱ ሰው አንድ ወረቀት ስጥ። ከወረቀቱ አናት ላይ፣ «እርስ በርሳችን እንበረታታ» የሚል ዓረፍተነገርና ስማቸውን እንዲጽፉ ንገራቸው። ከዚያም ወረቀቱን ከቀኛ

ቸው በኩል ላለው ሰው ይሰጡታል። እያንዳንዱ ሰው ስም የተጻፈበትን ወረቀት ሲያገኝ ለልጁ የማበረታቻ አስተያየቶችን ይጽፋል። ለምሳሌ፣ ፈገግታህ ደስ ይላል። ሁልጊዜም የወዳጅነት መንፈስ ይታይብሃል። ለሌሎች የሚገድህ ዓይነት ሰው ነህ፣ ወዘተ. እያሉ ሊጽፉ ይችላሉ። ሁሉም ሰው የየራሱን ወረቀት መልሶ እስኪያገኝና የተጻፉለትን አስተያየቶች እስኪያነብ ድረስ ወረቀቶቹ ከአንዱ ወደ ሌላው መተላፋቸውን ይቀጥላሉ።

በጸሎት ፈጽሙ።

# እርስ በርሳችን እንመካከር

ዕብራውያን 10:25



## ራስህን መቆጣጠር

ከዳግ ራንያን

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. በክርስቶስ ለማደግ ከፈለግን ራሳችንን እንዴት እንደምንቆጣጠር መማር አለብን።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች ለዕለታዊ ሁኔታዎች የሚሰጧቸው ምላሾች ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆኑ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶች እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ የራሳቸውን ውሳኔዎች የሚያስተላልፉበት ነጻነትና ከወላጆቻቸው ወይም ከሌሎች አዋቂዎች ቁጥጥር ውጭ የሚሆኑባቸው ጊዜያት ይሰጧቸዋል። በተጨማሪም፣ ሰውነታቸው እያደገ በሚሄድበት ጊዜ ሥጋዊ ፍላጎቶቻቸውና ስሜታዊ ምላሾቻቸው ይለወጣሉ። እነዚህ ለውጦች ከዚህ በፊት የማያውቋቸው ፍላጎቶችና ስሜቶች እንዲከሰቱባቸው ያደርጋሉ። ስለሆነም ነው፣ ዕለታዊ ሁኔታዎችን ገንቢና የክርስቶስን በሚመስል መንገድ ለመቆጣጠር (ሁኔታዎቹ ሳይቆጣጠሯቸው) መማር የሚኖርባቸው።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. የተወሰኑ ቁጥሮች ሲያጋጥሙ መቆም። የቡድኑ አባላት በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ ንገራቸው። አንድ ሰው «1» ቁጥርን እንዲጠራ ጠይቅና እስከ «20) ቁጥር ድረስ በክቡ ዙሪያ የሚገኙ ልጆች ተራ በተራ እንዲጠሩ አድርግ። ሁለት ወይም ከዚያ የሚበዙ ቡድኖች ካሉ፣ ማን ከሁሉም ፈጥኖ እንደሚፈጽም ተመልከት። ይህንን ካደረግህ በኋላ፣ አሁን ሲጠሩ የተዘጋጁት ቁጥር በ«ስ» ወይም በ«አ» የሚጀምር ከሆነ እንዲቆሙ ትነግራቸዋለህ። (ቁጥሩን ሳይጠሩ መነሣት አለባቸው።) ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ቡድኖች ካሉ፣ የትኛው ቡድን ከሌሎች ፈጥኖ ይህንኑ እንደሚያደርግ ተመልከት። በሚስቱበት ጊዜ ሁሉ እንደገና ይጀምራሉ።
2. ራስን የመቆጣጠር ጨዋታ። ከወጣቶቹ አንዱን ፊት ለፊት አስቁመውና በምንም ዓይነት ፈገግ ማለት እንደማይችል ንገረው። ከዚያም ለአንድ ደቂቃ ያህል በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች እሱን ፈገግ ለማሰኘት የሚችሉትን ጥረት ሁሉ እንዲያደርጉ ንገራቸው። ወጣቶቹ ልጁን ከመንካት (ከመኮርኮር) ውጭ የመሰሏቸውን ቃላትና ድርጊቶች ሁሉ በመጠቀም ፈገግ

እንዲልላቸው ሊሞክሩ ይችላሉ:: አንዷ ደቂቃ እስክትጠናቀቅ ድረስ ፈገግ ሳይል ለቆየ ልጅ ሽልማት ስጠው::

3. የቡድን ዝማሬ::

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)

ለመጨረሻ ጊዜ መጥፎ ስሕተት የፈጸምኸው መቼ ነበር? ምናልባትም ጓደኛህ ሳያውቅ የቤት ሥራህን የሠራህባቸውን ወረቀቶች ቆሻሻ ማስቀመጫ ውስጥ በጣለብህ ጊዜ ይሆናል:: በዚህ ጊዜ የቅርብ ጓደኛህ በቆሻሻው ውስጥ ወረቀቶችህን ስትፈልግ በአጠገብህ አለፈ:: ምላሽህ «ቁጥጥር የተደረገበት» ነበር? ትልቁ ፈተናህ ነገ እስኪሆን ድረስ ሳታጠና በቆየህበትና በዚያው ምሽት ግን የምትደግፈው የእግር ኳስ ቡድን ለዋንጫ የተጫወተበትስ ዕለት? ጨዋታው ረዥም ጊዜ ወሰደ:: አንደኛውን ምዕራፍ አጥንተህ ሳትጨርስ በፊት እንቅልፍ ተጫጫነህ:: ውጤት በተነገረበት ጊዜ ምላሽህ ምን ነበር? ላገኘኸው መጥፎ ውጤት ማንን ወቀስህ? ምላሽህን ተቆጣጠርህ ወይስ አልተቆጣጠርህም? እስኪ አንድ ሌላ ሁኔታ እንመልከት::

ታቦ በትምህርት ቤት በሌሎች ወጣቶች፣ በተለይም ባልደኑት ተማሪዎች ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ነበር:: ባለፈው እሑድ ሰባኪው «ራስን በመቆጣጠር ፍሬ አማካኝነት የዲያብሎስን ወጥመዶች ማስወገድ» በሚል ርእስ ያቀረቡት ስብከት ወደ ታቦ ልብ የዘለቀ ነበር:: መጋቢው በየቀኑ መጸሐፍ ቅዱስን በማጥናት፣ ከዕለታዊ ሕይወታችን ጋር እንዴት እንደሚዛመድ በማሰብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገርና የሚነግረንን በመስማት ሰፊ ጊዜ ማሳለፉ ጠቃሚ እንደሆነ ገልጸው ነበር:: ችግሩ ታቦ ከትምህርት ቤት ተመልሶ ለሁለት ሰዓታት ያህል እግር ኳስ ከተጫወተ፣ እራቱን ከበላና የቤት ሥራውን ከሠራ በኋላ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መጸለይ ይደክመዋል:: ታቦ እግዚአብሔርን ይወዳል:: ነገር ግን ብዙ ራስን የመግዛት ወይም የመቆጣጠር ብቃት የለውም:: ታቦ ኪጎትሶን ወደ ቤተክርስቲያን የጋበዘው ሲሆን፣ በዚህም ተግባሩ ደስ ይሰኛል:: ነገር ግን ኪጎትሶ የእንግሊዝኛ የቤት ሥራውን ስለሚያስገለብጠው ይከፋዋል:: ነገር ግን አቋርጨን አማራጭ በመጠቀም እግረ መንገዱን የኪጎትሶን መልሶችም ለራሱ ይገለብጣል:: ታቦ ክርስቲያን ወጣቶች ለሚሰጠው ክርስቲያናዊ ምስክርነት እንደሚያደንቁት ያውቃል:: አሁን ግን ምስክርነቱ አደጋ ገጥሞታል:: ምክንያቱም ባለፈው ምሽት በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ከመሪዎቹ ጋር ተከራክሯል:: ታቦ እግዚአብሔርን የሚወድና ትክክለኛውን ተግባር ለመፈጸም የሚጥር ወጣት ነው:: ነገር ግን ታቦ የክርስትና ሕይወቱ ለምን እሱ ሊሆን ይገባዋል በሚለው መልኩ እንደማይስተካከልለት ሊገባው አልቻለም::



መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ::)

1. የታቦ አሳቦችና ተግባራት እርስ በርሳቸው የሚጋጩት እንዴት ነው?
2. የታቦ ተግባራት ከእግዚአብሔር መመዘኛዎች ጋር የሚጋጩት እንዴት ነው?
3. ታቦ መንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲስተካከል ምን ማድረግ አለበት?
4. በታቦ ሕይወት ውስጥ የጎደለው ነገር ምንድነው?
5. ከታቦ ታሪክ ውስጥ የራስህን የሚመስል ነገር አይተሃል? በዚህ ታሪክ ውስጥ ራስህን የሚያስታውስህ ነገር ምንድነው?
6. ወጣቶች ምላሾቻቸውን ሊቆጣጠሩ የሚገባቸው ሌሎች ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው::)

1. 1ኛ ጴጥሮስ 5:8-9: *«ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና:: በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት::»*
   ሀ. ሰይጣን የአንበሳን የሚመስል ብልጠትና ተፈጥሯዊ ችሎታዎች አሉት:: መቼና እንዴት ሊያጠቃን እንደሚችል ያውቃል:: ሰይጣን ሊያጠቃን እንደሚፈልግ ማወቅ አለብን:: ሕይወታችንንም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ውስጥ ልናደርግና እንድንከተል የሚፈልገውን መስመር ተከትለን መጓዝ ይኖብናል::
   ለ. ሰብአዊ ፍላጎቶቻችንና ስሜቶቻችን ሊቆጣጠሩን አይገባም:: ይልቁንም እኛ ልንቆጣጠራቸው ይገባል:: ፍላጎቶቻችንንና ስሜቶቻችንን ካልተቆጣጠርን ሰይጣን በነሱ ተጠቅሞ ሊያጠቃን ይችላል:: ሰይጣን በኛ ላይ የሚሰነዝረውን ጥቃት ልንቋቋም የምንችለው ፍላጎቶቻችንና ስሜቶቻችን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር የሆኑ እንደሆነ ብቻ ነው::
2. ምሳሌ 25:28: *«ቅጥር እንደሌላት እንደፈረሰች ከተማ፣ መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው::»* በጥንት ዘመን በግንብ ያልታጠሩ ከተሞች ለጥቃት ልቅ እንደነበሩ ሁሉ፣ ሰይጣን ራሱን የማይቆጣጠረውን ሰው በቀላሉ ያጠቃዋል::
3. ገላትያ 5:22-25: *«የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው... የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ:: በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ::»*

ሀ. ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ወይም መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ እንዳለ ከሚያሳዩ ውጫዊ መገለጫዎች ዝርዝር ውስጥ ራስን መግዛትን ጨምሮታል።

ለ. ጳውሎስ ሰብአዊ ሥጋችንን ወይም የኃጢአትን ተፈጥሮ ከምኞታዊ መሻቶቹ ጋር እንዴት ልንቆጣጠር እንደምንችል ነግሮናል። ይኸውም ሥጋችን ከክርስቶስ ጋር እንዲሰቀል በማድረግ የሚከናወን ነው። ክርስቶስ ምንም ኃጢአት ሳላሠራ፣ በመስቀል ላይ ለኛ ኃጢአት ሊሆን ችሏል። የኃጢአት ባሕርያችንን ለክርስቶስ አሳልፈን ከሰጠን በኋላ በኃጢአት ባሕርያችን ቁጥጥር ሥር መኖር የለብንም።

ሐ. ጳውሎስ ራሳችንን ልንቆጣጠር የምንችለው ደረጃ በደረጃ በመንፈስ ቅዱስ በመመላለስ መሆኑን በመግለጽ፣ ይህንን ክፍል ያጠቃልላል።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. እነዚህ ምንባቦች ራስን ስለ መግዛት አስፈላጊነት ምን ያስተምሩሃል?
2. አንደኛው ጥቅስ ራሱን የማይገዛ ሰው ምን ይመስላል ይላል? መልስህን አብራራ።
3. ሰበእዊ (የኃጢአት) ፍላጎቶችና ስሜቶች ከሚገለጹባቸው መንገዶች አንዳንዶቹን ልትጠቃቅስ ትችላለህ? በሌላ አገላለጽ፣ ራስን የመቆጣጠር ትግሎች የሚካሄዱት በየትኞቹ የሕይወትችን ክፍሎች ነው?
4. ሰብአዊ (የኃጢአት) ባሕርያችንን ከቁጥጥር ሥር ልናውል እንችላለን? ከሆነ፣ እንዴት?
5. ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ እንዳለ ለሰዎች ያረጋግጣል ያለው ምንድነው?

ሰ. መዝጊያ (የሚከተለውን ለቡድኑ አባላት አንብባቸው።)

ራስህን በመቆጣጠር ለመኖር ከፈለግህ፣ ወደዚሁ ስፍራ የሚያደርሱትን ቀጣይ መምሪያዎች ልትከተል ይገባል።

1. በሕይወታችን ውስጥ አንዳንድ ነገሮች ከሌሎች የበለጠ ለመቆጣጠር የሚያስቸግሩ መሆኑን ተገንዘብ።

   ለአንተ ለመቆጣጠር የሚያዳግትህ ነገር ለሌላው ሰው ቀላል ሊሆን ይችላል። ይህ ግላዊ ጉዳይ ነው። ይሁንና፣ ግልጽና ታማኝ መሆን አለብህ። እግዚአብሔር ሊረዳን የሚችለው የተወሰነ የሕይወታችን ክፍል በመቆጣጠሩ በኩል ችግር እንዳለብን ስንነግረው ነው።

2. ይህን ችግር ክርስቶስ እየተቆጣጠረው አለመሆኑን አምነህ ተቀበል።



   ይህ በተለይ ለወጣቶች አምኖ ለመቀበል የሚያስቸግር ጉዳይ ነው። ለወጣቶች ራስን መቆጣጠር ማለት ሙሉው ማንነትን ለክርስቶስ ቁጥጥር ማስገዛት ማለት ነው።

3. ይህን ችግር ለእግዚአብሔር መስጠት እንዳለብህ ተገንዘብ።

   ክርስቲያን፣ «ጌታ ሆይ፣ ይህንን ራስን የመግዛት ችግር ለማሸነፍ ሞክሬአለሁ። ነገር ግን አልቻልሁም። እባክህን የዚህን ጉዳይ ቁጥጥር ተረክበህ ከራስህ ቁጥጥር ሥር አድርገው። የምደገፈው በአንተ ላይ እንጂ በራሴ ብርታት ላይ አይደለም» የሚልባቸው ጊዜያት አሉ።

4. ይህንኑ የሕይወት ክፍል ተቆጣጥረህ እንድትዘልቅ ጸልይ።

   መንፈስ ቅዱስ ሕይወትህን የሚቆጣጠረው በጸሎትና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመንፈስ ቅዱስ ስትመላለስ ብቻ ነው።

5. ራስህን እንድትገዛ የሚጠይቅ ሁኔታ ሲያጋጥምህ፣ የሚከተሉትን ሦስት ቀላል ጥያቄዎች ለራስህ አቅርብ።

   ሀ. ይህን ማድረጉ ጠቃሚ ነው? ይህን ተግባር ልፈጽም ወይስ አልፈጽም? ይህ የተሻለ ሰው ወይም የተሻለ ክርስቲያን ያደርገኛል?

   ለ. ይህ ሁኔታ በሕይወቴ ላይ መልካም ተጽዕኖ ይኖረዋል? ከዚህ ተግባር የተነሣ የተሻልሁ ሰው እሆናለሁን?


   ሐ. ይኼ እግዚአብሔርን ያስከብራልን? ይህ ተግባር ክርስቶስን በማስከበር ሌሎች ሰዎች እንዲከተሉት ያነሣሣል ወይስ ሰዎች በክርስትና እምነት ላይ ጥያቄ እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል? 1ኛ ቆሮንቶስ 10:23፣ 31 አንብብ።

ራስን ለመቆጣጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ የት ላይ ነህ? ፍላጎቶችህ እየተቆጣጠሩህ ነው ወይስ ፍላጎቶችህን እየተቆጣጠርህ? ራስህን በመቆጣጠርህ ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ውስጥ እንዳለ እየተገነዘቡ ነው? ካልሆነ፣ አሁኑኑ ሰብአዊ (ሥጋዊ) ባሕርይህን ለክርስቶስ አሳልፈህ እንድትሰጥ ላበረታታህ እፈልጋለሁ። ደካማ ስለሆንህባቸው የሕይወት ክፍሎች አስብ - ንዴት፣ ንጹሕ ያልሆኑ ወሲባዊ አሳቦች ወይም ተግባራት፣ ለወላጆችህ ወይም ለሌሎች ሰዎች ያለህ መጥፎ አመለካከት፣ ወዘተ. እነዚህን ነገሮች አሁኑኑ ለክርስቶስ አሳልፈህ ስጥ። የሚከተለውንም ጸሎት ጸልይ።

ውድ እግዚአብሔር ሆይ፣ ስለ ድክመቶቼና ውድቀቶቼ ለአንተ እናዘዛለሁ። አሁኑኑ የኃጢአት ተፈጥሮዬንና ፍላጎቶቼን ለአንተ አሳልፌ እሰጣለሁ። በምትሰጠኝ ራስን የመቆጣጠር ኃይል

አማካኝነት መንፈስ ቅዱስህ በውስጤ እንዳለ ሌሎች ሰዎች እንዲመለከቱ ይሁን። የሕይወቴ ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጸልያለሁ። አሜን።

## መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ



## ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ። ማቴዎስ 5፡16



## «አትጨነቁ!»

ሱዚ ሽለንበርገር

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ ፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹ በጭንቀት እንዲናጡ አይፈልግም።
2. የትምህርቱ ዓላማ ፡፡ ይህ ትምህርት ወጣቶች የሚያሳስቧቸውንና የሚያስጨንቋቸውን ነገሮች በእግዚአብሔር እጆች ላይ ማኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያስተምራቸዋል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ ፡፡ ምናልባትም በቡድንህ ውስጥ ከሚገኙት ወጣቶች አብዛኞቹ ስለ አንድ ነገር በመጨነቅ ብዙ ጊዜ ያጠፉ ይሆናል። በወጣትነታቸው ጊዜ ጭንቀታቸውን እንዴት ሊቆጣጠሩ እንደሚችሉ ከተማሩ፣ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ዓይነት በእምነት የተሞሉ አዋቂዎች ወደመሆኑ ደረጃ እየበሰሉ ይሄዳሉ።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች ፡፡ የማብሰያ ድስት፣ እርሳሶችና ክብሪቶች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. የመተማመን ጉዞ። ለቡድንህ ወጣቶች መተማመን የመጨነቅ ተቃራኒ መሆኑን አብራራላቸው። ከመጨነቅ ይልቅ መተማመን ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ይህ ጨዋታ ያግዛቸዋል። ወጣቶቹ ሁለት ሁለት እየሆኑ ቡድን እንዲፈጥሩ ንገራቸው። ከሁለቱ አንደኛው ዓይኖቹን በጨርቅ ይሸፈናል። (ወይም በእምነት ዓይኖቹን እንዲጨፍን ማድረጉ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል።) ሌላኛው ልጅ በመተማመን ጉዞ ላይ «ዓይነስውሩን» ይመራዋል። የማያየው ልጅ ወዴት እንደሚሄድ አያይም። የሚያየውን ልጅ ሊነካው ወይም ሊይዘው አይችልም። መሪው ድምጹን በማሰማት ብቻ ይመራዋል። ይህ ጨዋታ ሌላውን ሰው በመተማመን ሙሉ በሙሉ በሱ ምሪት ላይ መደገፍ ምን ማለት እንደሆነ ለወጣቶቹ ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል። ለሁሉም ወጣቶች የአምስት ደቂቃ ጊዜ ስጣቸው። እያንዳንዱ ቡድን ጨዋታውን ሲጨርስ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቃቸው።

   ሀ. በሰው ላይ ሙሉ በሙሉ መተማመን ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል?

   ለ. የት እንደምትሄድ በማሰብ ለመጨነቅ የተፈተናችሁበት ጊዜ ነበር?

ሐ. በመተማመን ጉዞው ወቅት በሌላ ሰው መተማመን ቀላል ነው ብላችሁ ያሰባችሁበት ጊዜ ነበር? ለምን?

መ. ትልቁ ጭንቀታችሁ ምን ነበር?

ሠ. የሚመራችሁን ሰው እንዳታምኑ ችግር የፈጠረባችሁ ነገር ነበር?

2. የጭንቀት ድራማዎች። እያንዳንዱ ቡድን ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ስለሚጨነቁበት አንድ ነገር ድራማ እንዲሠራ የአሥር ደቂቃ ጊዜ ስጣቸው። በድራማቸው ውስጥ የሆነ ቦታ ላይ በማቴዎስ 6:27 የተገለጸውን አሳብ መጠቀም ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ ቡድን ድራማውን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ከወሰደ በኋላ፣ ድራማውን ለሁሉም ወጣቶች እንዲያቀርቡ ጋብዛቸው።
3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

አንዳንድ ጊዜ ሊከሰቱ ስለሚችሉና ዳሩ ግን በፍጹም ስለማይከሰቱ ነገሮች እንጨነቃለን። ከፍተኛ የጭንቀት ችግር ስለነበረባት አንዲት ወጣት የሚናገር ታሪክ እነሆ።

ዊልማና ቤተሰቧ በትምህርት ዓመቱ አጋማሽ ላይ ከነበሩበት ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ተዛወሩ። ዊልማ በትምህርት ቤትና በቤተክርስቲያን ሥራዎች ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ታደርግ ነበር። ዊልማ ቤተሰቦቿ ወደ አዲስ ከተማ በመዛወራቸው ምክንያት ጓደኞች አይኖሩኝም ብላ ተጨነቀች። «ሁሉም ሰው ጓደኛ ይዞ ስለሚያበቃ ከነሱ ጋር መኖር የምችል አይመስለኝም!» ስትል በወላጆቿ ላይ አለቃቀሰች።

ዊልማ በሚቀጥለው እሑድ ማለዳ የሰንበት ትምህርት ክፍል ውስጥ ፔጊ የምትባል ልጅ አገኘች። በጭውውታቸው ወቅት፣ ዊልማ ፔጊ ወደምትማርበት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደምትገባ ተገነዘበች። ፔጊ በሚቀጥለው ቀን አብራት ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድና ከአንዳንድ ጓደኞቿ ጋር ልታስተዋውቃት እንደምትችል ለዊልማ ገለጸችላት።

ዊልማ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ እየተዘጋጀች ሳለች ፈራ ተባ ትል ጀመር። «ልብሶቼን ባይወዱስ? ልክ በሌላ ዓለም ውስጥ ያለሁ መስሎ ይሰማኛል። አነጋገሬ ቢያስቃቸውስ? ማንም ሰው አይወደኝም ብዬ እጨነቃለሁ።» ፔጊ ወደ ዊልማ ቤት መጣች። ዊልማ፣ «ወደ ትምህርት ቤት አብረሽኝ በመሄድሽ አመሰግንሻለሁ። ግን ለምን መጣህ? በራሱ ጥረት ጓደኛ ማፍራት የማልችል መስሎሽ ነው? ምናልባትም ትክክል ልትሆኚ ትችያለሽ። አነጋገሬ ከሌሎች ልጆች እንደሚለይ አውቃለሁ። ዛሬ ሁሉም ሰው ይስቅብኛል ብዬ እፈራለሁ» አለቻት።

ፔጊም፣ «መጨነቅ የለብሽም። በትምህርት ቤታችን አንዳንድ አሪፍ ልጆች አሉ። አብዛኞቹ አዳዲስ ተማሪዎች የተቀባይነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ ይጥራሉ» ስትል መለሰችላት።



ዊልማ በትምህርት ቤት የመጀመሪያውን ቀን ከጨረሰች በኋላ፣ የቤት ሥራዋን በሚገባ ሠርታ አስተማሪዋን ስለምታስደስትበት መንገድ እያሰበች መጨነቅ ጀመረች። «አዲስ ተማሪ ስለሆንሁ ምናልባት አስተማሪዎቹ ከእኔ ብዙ ሥራ ይጠብቁ ይሆናል። እንዳደርግ የሚፈልጉትን እንደማደርግ ተስፋ አደርጋለሁ» ስትል አሰበች።

ፔጊ ዊልማን በቤተክርስቲያን ውስጥ ወደሚደረገው የወጣቶች የመዘምራን ልምምድ ላይ ጋበዘቻት።

ዊልማ፣ «አዘማመሬን ባይወዱትስ?» ስትል ጠየቀች።

ፔጊ፣ «ጥሩ አድርገሽ እንደምትዘምሪ አይጠረጠርም። በዝማሬው ውስጥ እንድትሳተፊና የቡድኑ ጠቃሚ ክፍል መሆንሽን እንድትረጂ እንፈልጋለን» ስትል መለሰችላት።

የቤት ሥራዋን የምትሠራበት ጊዜ እንዳያንሳት ስለሰጋች፣ «የመዝሙር ልምምዱ በስንት ሰዓት ነው የሚያልቀው?» ብላ ጠየቀች።

ፔጊ፣ «ዛሬ ማታ መዝሙር ከተለማመድን በኋላ የሳንዱችና የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ይደረግልናል» ስትል መለሰችላት።

ዊልማ፣ «ሰዎቹ ሳንዱች ለመብላት ስል የመጣሁ ይመስላቸዋል» ስትል ጮኸች።

ፔጊ፣ «ሁልጊዜም ተጨማሪ ሳንዱቾችን መጠቀም እንችላለን። ከቤት ይዘን ብንመጣ የተሻለ ስሜት ይሰማሻል?» ብላ ጠየቀቻት።

ዊልማ፣ «አዎ፣ ጥቂት ሳንዱቾች ይዤ እመጣለሁ» አለች።

በዚህ ጊዜ ፔጊ ዊልማ ከጓደኞቿ መካከል ለመቀላቀል በመሞከሯ ትክክለኛ ውሳኔ ማድረጓን ትጠራጠር ጀመር። ዊልማ ሁልጊዜም የምትጨነቅበትን ምክንያት የማታጣ ዓይነት ልጅ ነበረች።

ማታ ዊልማ ፔጊን ቤተክርስቲያን ውስጥ ስታገኛት፣ «ዛሬ እዚህ እንድመጣ ስለጋበዝሽኝ በጣም አመሰግንሻለሁ፣ ፔጊ» አለቻት። «ግን ሰዎቹ ሳንዱቾቼን የሚወዱት አይመስለኝም። አዘማመሬንም እንደማይወዱት እርግጠኛ ነኝ» አለች።

«በቃሽ» ስትል ተቆጣቻት ፔጊ። «በጣም ትጨነቂያለሽ! ከመዝሙር ልምምዱ በኋላ ስለዚሁ የጭንቀት ችግርሽ ከመዘምራን ቡድን መሪው ጋር መነጋገር አለብሽ።»

«ይኼማ አይሆንም። ምን እለዋለሁ?»

መ. የመወያያ ጥያቄዎች

ወጣቶቹን የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍልና የሚከተሉትን መመሪያዎች ስጣቸው።

ዊልማ የምትገኝበት የወጣቶች አገልግሎት መሪ ብትሆን፣ ምን ምክር ትሰጣታለህ? ማቴዎስ 6:25፣ 27 እና ፊልጵስዩስ 4:6ን አንብብ። ለዊልማ ምን ዓይነት ምላሽ ትሰጣታለህ?

እያንዳንዱ ቡድን ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ እንዲያዘጋጅ አሥር ደቂቃ ስጣቸው፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ቡድን ምክሩን ለሁሉም ወጣቶች እንዲያካፍል አድርግ፡፡

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው፡፡)

1. ሉቃስ 10:38-42 .. ማርታ በሥራ ከመወጠሯ የተነሣ ከጌታ ጋር የመቀመጥና የማረፍ እድሏን አጥታለች፡፡ ጠቃሚ ስላልሆኑት ነገሮች ከመጠን በላይ በመጨነቋ ምክንያት ከሁሉም የሚበልጠውን ነገር (የዓለም ፈጣሪ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አብሮ መሆን) አጥታለች! ማርታ ምግብ በማዘጋጀቱ ሥራ በመጠመዷ ምክንያት ሁሉን የሚችል አምላክ ባለበት ስፍራ መሆኗን ለመገንዘብ ሳትችል ቀርታለች! እኛም ብዙውን ጊዜ በተመሳሳይ ወጥመዶች እንያዛለን፡፡ በሥራችን ተወጥረን ስለምንገኝ አንዳንድ ጊዜ ጌታ በመካከላችን እያለ ሳናየው እንቀራለን፡፡
2. ማቴዎስ 6:23-34 .. ክርስቶስ ስለ ችግሮቻችንና ስለሚያሳስቡን ነገሮች በማሰብ ጊዜያችንን እንድናጠፋ አይፈልግም፡፡ እነዚህን ነገሮች አሳልፈን እንድንሰጠው ይፈልጋል፡፡ እርሱ የሞተው ነገሮች ለኃጢአታችን ሳይሆን... ለችግሮቻችንና ለሚያሳስቡን ነገሮች ጭምር ነው፡፡
   ብዙውን ጊዜ ከመጸለይና ችግሮቻችንን ለጌታ አሳልፈን ከመስጠት ይልቅ፣ ዝም ብለን እየተጨነቅን እንኖራለን፡፡ ኢየሱስ ችግሮቻችንን አሳልፈን እንድንሰጠው ይፈልጋል፡፡ እርሱ ስለነዚህ ነገሮች ሊጨነቅልን ይፈልጋል... ለርሱ አሳልፈን ከሰጠን ይህንኑ እንደሚያደርግልን ግልጽ ነው፡፡ መጸለይ፣ ተስፋ ማድረግና ጌታን በችግሮቻችን ሁሉ ሙሉ በሙሉ መተማመን የኛ ኃላፊነት ነው፡፡

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

የአስጨናቂ ነገሮች ዝርዝር፡፡ የቡድንህ አባላት ወጣቶች የሚጨነቁባቸውን ጉዳዮች እንዲዘረዝሩልህ ጠይቃቸው፡፡ ከወጣቶቹ አንዱ እነዚህን ነገሮች በወረቀት፣ በፖስተር ወይም በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲዘረዝር ጠይቅ፡፡ (ምሳሌ፡ ልብስ፣ ጓደኛ፣ ትምህርት ቤት፣ ገንዘብ፣ ወዘተ.)

ሰ. መዝጊያ .. እነዚያን ጭንቀቶች አቃጥላቸው

ለዚህ ተግባር ድስትና ክብሪት ያስፈልግሃል፡፡ ለወጣቶቹ ወረቀትና እርሳስ ስጣቸውና የሚያስጨንቋቸውን አንዳንድ ነገሮች እንዲጽፉ ንገራቸው፡፡ ወደፊት ሊያስጨንቋቸው የሚችሉትን የትኞቹንም ችግሮች እንዲጽፉ አበረታታቸው፡፡ ሁሉም ሰው ጽፎ ከጨረሰ በኋላ፣ ወጣቶቹ በጸሎት የሚያስጨንቋቸውን ነገሮች ለእግዚአብሔር አሳልፈው



እንዲሰጡ አድርግ፡፡ ከዚያም ወረቀቶቻቸውን ድስቱ ውስጥ ጨምረው እንዲያቃጥሉ ንገራቸው፡፡ የችግሮቻቸውና የጭንቀቶቻቸው ዝርዝሮች ሲቃጠሉ በሚመለከቱበት ወቅት፣ ወጣቶቹ እነዚህን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ለጌታ አሳልፈው እንደሰጡ አስገንዝባቸው፡፡ በተጨማሪም፣ ይህ በተግባር ሊያከናውኑት የሚገባው እርምጃ ተምሳሌታዊ አፈጻጸም መሆኑን ግለጽላቸው፡፡